የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት

ቮልዩም ፲፩ (፲፱፻፸፬ ዓ. ም.)



JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

Vol. 11 (1980)

የኢትዮጵያ ሕግ

መጽሔት ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት
ከሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር
የሚያዘጋጀው ።

፲፱፻፷፪ ዓ. ም.

001786

ትምህርት ሊሰጡ የሚችሉ ሕግን የሚመለከቱ የምርምር ጽሑፎችን ፣ በፍርድ ቤት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ ጠቃሚ የፍርድ ትችቶችን ፣ በሕጎችና በሌሎችም ሕግ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ብት ልኩልን በደስታ የምንቀበል መሆናችንን እንገልጻለን ።

ለዚህ መጽሔት ደንበኞች መሆን የምትሹ ሁሉ ፍላጎታችሁን በአድራሻችን ጽፋችሁ ወይም ደውላችሁ ብትገልጹልን በፍላጎታችሁ መሠረት ለመፈጸም ዝግጁ ነን ።

ለአገር ውስጥ ደንበኞች የያንዳንዱ መጽሔት ዋጋ 5 (አምስት) የኢት ብር ሲሆን ፣ ለመላኪያ እንደ ሁኔታው ተጨማሪ ክፍያ ይደረጋል ።

አድራሻችን ፤—

የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፤ የሕግ ትምህርት ቤት
ፖ. ሣ. ቁ. 1176
አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ

ስልክ ቁጥር ፡ 11-17-33 ወይም 11-08-44 (108) ነው ።

የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ትምህርት ቤት
ከሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር
የሚያዘጋጀው ።

የቦርድ አባሎች

ከበደ ገብረማርያም ፤
ሊቀ መንበር
የሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ፤ ቋሚ ተጠሪ

ፋሲል ናሆም ፤
የሕግ ፋኩልቲ ዲን
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ጆርጅ ክሽችኖቪች ፤
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሕግ ፋኩልቲ ፕሮፌሰር

ተሾመ ጋይለ ማርያም ፤
የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

ሰላሙ በቀለ ፤
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሕግ ፋኩልቲ ረዳት ፕሮፌሰር

አሰፋ ሊበን ፤
የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

አዘጋጆች

ፋሲል ናሆም ፤
ዋና አዘጋጅ

ዝጅስዋቭ ጋሊስኪ ፤
የምርምር ጽሑፎች አዘጋጅ

ዮሴፍ ገብረ እግዚአብሔር ፤
የአስተያየቶችና የፍርድ ትችቶች አዘጋጅ

ይታይህ ዘለዓለም ፤
ሥራ አስኪያጅ አዘጋጅ

የሕግ ትምህርት ቤት መምህራን (፲፱፻፫፪ ዓ/ም)

በ፲፱፻፺፮ ዓ/ም ተቋቁሞ በአሁኑ ጊዜ የኤል ኤል ቢ ዲግሪና የሕግ ዲፕሎማ ትምህርቶችን የሚሰጠው የአዲስ አበባ ዩኑቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት መምህራን የሚከተሉት ናቸው ።

ፋሲል ናሆም ፤ ኤል ኤል ቢ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ጀይ ኤስ ዲ ፤
ረዳት ፕሮፌሰርና የፋኩልቲው ዲን

በላይነህ ሥዩም ፡ ኤል ኤል ቢ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ሌክቸረርና ረዳት ዲን

ዳንኤል ኃይሌ ፤ ኤል ኤል ቢ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ረዳት ፕሮፌሰር

ኤፍሬም የማነ ብርሃን ፤ ኤል ኤል ቢ ፤ ረዳት ምሩቅ

ዝጅስዋቭ ጋሊትስኪ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ኤል ኤል ዲ ፤ ረዳት ፕሮፌሰር

ግርማ ወልደ ሥላሴ ፤ ኤል ኤል ቢ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ጀይ ኤስ ዲ ፤ ረዳት ፕሮፌሰር

ጆርጅ ክሽችኖቪች ፤ ቢ ኤ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ሊክ ሰክ ኮምና ፖሊት ፤
ዶክተር ጄር ፕሮፌሰር

ሄንሪክ ሌሰቼና ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ኤል ኤል ዲ ፤ ረዳት ፕሮፌሰር

ሰላሙ በቀለ ፤ ኤል ኤል ቢ ፤ ረዳት ፕሮፌሰር

ሰሎሞን ጅሩ ፡ ቢ ኤስ ሲ ፤ ኤል ኤል ቢ ፤ ሌክቸረር

ወርቁ ተፈራ ፤ ኤል ኤል ቢ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ረዳት ፕሮፌሰር

ይታይህ ዘለዓለም ፤ ኤል ኤል ቢ ፤ ሌክቸረር

የሴፍ ገብረ እግዚአብሔር ፤ ኤል ኤል ቢ ፤ ሌክቸረር

ገጽ

መቅድም 1

ከሕግ ፋኩልቲ የተሰጠ የፓፒያሮይ እና ፓፒያሮይ ዓ/ም ራፖር

በፋሲል ናሆም 3

የኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት ሮማዊ መሠረቶች

በፒተር ኤች ሳንድ... 7

የሶሻሊስት ኢትዮጵያ የሥራ ክንውኖች በመሠረታዊ ሕጎች እንደታየው

በፋሲል ናሆም 13

የኢትዮጵያን የመወለድ ሕግ በሚመለከት የተደረገ ተጨማሪ ጥናት

በጆርጅ ክሸችኖቪች 19

ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ሥስተኛ መንግሥታት

በዝጂስዋቭ ጋሊትስኪ 35

ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት ስለሚከብዱ ወንጀሎች ክስ አቀራረብ የተለየ ሥነ ሥርዓትና ዓላማው ፡ በማናቸውም ሁኔታ ተፈጻሚ ነት ይኖረዋል ወይ ?

በዮሴፍ ገብረ እግዚአብሔር 43

በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፩ሺ፯፻፷፯ ላይ የተሰጠ አስተያየት

በጆርጅ ክሸችኖቪች 47

ፍርድና በዚሁ ፍርድ ላይ የቀረበ ትችት

በጆርጅ ክሸችኖቪች 48-50

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

Published by the Faculty of Law, Addis Ababa University,
in co-operation with the Ministry of Law and Justice
(to be cited as 11 J. Eth. L.)
1980

IX

The Editors encourage all interested persons to submit to them any material which would be appropriate for publication in the journal such as works of scholarly research in the field of law, comments on court decisions and commentaries on legislations.

You are hereby invited to communicate to us your wish to subscribe to the *Journal of Ethiopian Law* and get copies of each issue.

The Rate for foreign subscribers is five dollars (American) per copy plus postage.

Our address Journal of Ethiopian Law
Addis Ababa University, Faculty of Law
P.O. Box 1176
Addis Ababa, Ethiopia
Telephone 11-17-33 or 11-08-44 (108)

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

Published by the Faculty of Law,
Addis Ababa University. in co-operation with the
Ministry of Law and Justice.

Editorial Board

Kebede Gebre Mariam,	*Chairman* *Permanent Secretary, Ministry of Law and Justice.*
Teshome Haile Mariam,	*President, Supreme Court.*
Aseffa Liben,	*President, Hight Court.*
Fasil Nahum,	*Dean, Faculty of Law, Addis Ababa University.*
George Krzeczunowicz,	*Professor, Faculty of Law, Addis Ababa University*
Selomu Bekele,	*Assistant Professor, Faculty of Law, A.A. University*

Editors

Fasil Nahum,	*Editor-in-chief*
Yoseph Gebre Egziabher,	*Cases and current Issues Editor*
Zdizslaw Galicki,	*Articles Editor*
Yittayih Zelalem,	*Managing Editor*

The editors are grateful for the the English language editorial assistance of Mrs. Innes Marshall of the Addis Ababa University Press.

Law Faculty Staff (1980)

The following are the staff members of the Faculty of Law of Addis Ababa University established in 1963 which offers courses leading to the LL.B Degree and Diploma in Law.

Fasil Nahum;	LL.B, LL.M, J.S.D., Assistant Professor, Dean
Belayneh Seyoum;	LL.B, LL.M, Lecturer, Assistant Dean
Daniel Haile;	LL.B, LL.M, Assistant Professor
Efrem Yemaneberhan;	LL.B, Graduate Assistant
Zdzislaw Galicki;	LL.M, LL.D, Assistant Professor
Girma Wolde Sellasie;	LL.B, LL.M, J.S.D., Assistant Professor
George Krzeczunowicz;	B.A., LL.M, Lic. Sc. Comm. Polit, Dr. Jur, Professor
Henryk Leszczyna;	LL.M, LL.D, Assistant Professor
Selamu Bekele;	LL.B, Assistant Professor
Solomon Jiru;	B.S.C., LL.B, Lecturer
Worku Tafara;	LL.B., LL.M., Assistant Professor
Yittayih Zelalem;	LL.B., Lecturer
Yoseph Gebre Egziabher;	LL.B, Lecturer

TABLE OF CONTENTS

Page

Preface 55

Progress Report from the Dean (1978-80)
by Fasil Nahum 57

Roman Origins of the Ethiopian "Law of the Kings" (Fetha Nagast)
by Peter H. Sand 71

Socialist Ethiopia's Achievements as reflected in its basic Laws
by Fasil Nahum 83

The Ethiopian Law of Filiation Revisited
by George Krzeczunowicz 89

International Treaties and Third States
by Zdzislaw Galicki 105

Special Procedure for the Charging of Offences Aggravated by previous convictions and its rationale: Implemented in all instances?
by Yoseph Gebre Egziabher 115

Comment on Civil Code Article 1767
by George Krzeczunowicz 121

Judgement and Case Comment
by George Krzeczunowicz 122-124

በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ነበር ፤ ያም ፥ ያሮጌ ዘመን መደምደሚያ ፥ ያዲስ ሕይወት በር መክፈቻ ወቅት ነበር ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ከዚያ ወዲህ ብዙ ተፃራሪ ኃይሎችን አሸንፎ አያሌ ሥር ነቀል ለውጦችን አስገኝቷል ። በዓላማና በፍልስፍና በኩልም መሠረታዊ የአቅጣጫ ለውጦችን አድርጎአል ። ትግሉ የማይበገርና የሕዝቡን ሕይወት በማናቸውም ረገድ የሚነካ እንደመሆኑ መጠን ገና አላከተመም ። ሕግና ፍትሕም በአብዮቱ በቀላሉ ተነክቶ የታለፈ አይደለም ። እንዲያውም ጉልህ የሆነው ማስረጃ የኢትዮጵያ አብዮት መሠረታዊ የሶሻል ለውጦችን ለማስገኘት በሕግ መሣሪያነት መጠቀሙ ነው ። እንደዕውነቱ ከሆነ ያለ ሕግ አመራር እሥራ ላይ የዋለ አንዳችም መሠረታዊ ለውጥ የለም ።

ይህን የዛሬውን እትምና ወደፊት በተከታታይ የሚወጡትን የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት እትሞች በማናቸውም የሕይወት ዘርፍ ማኅበራዊና ግለሰባዊ ፍትሕ ለማስገኘት ያልተቋረጠ ትግል ለሚያደርገው ለጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ መታሰቢያ ይሆኑ ዘንድ እናቀርባለን ። ወዲያውም ሕግና ተቅዋሞቹ ሁሉ በአዲስ አቅጣጫ ለጎ ብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ግንባታ አገልግሎት እንዲያበረክቱ ከልብ እንጥራለን ። ሕግ ሕይወት የሚያገኘው ለሰላም ለፍትሕና ለብልጽግና በብሔሮች ፥ በመደቦችና በግለሰቦች በሚደረገው የማያቋርጥ ትግል ነው የሚለውን ዐቢይ ቁም ነገር ልናስገነዝብ እንወዳለን ። እዚህም ላይ አንድ የታወቀ የሕግ ተመራማሪ የሰነዘረው አሳብ ጠቃሚና አግባብ ያለው ትምህርት ሆኖ እናገኘዋለን ።

> "ሕግ ንድፈ አሳብ ብቻ ሳይሆን ሕያው የሆነ ኃይልም ነው ። ስለዚህ ነው ፥ ፍትሕ ዕውነትን የምትመዝንበት ሚዛን በአንድ እጅዋ ይዛ በሥራ ላይ የምታውልበት ሰይፍ በሌላ እጅዋ የምትጨብጠው ። ሰይፍ ያለ ሚዛን ልጓም የለሽ የጭካኔ ኃይል እንደሆነ ሁሉ ሚዛኑም ያለሰይፍ የሕግ መዋቲነት ነው ። ሚዛንና ሠይፍ የማይነጣጠሉ ናቸው ። የሕግ ሥርዓት የሚሠምረውም (ፍጹም የሚሆነው) ፍትሕ ሰይፍን የምትጨብጥበት ኃይል ሚዛኑን ከምትይዝበት ጥበብ ጋር የሚስተካከል ሲሆን ብቻ ነው ።"

የዘመናዊ ኅብረተሰብአዊ መንግሥትን ምንነት መረዳት የሰይፉንና የሚዛኑን በትክክል መመጣጠን በዓይነ ልቦና መመልከት ማለት ነው ። ሰይፉና ሚዛኑ በሚ ገባ እንዲመጣጠኑም ለአገሪቱ ተገቢውን አገልግሎት ለማበርከት የሚያስችል ጥል ቅት ያለው የሕግ ትምህርትና ምርምር አስፈላጊና ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው ። ምንም እንኳ ሕግ የኅብረተሰብ ላዕላይ መዋቅር አንደኛው አካል መሆኑ ቢታወቅም የመንግሥት ኃይለኛ የፖሊሲ መሣሪያ ሆኖ በማገልገል ታህታይ መዋቅሩን ስለሚ ነካና እንዲለወጥም ስለሚረዳ በጊዜ ብዛት የላዕላይ መዋቅሩ ኃይለኛ ክፍል መሆኑን በተግባር አስመስክሯል ።

የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት ለብዙ ዓመታት ተቀብሮ ከቆየ በኋላ እንደገና መው ጣቱ ሕዝባዊ አብዮት ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያረጋግጥ ነው ። መጽሔቱ በአብዮቱ መንፈስ በመመራት ፣ የአብዮቱንም ችቦ ከፍ አድርጎ በመያዝ ፣ ሰላምና ፍትሕ የሚሰፍንባትን አዲሲቷን ፣ ጠንካራዋንና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመገንባት ለሚደ ረገው ጥረት የበኩሉን ድርሻና አስተዋጽኦ ለማድረግ ቃል ይገባል ።

የዩኒቨርሲቲው የሕግ መምህራንም ሆኑ የፍርድ ቤት ባልደረቦች ወይም በመ ንግሥት ሥራም ሆነ ከመንግሥት ሥራ ውጭ በልዩ ልዩ የሥራ ክፍል የተሠማሩ የሕግ ባለሙያዎች ሁሉ በመጽሔቱ ታትመው ሊወጡ የሚችሉ ጽሑፎችን በማበርከትና አስፈላጊ ምክርና ድጋፍ በመስጠት የመጽሔቱን ሕይወት ያለማቋረጥ እንደሚንከ ባከቡ እንተማመናለን ፤ ለዚሁም አብዮታዊ ጥሪ እናስተላልፍላቸዋለን ። አስፈላጊውን ጥረትና አስተዋፅኦ በማድረግ ይህ ከአብዮቱ ወዲህ የመጀመሪያ የሆነው የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት እትም እንዲወጣ ላስቻሉት ሁሉ ምስጋና እናቀርባለን ።

የአዘጋጅ ቦርድ

ከሕግ ፋኩልቲ የተሰጠ የ፲፱፻፸፩ እና የ፲፱፻፸፪ ዓ/ም

ራ ፖ ር ት

ፋሲል ናሆም ፤ ዲን

የሕግ ፋኩልቲ በዚህ የጎብረተሰብአዊ ለውጥ የተ ጨጨፈባት ወሳኝ አብዮታዊ ወቅት ብሔራዊ ፍላጎት ትን እንዲያሟላ ለማድረግ የተወጠነው ታላቅ ተግባር ከመቸውም ይበልጥ የተሰማበት ጊዜ ነው ። ይህንንም የምንልበት ምክንያት ከፊታችን የተደቀነውን አስቸ ጋሪው ተግባር ለመቋቋም ወደፊት የሚመጣው ጊዜ ከአለፈው የተሻለ የሥራ ውጤቶች ይኖሩታል የሚል ጽኑ እምነት ስላለን ነው ። የሕግ ፋኩልቲ በ፲፱፻፶፮ ዓ/ም መቋቋምና የኢትዮጵያ ሕጐች በመጽሐፍ (በኮድ) መውጣታቸው ወዲያውኑም ተከታትለው የመጡት አስር ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ በሕግ መስክ ተገቢ ለሆነ ትምህርትና ምርምር መሠረት ጥለዋል ። ምንም እንኳን በጊዜው በምሁራን አካባቢ የነበረው ሁኔታ ለመቅዳት ፣ ለማስተጋባትና ከቀድሞው ትምህርታዊ ወግ አልፎ እንዳይሄድ የታቀደ ለጥቂት ምርጥ ሊቃው ንት ብቻ የተዘጋጀና ቀለም የለሽ ፖለቲካ ሰፍኖበት የነበረ ሁኔታ ቢሆንም ፣ የሕግ ፋኩልቲ በኢትዮጵያ መሬት ላይ መቋቋምና ኢትዮጵያዊ ችግሮችን መመር መሩ በእርግጥ ከፍተኛ እድገት ነበር ማለት ይቻላል ። ሆኖም ብዛት ያላቸው የውጭ አገር መምህራን ወደአ ገራቸው በመመለሳቸውና ያሉትም ጥቂት ወጣት ኢትዮ ጵያውያን መምህራን ለከፍተኛ ትምህርት ወደውጭ በመ ሄዳቸውም ሆነ በከፍተኛ የመንግሥት ሥራዎች ላይ በመ ሳተፋቸው የሕግ ፋኩልቲው የተመኘውን ያህል በሙሉ ጉልበትና በከፍተኛ ደረጃ ሊያመርት አልቻለም ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ፤ የሕግ ፋኩልቲ ከአለበት ከፍ ተኛ የመምህራን እጥረት ገና ማገገም አለበት ፤ ከዛ ሬው ከጥቂት የመምህራን ቁጥር አልፎ በሚያስተማ ምን አኳኋን ሥራውን ማከናወን ይኖርበታል ። እነዚ ህን የትምህርት ዘመናት የጀመርነው መላውን የሕግ ፋኩልቲ ለማንቀሳቀስ ስድስት የሙሉ ቀን መምህራን እና አንድ የግማሽ ቀን መምህር ብቻ በመያዝ ነው ። በሌላው በኩል ፋኩልቲው በታሪኩ ውስጥ በነዚህ ሁለት ዓመታት ካለው የበለጠ የተማሪዎች ብዛት አጋ ጥሞት አያውቅም ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሚቻለው ሁሉ ለተማሪው ጥሩ የሕግ ትምህርት ለመስጠት ታቅደው የተደረጉት የሥርዓተ ትምህርት ለውጦች እነዚህን ዓመታት አጣዳፊና አስጨናቂ አድርገዋቸዋል ። ቢሆ ንም ወደፊት መጓዝ የሚቻለው በትግል ነውና ካከናወ ናቸው የሥራ ውጤቶች አንፃር ሲታይ ፋኩልቲው ላካ ሄደው ትግል በበቂ አኳኋን ተክሶአል ለማለት እንች ላለን ። ጎላ ብለው ከሚታዩት የሥራ ውጤቶች አንዳ ንዶቹን ከዚህ እንደሚከተለው መጥቀስ እንወዳለን ።

፩ኛ/ የሥርዓተ ትምህርት ዕድገት

ሀ/ ስለሥርዓተ ትምህርት ጥናት የተደረገ ስብሰባ ፤ በመንግሥት አስተዳደር የፖሊሲ አውጭ አካል ተሳታፊ በመሆን የሚያገለግል ፤ በሙያው ችሎታ ያለውና በፖለቲካ የታነጸ ምሩቅ ለማውጣት ለአ ያሌ ዓመታት በፋኩልቲው ሥርዓተ ትምህርት ላይ ሰፊ ሙከራ ሲደረግ ከቆየ በኋላ ስለሥርዓተ ትምህርት ጥናት ስብሰባ ተዘጋጀ ። ስብሰባው መም ህራን ፣ ምሩቃንና የመንግሥት ባለሥልጣኖች የተ ሳተፉበት ከሐምሌ ፮ እስከ ፰ ፲፱፻፸፩ ዓ/ም የተካ ሄደ የሦስት ተከታታይ ቀናት ሥራ ነበር ። የሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ተቀዳሚ የሰው ኃይል ፈላጊና ለፋኩልቲውም መጠናከር አሳቢ አካል እንደ መሆኑ ፣ በቋሚ ተጠሪው በሚመራ አራት ከፍ ተኛ ባለሥልጣኖች በሚገኙበት ቡድን ተወክሎ በስብሰባው ላይ ተገኝቶ ነበር ። በአብዛኞቹ ሚኒስ ቴሮችና የመንግሥት ድርጅቶች የሚገኙ ዋና የሕግ አማካሪዎችና እንደዚሁም የከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኞ ችና የቀበሌ ማኅበራት የፍርድ ሽንጎ አባላት በስ ብሰባው ተካፍለው ነበር ። በተጨማሪም የከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን ተወካይና የዩኒቨርሲቲው የአ ካዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት በሕግ ባለሙያነታ ቸውና በሥራቸው ምክንያት በስብሰባው ላይ ተካፍለው ነበር ።

ስብሰባው በነበረው ሥርዓተ ትምህርት ላይ በሰ ፊው ተነጋግሮ ጥልቀት ያላቸው ማሻሻያዎችና የፖ ሊሲ ውሳኔዎች ለመቅረጽ በመቻሉ የተሳካ ስብሰባ እንደነበር እዚህ ላይ ማስታወስ እወዳለሁ ። በእ ርግጥ እነዚህ ጠቃሚ ማሳሰቢያዎችና ማሻሻያዎች የሚያመለክቷቸው ሁኔታዎችና አፈጻጸማቸው በፋ ኩልቲው በጥንቃቄ የሚታዩና የሚቀናጁ የረጅም ጊዜ እቅዶች ናቸው ። (በእንግሊዝኛ ተጨማሪ ፩ና ተጨማሪ ፪ የተባሉትን ጽሑፎች ይመልከቱ ።)

ለ/ ሥርዓተ ትምህርት ፤ የሥርዓተ ትምህርቱ ስብሰባ ባቀረበው ሐሳብና በፋኩልቲውም በተካሄዱት ውይይቶች ላይ የተመሠረተ ከ፲፱፻፸፪ ዓ/ም የት ምህርት ዘመን ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለው አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ተዘጋጅቶአል ። በእርግጥ

የሥርዓተ ትምህርት መሻሻል የማያቋርጥ ሂደት ነው ። ሥርዓተ ትምህርቱ በየጊዜው እንደገና እንዲታይና ወቅታዊ መልክ እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል ።

ፔኛ/ ምርምር ማድረግና ጽሑፎችን ማውጣት ፤

ምርምር የማድረግና ጽሑፎችን የማውጣት ሥራ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ለማስተማር በጣም አስፈላጊ ነገሮች መሆናቸውን ፋኩልቲው ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ተገንዝቧል ። እንደሕግ ፋኩልቲ በመሰለ የሙያ ትምህርት ቤት ምርምር ማድረግና የምርምር ውጤት የሆኑ ጽሑፎችን ማውጣት እንዲያውም የበለጠ ተፈላጊነት ይኖራቸዋል ። ምንም እንኳን ያለው ከፍተኛ የመምህራን እጥረት ባለፉት አያሌ ዓመታት ውስጥ ምርምር የማድረግንና ጽሑፎችን የማውጣትን ሥራ አዳጋች አድርጎት የነበረ ቢሆንም ፤ ፋኩልቲው በአሁኑ ሰዓት በእነዚህ አካባቢም ድፍረት ያለው እርምጃ መደረግ እንዳለበት ወስኗል ።

ሀ/ የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት ፤ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ዓላማ ፋኩልቲው የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት እንደገና እንዲያንሰራራ አድርጓል ። የአዘጋጅዎች ቡድን ተሰይሟል ። የሕግ አዋቂዎች ጽሑፎችና አስተያየቶች ተጠይቀዋል ፤ የአዘጋጂዎች ቦርድም ተቋቁሟል ። መጽሔቱ አግባብ ላለው የሕግ ምርምር መድረክ ብቻ ሳይሆን ፤ በአገሪቱ ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሕግ ሙያ የተሰማሩ ሊቃውንት የሚገናኙበት ማዕከላዊ ዘዴም በመሆኑ ተፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው እንላለን ። ከዚህም በላይ ይህ መጽሔት የአብዮታዊት ኢትዮጵያን ህብረተሰብአዊ እርምጃዎች በትክክል የሚያንጸባርቅ እንዲሆንና ጠለቅ ያሉ አከራካሪ የሕግ ጭብጦችን የሚፈታና ከፍተኛ የሕግ ዕውቀት የሚያሰራጭ መሆን ይኖርበታል ። ስለዚህም የመጽሔቱ አዘጋጆች ቦርድ አባላት ከሕግ ምሁራን ፤ ከፍተኛ ዳኞችና የመንግሥት ባለሥልጣኖች ተመርጠው እንዲገቡበት ተደርጓል ። የዚህም መላው የሕግ ባለሙያዎች ቡድን ቅንብር የተደረገው ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው የሕግ አዋቂዎችንና የፖለቲካ ብስለት ያላቸው ግለሰቦችን በመሰብሰብ የመጽሔቱን ጥራት ለማረጋገጥ ታስቦ ነው ። ይህ ራዕር ወይም መግለጫ በሚጸፍበት ጊዜ የመጽሔቱ የመጀመሪያው ክፍል ወደ ማተሚያ ቤት በመላክ ላይ ነው ። እዚህ ላይ የዩኒቨርሲቲ አስተዳደር በመጽሔቱ ማንሰራራት ላሳየው የጋለ ድጋፍና ማበረታቻ የፋኩልቲውን ምስጋና መቀበል ይገባኛል ።

ለ/ የኢትዮጵያ የተጠቃለሉ ሕጎች ፤ ሌላው ፋኩልቲው እንዲያንሰራራ የወሰነው ምርምር የማድረግና ጽሑፍ የማውጣት ሥራ የተጠቃለሉ የኢትዮጵያ ሕጎችን ነው ። የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜ ያዊ ወታደራዊ መንግሥት ያወጣቸው አዳዲስ ሕጎች ገና መጠቃለል ይኖርባቸዋል ። ሥራው ለብዙ የመንግሥትና የሕዝብ ተቋሞች እጅግ አስፈላጊ ነው ። ለዚህም እጅግ ጠቃሚ ሥራ ችሎታ ያላቸው አዘጋጂዎች ተመርጠው ሥራውን በማካሄድ ላይ ይገኛሉ ።

ሐ/ የፋኩልቲና የግል ምርምር ፤ የፋኩልቲው አባላት ከማስተማር ፣ ፋኩልቲ አቀፍና የኒቨርስቲ አቀፍ በሆኑ የአስተዳደር ሥራዎች ውስጥ ከመሳተፉ በላይ በተጨማሪ ፣ የፋኩልቲና የግል ምርምር ውጥኖች በማካሄድ የመጀመሪያ ፍሬአቸው የሆነውን ይህን የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት እትም ለማውጣት በቅቷል ።

ፎኛ/ የውጭ ግንኙነቶች ፤

የትኛውም ፋኩልቲ ቢሆን ራሱን የቻለ ለብቻው የቆመ ደሴት አይደለም ። በተለይም በሙያ ትምህርት ቤት ውስጥ ከፋኩልቲው ውጭ ካሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ያለማቋረጥ ግንኙነት የማድረጉ አስፈላጊነት ምንም የማያጠያይቅ ጉዳይ ነው ። የሕግ ፋኩልቲ በነዚህ ዓመታት ከሌሎች ድርጅቶችና የትምህርት ተቋሞች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ሞክሯል ።

ሀ/ ዩኒቨርስቲ አቀፍ ትብብር ፤ በማስተማሩ ደረጃ ከሁለት የሶሻያሊስት ዩኒቨርስቲዎች ማለትም ፣ በፖላንድ ከሚገኘው ከዋርሶው ዩኒቨርስቲና በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ከሚገኘው ከላይፕዚግ ካርል ማርክስ ዩኒቨርስቲ ጋር ጥሩ ግንኙነት ጀምረናል ። ከዚህም ግንኙነታችን የተነሳ ፣ ከዋርሶው የሕግና የአስተዳደር ትምህርት ቤት ሁለት ረዳት ፕሮፌሰሮች በሁለት ዓመት ውል አስመጥተናል ። በተጨማሪም ከካርል ማርክስ ዩኒቨርስቲ በ፲፱፻፸፭ ዓ/ም ለአምስት ሳምንታት የመጡ አንድ ፕሮፌሰር አግኝተናል ። ጀርመናዊው ፕሮፌሰር በፋኩልቲው ውስጥ ከሰጡት ትምህርት በተጨማሪ ቁጥራቸው ከአንድ ሺህ አምስት መቶ በላይ ለሆኑ የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ስለሶሺያሊስት ሕገ መንግሥቶች የተሟሉ ትምህርታዊ ገለጻ አድርገዋል ። በውጭ ግንኙነት መምህራንን ፣ ተማሪዎችንና ጽሑፎችን በመለዋወጥ ይህን የመሰለውን ትብብር ይበልጥ ፍሬያማ ለማድረግ ይህ የመጀመሪያ ሙከራ ብቻ ነው ።

ለ/ ከመንግሥት ተቋሞች ጋር ትብብር ፤ ከቀድሞ የፋኩልቲው ተማሪዎችና ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር ያለንን ግንኙነት በሚመለከት ረገድ ፤ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው የሥርዓተ ትምህርት ስብሰባና የኢትዮጵያ የግል መጽሔት ዓይነተኛና ጠቃሚ ግንኙነት ለመፍጠር አመች መሣሪያ ሆኖአል ። ስለዚህም ነው የጠቅላይ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች ለማስተማሪያና ለምርምር ሥራ የሚያገለግሉ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን አቀናጅተው ለፋኩልቲው ለመስጠት ቃል የገቡልን ።

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚሠሩ የሕግ ባለ ሙዎችም ስለፋኩልቲያችን ያላቸውን በጎ ፈቃድ በማሳየት የፋኩልቲውን የማስተማርና የምርምር ጥራት በከፍተኛ ደረጃ ለማራመድ የሚያስችል የሕግ ጽሑፍ (ማቴሪያል) ሊያቀርቡልን ቃል ገብ ተዋል ።

፩ኛ/ የመምህራን ምልመላ ፤

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የመምህራን እጥረት ዋነኛው ችግራችን ሆኖ ቆይቷል ። ችግሩን ለማ ቃለል አያሌ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ እን ገኛለን ። (፩) በጊዜያዊ መልክ ችግራችንን ለመ ፍታት አንዱ ፈጣን መንገድ ብቁ ከሆኑና ከፍተኛ ችሎታ ካላቸው የመንግሥት ሹማምንትና ኤክስ ፐርት መካከል ላስተማሪነት በትርፍ ሰዓት መቅ ጠር ነበር ። ሆኖም እነዚህ ሹማምንትና ኤክስፐርት በመደበኛ ኃላፊነታቸው ሥራ የሚበዛባቸው ግለ ሰቦች በመሆናቸው ይህ በእርግጥ ዘላቂ መፍትሔ ነው ለማለት አልተቻለም ። ፍጹም አስፈላጊ እስከ ሆነ ድረስ በከፊል ጊዜ መምህራን መጠቀማችንን እንቀጥላለን ። በተለይ በከፍተኛ ደረጃ ጠለቅ ያለ እውቀት በሚጠይቁ አካባቢዎች ችሎታ ያላቸው መምህራን የሌሉን ስለሆነ በከፊል ጊዜ መምህራን በመጠቀም ከችግሩ መውጫ አንዱ መንገድ ሆኖ አግኝተነዋል ። (፪) የውጭ አገር መምህራንን መቅ ጠሩ ችግሩን ለማቃለል የሚረዳ ሌላው መንገድ ነው ። የውጭ አገር የሕግ መምህራን በተለይም ከደረጃ የሶሺያሊስት አገሮችና ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች የሚመጡት መምህራን ይበልጥ ተቀባይ ነት ይኖራቸዋል ። (፫) ሆኖም የመምህራንን እጥ ረት ለመፍታት ዋናው መንገድ ብቁ የሆኑና ከፍ ተኛ ችሎታ ያላቸውን ኢትዮጵያውያን የሕግ ምሑ ራን ማፍራት ብቻ ይሆናል ። አስተማሪነት የዕ ድሜ ልክ ሥራ እንደመሆኑ ሕግም ከጎበረተሰቡ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ያለጥርጥር የተሳሰረ ነው ። ስለዚህም ነው የፋኩልቲውን የመምህራን እጥረት ለማስወገድ በመጨረሻው አማራጭ ማለት በኢትዮጵያውያን መምህራን እንድንጠቀም እነ ዚህ ሁለት ሁኔታዎች በተጨማሪነት የሚያስገ ድዱን ። ይህን መሠረት በማድረግ አንዳንድ እር ምጃዎች በመወሰድ ላይ ናቸው ። ሦስት አዲስ መምህራን ተቀጥረዋል ፤ እንዲሁም ሁለት መም ህራን በውጭ አገር ከፍተኛ ትምህርታቸውን ሲከ ታተሉ ቆይተው ተመልሰዋል ። ስለዚህ መምህ ራንን መመልመል በሚመለከት ረገድ የፋኩልቲ ውን በትክክለኛ አቅጣጫ መጓዝ ስገልጽ በሥራ መሚላትና በእፎይታ ስሜት ነው ። በእርግጥ ያሉን መምህራን ወጣትና መጠነኛ የሆነ የሥራ ልምድ ያላቸው ናቸው ። እነዚህን የበሰሉ ባለሙያ ማድረጉ ምርምርና ተጨማሪ የማሰልጠኛ ዕድሎች የሚያስፈልጉበት የረጅም ጊዜ ሂደት ነው ። አያሌ የፋኩልቲ አባላት ሶቭየት ሕብረትንና የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክን የጎበኙባቸው ባለፉት ሁለት የክረምት ወራቶችና በዚህም ክረምት ተሳ ትፈው እንደነበሩት ዓይነት የአጭር ጊዜ የክረምት ስብሰባዎች ተቀባይነት አላቸው ። ነገር ግን የመ ጨረሻውን ከፍተኛ ውጤት ማግኘት ይቻል ዘንድ በተገቢ ድርጅቶች ውስጥ ለምርምርና ለመሰል ጠን ይበልጥ ሰፋ ላለና ረዘም ላለ ጊዜ ለመጋለጥ መታቀድ ይኖርበታል ። በተጨማሪም መመለሳ ቸውን በጉጉት የምንጠባበቀው ከፍተኛ ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኙ አያሌ መምህራን እን ዳሉን መግለጽ ይገባኛል ።

፪ኛ/ የዲግሪ ተማሪዎች ስታትስቲክስ ፤

በ፲፱፻፸፩-፸፪ ዓ/ም የትምህርት ዘመናት ፋኩል ቲው ከመቼውም ጊዜ ቁጥራቸው የበዛ ተማሪዎች መዝግቦ በማስተማር ላይ ይገኛል ። የሕግን ሙያ ለሴቶች በመክፈት ቁጥራቸው በመጠኑም ቢሆን በዛ ያለ የሴት ተማሪዎችን የመቀበል ጤናማ ዝን ባሌ በተጨማሪ ተጀምሯል ። እውነቱን ለመናገር ከዚህ በፊት የነበሩት ዓመታት ሁሉ ተደምረው ከነበረው የሴት ተማሪዎች ቁጥር የሚበልጡ የሴት ተማሪዎች በነዚህ ሁለት ዓመታት ተቀብለናል ። ቢሆንም የሴት ተማሪዎች ቁጥር አሁንም ቢሆን ከአጠቃላይ አሥር በመቶ የሚበልጥ አይደለም ። በነዚህ ሁለት ዓመታት በፋኩልቲው ተመዝግበው ትምህርታቸውን የሚከታተሉት ተማሪዎች እንደ ዓመታቸው ሲከፋፈሉ እንደሚከተለው ይሆናሉ ።

	፲፱፻፸፭ ዓ/ም		፲፱፻፸፮ዓ/ም	
የሕግ ትምህርት ጀማሪዎች	፭፻	ተማሪ	፹፭	ተማሪ
የሕግ ትምህርት ፩ኛ ዓመት	፳፯	”	፹፯	”
” ” ፪ኛ	፵፯	”	፷	”
” ” ፫ኛ	፳፯	”	፵፫	”
” ” ፬ኛ	፳፫	”	፲፬	”
የማታ የሕግ ባችለር ዲግሪ	፳	”	፳፪	”

ከእነዚህ ውስጥ ፵ የ፬ኛ ዓመት የሕግ ተማሪዎችና ቀደምትነት ያላቸው የ፫ኛ ዓመት የሕግ ተማሪዎች በ፲፱፻፸፭ ዓ/ም በዲግሪ ሲመረቁ ፤ በ፲፱፻፸፮ ዓ/ም ደግሞ ፫፭ የ፬ኛ ዓመት የሕግ ተማሪዎች የ፫ኛ ዓመት የሕግ ተማሪዎችና የማታ የዲግሪ የሕግ ተማ ሪዎች ይመረቃሉ ።

፫ኛ/ የሕግ ትምህርት ፕሮግራሞች ፤

ከዚህ በፊት ፋኩልቲው በሕግ የባችለር ዲግ ሪን ፣ በሕግ ዲፕሎማና ሰርቲፊኬትን ጨምሮ በተ ለያዩ የሕግ ትምህርት ፕሮግራሞች ደረጃዎች ሙከራ አድርጓል ። በአሁኑ ወቅት ከሚሰጠው መደበኛ የቀን በሕግ የባችለር ዲግሪ ፕሮግራም የፋኩልቲው ተጨማሪ ፕሮግራም እንደሚከተ ለው ነው ፤

ሀ/ በሕግ የዲፕሎማ ፕሮግራም ፤ ከብዙ የመንግሥት ድርጅቶች ጋር ምክክር ከተደረገ በኋላ በ፲፱፻፸፭

የትምህርት ዘመን በሥራ ላይ የዋለ የሁለት ዓመት የሕግ የዲፕሎማ ፕሮግራም በ፩፱ ተማሪዎች ተጀምሯል ። የማስተማሪያው ቋንቋ አማርኛ የሆነው ይህ ፕሮግራም በመንግሥት ድርጅቶች ውስጥ የሚያገለግሉ መለስተኛ የሕግ ባለሙያዎችን ጥራት ለመጨመር በማሰብ የታቀደ ነው ። ፕሮግራሙ ለጊዜው በአዲስ አበባ ብቻ ቢሰጥም ፥ ሁኔታዎች እስከፈቀዱ ድረስ በሌሎች ስፍራዎች ወደፊት ሊሰጥ የማይችልበት ምንም ምክንያት አይኖርም ።

ለ/ <u>ሌሎች ፕሮግራሞች ፤</u> ፋኩልቲው በበቂ ሁኔታ ተሟልቶ የማታውን በሕግ የባችለር ዲግሪ ፕሮግራም መቀጠል ያለበት ይመስላል ። እንዲሁም የኤል ኤል ኤም ሁለተኛ የሕግ ዲግሪ የሚያሰጥ ፕሮግራም ለመክፈት ማሰብ ይኖርበታል ። በሌላ በኩል ደግሞ አጫጭር በተለይ ለሕዝባዊ ድርጅቶች የፍርድ ሸንጎዎችና ለመሳሰሉት የሚዘጋጁት ፕሮግራሞች ላይ ማተኮር ይኖርበታል ። ሆኖም እነዚህ ሁሉ የሚቀጥለው የትምህርት ዘመን ጉዳዮች ናቸው ።

፯ኛ/ <u>የወደፊቱን ሁኔታ ስንመለከት ፤</u>

ፋኩልቲው የዛሬይቱና የነገይቱ ኢትዮጵያ የምትፈልገውን በሕግ ሙያ የሰለጠነ የሰው ኃይል የማፍራት ኃላፊነቱን ሙሉ በሙሉ ተገንዝቧል ። እንደሚታወቀው ሁሉ ትምህርት በአንድ ዓይነት ፕሮግራምም ሆነ በክፍል ትምህርት የተወሰነ አይደለም ። በፈጣን ለውጥ ላይ በሚገኝ ሕብረተሰብ ውስጥ በሕግና በፍትሕ ላይ ምርምርና ትምህርት ለማካሄድ ልዩ ትኩረት መስጠት ምንም እንኳን መንፈስን የሚቀሰቀስና የሚያረካ ቢሆንም ፥ በተግባር ለመተርጎም የዚያኑ ያህል አስቸጋሪ ነው ። የመጨረሻ ዓላማው ፍትሕ ፥ ማለትም ማኅበራዊ ፍትሕ የሆነው የኢትዮጵያ አብዮት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ፋኩልቲ ጥረቶች አርማና መሪ ኮከብ ነው ።

ፋኩልቲው ወደፊት የሚያጋጥሙትን ማናቸውንም ችግሮች እንደሚወጣና ፥ ፍትሕን ለማግኘት በሚያደርገው የወደፊት ግስጋሴና ትግል ውስጥ ተካፋይ ሆነው የሚያገለግሉ የሕግ ሰዎችን ማፍራያ መሆኑን እንደሚቀጥል ተስፋ በማድረግ በልበ ሙሉነት ወደፊት ይመለከታል ።

የኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት

ሮማዊ መሠረቶች*

በፒተር ኤች ሳንድ**

በኢትዮጵያ ሕግና በአውሮፓ ሕግ ፥ በተለይ በሮማውያን ሕግ ፤ መሐከል ያለው ዝምድና ብዙ ጊዜ የተነሳ ሲሆን ፥ በይበልጥ የኢትዮጵያን የ፲፱፻፷ የፍትሐ ብሔር ሕግ ባረቀቁት በፕሮፌሰር ረኔ ዳቪድ የኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት ሮማዊ ምንጭ ተለይቶ ተጠቅሶ አል ።[1]*** በሮማዊው ንጉሠ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት የተደረጉ ሙከራዎች ቢኖሩም ቅሉ እስከምናውቀው ድረስ ከሆነ ግን በሮምና በኢትዮጵያ ነገሥታት መሐከል የነበረው ቀጥተኛ ግንኙነት በጣም የተቀራረበ ሆኖ አያውቅም[2] ። ይህ የተባለው ዝምድና መኖሩ ሳይረጋገጥ ይህን ድብስብስ የሆነ ዝምድና መነሻ በማድረግ ፥ ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ሕግ ማርቀቅ አስገራሚ ይሆናል ። ይህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ጥንታዊ ሕግና በሮማ ጥንታዊ ሕግ መሐከል ያለውን እውነተኛ መተሳሰር ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራ ነው ።

፩ ጽሑፎች ፤

የሕግ ታሪክ በማነጻጸር በሚደረግ ዓለም አቀፍ ጥናት ኢትዮጵያ አሁንም ቢሆን የታወቀች አገር አይደለችም ።[3] ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የቋንቋ ገደብ ሲሆን ለሕግ ንጽጽር ጥናት በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍትን መረዳት አይቻልም ነበር ። የዓለም አቀፍ ምሁራን የግዕዝ ቋንቋ ዕውቀት ስለአልነበራቸው የሕግ ንጽጽር ጥናት ለማድረግ በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍትን መመርመር አልቻሉም ። በአንጻሩም ሊቃውንቱ የላቲን ቋንቋ ያውቁ ስለነበር ሮማዊ መጻሕፍትን ለመመርመር ተመሳሳይ ችግር አልገጠማቸውም ።

ግምቶች

ስለዚህ ቨርማንና ዌግሞር ከሃምሳ ዓመት በፊት የአሁኑ የሐበሻ ሕግ በጀስቲንያን ሮማዊ ሕግ ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ጥንታዊ ፍዳም ሮማዊነቱን[4] አጥቶም ከሮማንይስክ ዓይነት (Romanseque type)[5] ውስጥ የሚውል ስለመሆኑ ስላተቱት ጉዳይ ማስረጃ ሊያቀርቡ አይችሉም ። ምናልባትም የዚህ ግምታቸው መሠረት የሆነው አንዳንድ የውጭ መንገደኞች በ፲፱ኛው ምዕተ ዓመት ለአንድ የአልታወቀ ፍትሐ ነገሥት የሚል የግዕዝ መጽሐፍ "የጀስቲንያን ኮድ ኢትዮጵያዊ ትርጉም"[6] የሚል መግለጫ የሰጡት ይሆናል ። የእንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናዊ የሆነው ጐባት ይህ እምነት ሐበሾች የመጽሐፉን ደራሲነት "ከጀስቲንያን ይልቅ ለቆስጠንጢኖስ"[7] ይሰጡታል ካለው ሳይመነጭ አይቀርም ። ከዚህ በኋላ የተነሱት ጸሐፊዎች ፍትሐ ነገሥት የሙሴን መጻሕፍትና የወንጌልን ትዕዛዛት ከጀስቲንያን ሕግ ጥቂት ክፍሎች ከሞላ ጎደል በማሚላት[8] "ወይም" የሙሴን የጥንት ጽሑፍ ፥ ደራሲዎቻቸው ካልታወቁ መጻሕፍት (apocrypus) እና ከሐዋርያቶች ጉባኤ (ሲኖዶስ) እንዲሁም ከቲዎዶሲያስና ከጀስቲንያን ሕግጋት[9] አጠናቅረዋል የሚል አስተያየት ጨምረዋል ።

ያልታተሙ ጽሑፎች

ኢዝንበርግ በ፲፰፻፴፯[10] የፍትሐ ነገሥትን ቅጅ ወደ ለንደን ከላከ በኋላ ብሩስ በ፲፯፻፹፬ ከወሰዳቸው ጽሑፎች መሐከል የተሳሳተ መግለጫ የሰጠበትና ቀደም ሲል የተዘጋጀ ያልታተመ ጽሑፍ እንደ ነበረ ደልማን አግኝቷል[11] ። ሮሸር ደ ኸርኩርት ደግሞ ከሸዋ ንጉሥ ለፈረንሳይ ንጉሥ በገጸ በረከትነት የተላከውን የዚህን "የተከበረ መጽሐፍ" ቅጅ ፓሪስ አምጥቷል ።[12] ሩፔልም በአንድ ያልታተመ ጽሑፍና ከኢትዮጵያዊው ምሁር ከሊቅ አትክሚ[13] በግል ባገኘው መረጃ በመመርኮዝ የጽሑፉን ማውጫ አጭር መግለጫ በ፲፰፻፴ አሳትሟል ። በሩቅ ምሥራቅ ትምህርት የታወቀው ቮን ኤዋልድ ደግሞ በሚስዮናዊው ክራፍ አማካይነት አንድ ሌላ ያልታተመ ጽሑፍ አግኝቶ በ፲፰፻፴፯ መዝግቧል ።[14]

በሉርድ ናፒር የ፲፰፻፷፰ ወታደራዊ ዘመቻ የእንግሊዝ ሠራዊት አጼ ቴዎድሮስን ድል መትቶ የመቅደላን ቤተ መንግሥት ግምጃ ቤት ከዘረፈ በኋላ በርከት ያሉ ያልታተሙ ጽሑፎች ተገኝተዋል ። የእንግሊዝ ሙዚየም (ቤተ መዘክር) ባልደረባ ሪቻርድ ሆልምስ በከፍተኛ ተጫራችነት በተካፈለበት የተዘረፈው ጽሑፍ በቦታው በጨረታ ተሸጧል ።[15] ራይት የተባለው በ፲፰፻፸፯ ባወጣው የመጻሕፍት ዝርዝር በሙዚየሙ ውስጥ የነበሩ ከአሥራ አንድ ያላነሱ የፍትሐ ነገሥት ያልታተሙ ግልባጮች መዝግቧል ።[16] በአውሮፓ ቤተ መጽሐፍት የተረጋገጡ ሃያ የፍትሐ ነገሥቱ ያልታተሙ

---

* በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት ቀኖች በሙሉ እ ኤ አ ዓ/ም ናቸው ። ወደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ለመለወጥ ሰባት ወይም ስምንት ዓመት በመቀነስ ሊሰላ ይችላል ።

** ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ መምህር የነበሩ ሲሆን አሁን በዓለም የምግብ ድርጅት ይሠራሉ ።

*** የጽሑፉ ግርጌ ማስታወሻ በዚህ ትርጉም ያልተገለበጠ ስለሆነ የዚህን ጽሑፍ የእንግሊዝኛ ቅጂ በመመልከት ማገናዘብ ይቻላል ።

ጽሑፎች እንደሚገኙ ኮንቲ ሮሲኒ መዝግቧል ።[17] በ፲፱፻፲ ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ ሃያ አራት ይገኙ ነበር ።[18] ዛሬ በአውሮፓ ቤተ መጻሕፍት የሚገኙት ቁጥር ወደ ፴ የሚጠጋ ሲሆን (በእርግዋ ግራቪን ከሚለው ከአምስት በላይ[19]) በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት የሚገኙ ያልተመዘገቡ የእጅ ጽሑፎች ቁጥር ከመቶ በላይ እንደሚሆን በሚያስተማምን ሁኔታ ሊገመት ይችላል ።[20]

የታተሙ ጽሑፎች

ተከታዩም አቢይ የጽሑፍ ምርምር ቢሆን በአጋጣሚ በወታደራዊ እንቅስቃሴ ምክንያት የተጀመረ ነው ። በ፲፰፻፺ ኢትዮጵያን ለመያዝ ለነበረው መሰናዶ አካል በማድረግና ለቅኝ ግዛታዊ የዳኝነት ሥራ አካሄድ መግ ልገያ እንዲሆን ፍትሐ ነገሥትን አስተካክሎ እንዲተረ ጎም የኢጣሊያ የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር በሩቅ ምሥ ራቅ ትምህርት የታወቀውን ኢኖዚየ ጉዊደን ሰየመ ። የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት በ፲፰፻፺፯ በአጼ ምኒሊክ ድል ከ ተመታ በኋላ በግዕዝ ቋንቋ የተዘጋጀው የፍትሐ ነገሥት ግልባጭ ቀደም ሲል እንደታተደው ጊዜውን ከሞላ ጎደል ሳያዛንፍ በ፲፰፻፺፯ ታትሞ ወጣ ። እንዲሁም የኢ ጣሊያንኛው ትርጉም በ፲፰፻፺፱ ተከታትሎ ታተመ ።[21] ይህም ቀደም ሲል በአንድ ፈረንሳይ ቤተ መጽሐፍት የመጽሐፍ ዝርዝር[22] በቁንጽል ከታተመው በስተቀር በወቅቱ ከነበሩት የእጅ ጽሑፎች መሐከል ምርጥ የሆ ኑትን ለሰባት ዓመታት እጅግ አድካሚ በሆነ መንገድ በማነጻጸር በኢትዮጵያዊው ምሁር በክፍለ ጊዮርጊስ እርዳታ ጭምር የተዘጋጀ የመጀመሪያው የታተመ ግል ባጭ ነው ። ይህ እትም እስካሁን ከተዘጋጁት ትክክ ለኛ ነው ተብሎ የታመነበት ሲሆን ፤ ትክክለኛ ነው ተብሎ የታመነበት በመሆኑም ፤ በ፲፱፻፴ የወጣው የመ ጀመሪያው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቆጫ ሕግ ፍትሐ ነገሥቱን ሲጠቅስ የጉዊዱን ጽሑፍ ገጽ በገጽ በማመ ልከት ተጠቅሞበታል ።[23] "ኦፊሲያላዊ" የአማርኛ ግልባጭ መታተም በ፲፱፻፴፩ አዲስ አበባ ተጀምሮ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መሐከል በነበረው ጦርነት ከተቋረጠ በኋላ በመጨረሻ በ፲፱፻፵፮ ተጠናቋል ።[24]

ትርጉም

የፍትሐ ነገሥቱ ቁንጽል የላቲን ትርጉሞች በአርኖ ልድ (፲፰፻፴፭) እና በችማን (፲፰፻፺፱) ታትመዋል ።[25] የኢጣሊያንኛ እትም ቀደም ሲል በደስቲፋኖ በ፲፰፻ ፺፩-፺፯[26] የተዘጋጀ ሲሆን ይህም ቀደም ሲል የተዘጋ ጀው ትርጉም ሬይን (፲፱፻፳) በአጭሩ ላዘጋጀው የጀር መንኛ ትርጉሙ መሠረት ሆኖታል ።[27] ሆኖም ከሁ ሉም የጉዊዲ ትርጉም በይበልጥ የሚያስተማምን ነው ። ይህትርጉም ደ ካስትሮ (፲፱፻፲፱) ፤ ማውሮ ዳ ሲዎኔሳ (፲፱፻፴፭) እና ሮስካነቮሬ (፲፱፻፴፱)[28] በተከታታይ ባዘ ጋጅዋቸው የኢጣሊያንኛ ትርጉሞች በይበልጥ የተጠ ቀሙበት ሲሆን በጳውሎስ ዘ ጳድዋ ተተርጉሞ በስትራ ውስ በ፲፱፻፻፳፰[29] ለተዘጋጀው የመጨረሻ የእንግሊዝኛ እትም ዋና መሠረት ሆኗል ።

ይዘት

በከፊል ለንጽጽር ከሚያገለግሉት (አንቀጽ ፲፰ ምዕራፍ ፪ ጉልት) (Charitable Legacies)[30] በስ ተቀር የፍትሐ ነገሥቱ የመጀመሪያ ክፍል (አንቀጽ ፩-፳፪) መንፈሳዊ ሕግን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ብቻ ይይዛል ። ሁለተኛው ክፍል (ፍትሐ ሥጋዊ-አንቀጽ ፳፫-፺፩) እና አባሪው ግን ስለሚከተሉት ያወሳሉ ።[31] ፳፫ ፤ ምግብ ፥ ልብስ ፥ የመኖሪያ ሥፍራና ለክርስቲያ ኖች ተገቢ ስለሆነው መተዳደሪያ (ሥራ) ። ፳፬ ፤ መተ ጫጨት ፥ ጥሎሽ ፥ ጋብቻና የጋብቻ መፍረስ ፳፭ ፤ ዕቁ ባት ማኖር እንደማይገባ ። ፳፮ ፤ ስጦታ ። ፳፯ ፤ ብድር ፥ መያዣና ዋስትና ። ፳፰ ፤ ለጥቅም (ለአገልግሎት) ስለ ሚሰጥ ብድር ። ፳፱ ፤ አደራ ። ፴ ፤ ምግብና ፴፩ ፤ ባር ነትና ባርያን ነፃ ማውጣት ። ፴፪ ፤ ሞግዚትነት ፴፫ ፤ መሸጥ ፥ መግዛትና ተመሳሳይ ጉዳዮች ። ፴፬ ፤ ሽርክና (ተሳትፎ) ፴፭ ፤ በኃይል ማስገደድ ። ፴፮ ፤ ኪራይ ። ፴፯ ፤ ሕንፃ ፥ መንገድና ውኃ ። ፴፰ ፤ የንግድ ሥራዎች ። ፴፱ ፤ ብድርን (ዕዳን) ማመን ። ፵ ፤ የጠፉና ባለቤት የሌላ ቸው ዕቃዎች (ቁሳቁስ) ፵፩ ፤ ኑዛዜ ። ፵፪ ፤ ውርስ ። ፵፫ ፤ ዳኝነትና የዳኝነት ሥርዓት ። ፵፬ ፤ የንጉሥ መብትና ግዴታ ።፵፭ ፤ የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን የተለያዩ ድንጋጌዎች ። ፵፮ ፤ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ የማ ንሳት ፥ የክህደትና የአስማት ወንጀል ቅጣት ድንጋ ጌዎች ። ፵፰ ፤ የዝሙት ወንጀል የቅጣት ድንጋጌዎች ። ፵፱ ፤ የሌብነት ወንጀል የቅጣት ድንጋጌዎች ። ፶ ፤ የስ ካር ፥ አራጣ እና የተለያዩ ወንጀሎች የቅጣት ድንጋጌ ዎች ። ፶፩ ፤ ውርስ ፥ ግዝረት ፥ ኑዛዜና የካህናት ሕግ የማውጣት ሥልጣን የቤተ ክርስቲያን ደንቦች ። አባሪ ስለውርስ ።

፪ ፤ ምንጮች ።

ፍትሐ ነገሥት በአገር ውስጥ መሠረት የሌለው መሆኑ በአማርኛ አፈ ታሪክ የባህር ሕግ ማለትም "ከባ ሕር ማዶ የመጣ ሕግ" ተብሎ በመጠራቱ ይታወቃል።[32] በአንድ በሕዝብ ዘንድ በታወቀ አፈ ታሪክ የሕግ መጽ ሐፍ (በሮማ ንጉሠ ነገሥት) ቆስጠንጢኖስ[33] ዘመነ መንግሥት ከሰማይ እንደወረደ ሲነገር ሌሎች ደግሞ ሠለስቱ ምዕት እንዳወጡት ይናገራሉ ። የፍትሐ ነገ ሥቱ የግዕዝ መቅድም በኒቂያ ጉባኤ (፫፻፳፭ ዓ/ም) ተሰ ብስበው የነበሩት ፫፻፲፰ የኦርቶዶክስ ጳጳሳት በንጉሠ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ ጥያቄ የሕግ መጽሐፉን እንዳ ዘጋጁ በግልጽ የሚናገር ሲሆን የሁለቱም አፈ ታሪኮች ምንጭ የዚሁ የስሚ ስሚ ቅጅ ነው ።[34] በ፲፱፻፳፭ የአ ማርኛ እትም እንደተገለጸው ሲወርድ ሲዋረድ በመ ጣው ታሪክ ኢትዮጵያዊው ንጉሠ ነገሥት ዘርዓ ያዕ ቆብ (፲፬፻፸፬-፲፬፻፷፭) መጽሐፉን ከግብጽ አስመጥቶ ወደ ግዕዝ[35] ቋንቋ እንዳስተረጎመው ይነገራል ።[36] ፍትሐ ነገሥቱን ወደ ግዕዝ የተረጎመው ሰው ግብ ፃዊው ክርስቲያን ኢብን አል አሳል ባጠናቀረው የአ ረብኛው ጽሑፍ መጠቀሙ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባህል ተጠቅሶአል ።[36]

የኮፕት የሕግ መጻሕፍ (Coptic Nmocanon)

እንግዲህ ያለቦታቸው የተጠቀሱት አንዳንድ ግልጽ ስህተቶች ከተወገዱ የፍትሐ ነገሥት የቅርብ ምንጭ በቂ በሆነ የታሪክ ማረጋገጫ ሊታወቅ ይችላል ። ከመ ቅድሙ የመጀመሪያ ክፍልና ከአባሪው[37] በስተቀር መጽሐፉ በመጀመሪያ በአረብኛ ከተጻፈውና ከዝነኛው የኮፕት "የሕግ መጽሐፍ" ቃል በቃል የተተረጎመ ነው ።[38] የዚህም መጽሐፍ ሠላሳ የሚሆኑ የታመኑ ያልታተሙ ጽሑፎች በአውሮፓና በግብጽ ቤተ መጻሕፍት ሲገኙ ሁለት እትሞች በ፲፱፻፩ እና በ፲፱፻፳፯ ወጥተዋል ።[39] የዚህ የሕግ መጽሐፍ ደራሲ የፍትሐ ነገሥቱ መግቢያ እንደሚያመለክተው በቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት አልነበረም ። የኮፕት ሥነ ጽሑፍ በገነነበት በ፲፫ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ክፍል ይኖር የነበረ ፣ የኮፕት ክርስቲያን ሊቅ የሆነ አስ-ሳፍ-ኢብን-አል-አሳል ነው ። እርሱም ለሰባ አምስተኛው የእስክንድርያ ፓትሪያርክ ቄርሎስ ሳልሳዊ ኢብን ላቅላቅ (፲፩፻፴፩-፲፩፻፵፫) የሕግ አማካሪ ሆኖ ከማገልገሉም በላይ በርከት ያሉ በተለይም ሃይማኖትን የሚመለከቱ ጽሑፎች አዘጋጅቷል ።[40] "አሳላዳውያን" (Assalades) በመ ንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶችና በትምህርት (ምሁርነት) ከፍተኛ ደረጃ የነበራቸው ጥንታዊ የኮፕት ቤተሰብ (አውላድ አል አሳል) ነበሩ ።[41] ኢብን አል-አሳል በሚል ስም የሚታወቁ ቢያንስ አራት ወንድማማቾች ሲኖሩ ከነዚህ መሐከል ሦስቱ በሥነ ጽሑፍ የታወቁ ስለነበሩ የትኛው ኢብን አል አሳል የሕግ መጽሐፉን እንደጻፈ መጠነኛ ውዥንብር ነበር ። በቅድሚያ በተዘጋጀውና እምብዛም ባልታወቀው ቅጅ ደራሲነት የሚታወቀው ታናሽየው አል ሙታማን (አድ-ደውላ) አቡ ኢሳቅ ኢብራሂም ኢብን አል-አሳል[42] ሲሆን ሁለተኛው አል አሳድ አቡል-ፋለግ ሂሊህ ኢብን አል አሳል የውርስ ሕግ ማብራሪያ እንደደረሰ ይታወቃል ።[43] የሚታመ ነው ቅጅ ደራሲ ግን ታላቅየው አስ ሳፍ ኢብን አል-አሳል እንደሆነ በሚገባ የተረጋገጠ ይመስላል ።[44] ጥንታዊ ከሆኑት የእጅ ጽሑፎች በአንዱ እንደተመ ለከተው የመጽሐፉ ዝግጅት በመስከረም ፲፪፻፴፰ ተጠ ናቀቀል ። ሕግን እንደገና በማብራራት ረገድ ለትም ህርታዊ ተጠቃሽነት የታቀደ ቢሆንም መጽሐፉ ወዲያ ውኑ በዳኝነት ሥራ አካሄድ በግንባር ቀደም በመጠ ቀስ የሚያገለግልና የግብፅ ኮፕት ቤተክርስቲያን የመ ተዳደሪያ ጽሑፍ[45] (textus receptus) ሆኗል ።

የኮፕት ቋንቋ በሕግ ሥነ ጽሑፍ የነበረው መገልገያ ነት በ፲፭ኛው ምዕተ ዓመት ቀርቶ ስለነበር የዘመኑ የጥ ንት የሕግ ጽሑፎች የተዘጋጁት በአረብኛ ነው ። እነ ዚህም ጥንታዊ የሕግ ጽሑፎች በግሪክ-ሮማን ዘመን[46] እንደሚገኘው ጥንታዊ የኮፕት ፓፓይር (Papyri)[47] ሳይሆን በአጠቃላይ "የክርስቲያን አረብኛ ሥነ ጽሁፍ" ተብሎ ከሚጠቀሰው ክፍል ናቸው ። በግብፅ ውስጥ በእ ስላም አስተዳደር ሥር እንደነበሩት እንደ ሌሎቹ የክ ርስቲያን ማኅበረ ሰብ ሁሉ ኮፕቶችም በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ራሳቸውን የማስተዳደር በተለይም የቤተ ሰብ ሕግንና ውርስን[48] በሚመለከቱ ጉዳዮች የቤተ ክርስ ቲያን ባለሥልጣኖች የፍርድ ሥልጣን (episcopales audientia) ነበራቸው ። ይህም በኢትዮጵያ[50] የእ ስልምና ፍርድ ቤቶች ካላቸው ከፊል ነፃነት (አውቶ ኖሚ) የሚመሳሰል ነው ። ሆኖም አጠቃላይ ከሆነው የእስልምና የሸርያ ሕግ ጋር ሲነጻጸር ለምዕመናኑ ዝር ዝር ያለ ሥርዓተ ሕግ አላወጣም ። የግብጽ መለካው ያን (Melechites) በቅዱሳት መጻሕፍትና በተለያዩ መንፈሳዊ ምንጮች ሊያገኙ ከሚችሏቸው ተራ የግብረ ገብነት ደንቦች ባሻገር በ፭ኛ ክፍ አካባቢ "ለሰዎች ሕግ" (Personal Law) ባደረጉት ፍለጋ የግሪክ ባህ ንታይን የፍትሐብሔር ሕጎችን እየመረመሩ ወደ አረብኛ መተርጎም ጀመሩ ።

ሆኖም የኮፕት ማኅበረሰብ አብዛኛዎቹን ትርጓሜ ዎችና ቅንጅቶች[50] የተጠቀመውና የተቀበለው በሃይ ማኖት ትምህርት ረገድ አንዳንድ ማስተካከያ በማድ ረግ ነው ። በዚህ ዓይነት በኮፕት ቤተ ክርስቲያን እንደ ከሃዲ የሚቆጠሩ የባዛንታይን ነገሥታት ክርዕሱ ተሰ ርዘው ሕጎቻቸውም ለታላቁ ቆስጠንጢኖስና ለኒቂያው ጉባኤ ተሰጥተዋል ። ይህ በዕምነት ላይ የተመረኮዘ የማመሳሰል ድርጊት ሬይል[51] እንደገመተው ባለማ ወቅ የተፈጸመ ሳይሆን ሆነ ብሎ የተደረገ ነው ። ይህም በዘመኑ የነበረውን የኮፕት ትምህርት ሃይማኖት ቃል በቃል ለሚጠቅሰው[52] በፍትሐ ነገሥቱ መቅድም መጀ መሪያ ክፍል ላለው ቦታውን የሳተ ሐሳብና መጽሐፍም ለተሰጠው "የነገሥታት ሕግ" የሚል ቁንጽል ስያሜ ምክንያት ሆኖአል ።

የባዛንታይን የሕግ መጻሕፍት

ኢብን አል-አሳል የሕግ መጻሕፉ ተመሠረተባቸው የሚላቸውን ምንጮች በመግቢያው አመልክቷል ። ለመጀመሪያው መንፈሳዊ ክፍል ከቅዱሳት መጻሕፍትና የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ደንቦች ውስጥ አስፈላጊ የሆ ኑት መሠረት ሲደረጉ[53] የሁለተኛው (ሥጋዊ) ክፍል ዋና ምንጭ ደግሞ "በንጉሡ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ ቤተ መንግሥት"[54] ተጽፎአል የሚባለው አራት መጻ ሕፍት ያሉት "የነገሥታት ሕግ" ነው ።

ከነዚህ አራት መጻሕፍት ለሕግ ንጽጽር ተፈላጊነት ያላቸው ሦስቱ ብቻ ሲሆን አራተኛው "የብሉይ ኪዳን ትእዛዛት"[55] የሚባለው ነው ። "የነገሥታት ደንብ" አንደኛ ፤ ሁለተኛና ሦስተኛ መጻሕፍት ፤ በሕግ መጽ ሐፍና በኢትዮጵያ ውስጥ በተተረጎመው በምኅጻረ ቃል ጠስ (TS) ፤ መክ (MAK) እና መጅ (MAG) ተብለው የተጠቀሱት ፡ የፍትሐ ነገሥቱ ትክክለኛ ሥጋዊ ምንጮች ናቸው ። የእነዚህን ሦስት መጻሕፍት አመጣጥ ለማወቅና ለመለየት ሲባል በሕግ ታሪክና ቋንቋ ሊቃውንት ብዙ ምርምርና ክርክር ተካሂዶአል ። ሬንዶ በ፲፯፻፲፫[56] ሲጽፍ በመጀመሪያ በነርሱና በባ ዛንታይን ሮማ ሕግ መሐከል ግንኙነት እንዳለ አመል ክቷል ። እነዚህ ደንቦች (ሕጎች) ከግሪክ የሕግ መጻሕ ፍት ፡ ከቴዎዲዮስና ጀስቲንያን ጥንታዊ ጽሑፎች (Codex) ፤ አዳዲስ ሕጎች (Digesta) እና ሕገ መን ግሥቶች (Novella) እና ባሲሊካ (Basilica) በሚባል መጠርያ ከታወቁ ሕግጋት የተውጣጡ እንጂ ሌሎች አዲስ ሕጎች ያልነበሩ ሲሆን ሕጎቹ ከላይ በተ

ጠቀሰው አኳኋን ተቀናጅተው በክርስቲያኖች መሐከል የሚነሱ ክርክሮችን ለመዳኘት ያገለግሉ ነበር ። ሆኖም ሥርዓት ባለው መንገድ በተከታታይነት የተካሄዱ ጥናቶች ከዚህ የሚከተሉትን ውጤቶች አስገኝተዋል ።

ሀ/ ፕሮሸሪየን (Procheiron)

"የነገሥታቱ ደንብ" የመጀመሪያው መጽሐፍ በባዛንታይን ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ባሲል ዘመቄዶንያ በ፰፻፸፱ በታወጀው የሮማውያን ሕግ ዝነኛ መመርያ የፕሮሸሪየን የአረብኛ ትርጉም መሆኑን አማሪ በ፲፰፻ ፶፱ አካባቢ ተገንዝቧል ። [57] ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ በ፲፰፻፹፫ [58] የተገለጸና በሬይል [59] የተረጋገጠ ሲሆን ናሲኖ አንቀጽ በአንቀጽ ባደረገው ንጽጽር ከ፰፻ በላይ የሆኑ የፍትሐ ነገሥት ጠስ (TS) ጥቅሶች በአረብኛ የሕግ መጽሐፍ በኩል ፕሮሸሪየን ውስጥ አግኝቷል ። [60] ከግሪክ ወደ አረብኛ የተተረጎመው በ፲፰ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ወይም በ፲፱ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በመለካውያን ይመስላል ። [61]

ለ/ የሱሮ-ሮማውያን (Syrio-Roman) የሕግ መጽሐፍ

"የነገሥታቱ ደንብ ሁለተኛ መጽሐፍ" "የሱሮ ሮማውያን የሕግ መጽሐፍ" ተብሎ ከሚታወቀው ፡ በተጨማሪ "የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ፡ ቴዎድስየስና ሊዎ ሕግ" የሚል ርዕስ ከተሰጠው ፡ ወደ አረብኛ መተርጎሙን ሳቻ [62] በ፲፰፻፹ ተገንዝቧል ። ይህም ከ፰፻፫-፰፻፹ ባለው ጊዜ በግሪክ ቋንቋ ተጠናቅሮ ፡ ወደ ሶርያ ቋንቋ በ፯፻፺ እና ወደ አረብኛ በ፰፻፭ ተተርጉሞአል። [63]

ሴልብ [64] በቅርቡ ያደረገው ጥናት ቀደም ሲል ከተሰጡ ትርጉሞች በመቃረን [65] ፤ በመሠረቱ በሮማ ንጉሠ ነገሥት ግዛት ምሥራቅ ክፍል በሥራ ላይ የዋለ የሮማ ሕግ መግለጫ እንደሆነና ምናልባትም ለማስተማርያነት እንዲያገለግል እንደተጻፈ አመልክቷል ። [66] ይህም ምንጭ በፍትሐ ነገሥቱ ውስጥ ፹፱ ጊዜ መክ (MAK) ተጠቅሶአል ። ደ ኤሚልያ በጣም ጠቃሚ ስለሆነው ሽያጭን ስለሚመለከተው አንቀጽ ባደረገውም ጥናት የፕሮሸሪየንና የሱሮ-ሮማን አዝማሚያ እንዳለበት አሳይቷል ። [67]

ሐ/ ኤኮልጋ (Ecolga)

በፍትሐ ነገሥቱ ውስጥ ከተጠቃለሉት መጻሕፍት ምንጩን ለመለየት የሚያስቸግረው ሦስተኛው መጽሐፍ ሲሆን ይህም ከኢብን አል-አሳል የምንጭ አመለካከት ግራ የሚያጋባ መሆን በከፊል የሚመነጭ ነው ። ሪዴልና ናሲኖ ሦስተኛው መጽሐፍ ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ የሆኑ ሥጋዊ ሕግጋት (ከነዚህም አብዛኛዎቹ የጋብቻ ጉዳይን የሚመለከቱ የሠለስቱ ምዕት (ኒቂያ) ሕግጋትና ትዕዛዝት) (Sanctorum Patrum 318 (Nicaenorium) Sanctiones et Decreta) [68] የአረብኛ ትርጉም መሆኑን ገምቷል ። በሌላ በኩል ግን ፍትሐ ነገሥት ውስጥ ያሉት ፵፭ መጅ (MAG) ጥቅሶች ፡ ጋብቻ ፡ ውስር ፡ የወንጀል ሕግ ፡ ጥገኝነትና ሥነ ሥርዓትን ጨምሮ ስለ ሕግ ጉዳዮች በዝርዝር የሚያወሱ ናቸው ። ኮስታንዞ [69] በ፲፱፻፸፯ አንቀጽ በአንቀጽ ያደረገው ትንታኔ ቢያንስ ፭፬ የመጅ (MAG) ጥቅሶች ፡ ኢብን አል-አሳል [70] የሚያውቀው መሆኑን ናሲኖ ባያምንበትም ከሌላ የታወቀ የሮማ የሕግ መጽሐፍ መመሳሰሉን አመልክቷል ። ይህም የታወቀው የሕግ መጽሐፍ በባዛንታይኑ ንጉሠ ነገሥት አሶርያዊ ሊዎ ሳልሳዊ እና በልጅዮው (እንደራሴውም) በቆስጠንጢኖስ አምስተኛ ኮፕሮንያሞስ [71] የታወጀው "ኤኮልጋ" (ምርጥ) የሚባለው ነው ። ጥቅሶቹ ቀደም ሲል ከነበረ የኤኮልጋ የአረብኛ ትርጉም በማውጣጣት መላካውያን በ፲፫ኛው ምዕተ ዓመት [72] ባዘጋጁትና የኒቅያ ደንቦች በተጠቃለሉበት ጽሑፍ የተመሠረተ ይመስላል ።

ከፍትሐ ነገሥት ክፍሎች እስካሁን ምንጩ ሳይታወቅ የቀረው አባሪው ብቻ ነው ። ይህም "የእስክንድርያው ፓትርያርክ አባ ቄርሎስ ከጳጳሳት ፡ ከዳኞችና ባላባቶች ጋር ያበጁት የውርስ ምዕራፍ" የሚባለው ነው ። ይህ በ፲፪፻፶፭ የታወጀውና ስለዚህም በቀዳሚው የኢብን ኤል አሳል የአረብኛ የሕግ መጽሐፍ የማይገኘው ምዕራፍ ከቄርሎስ ሳልሳዊ ኢብን ላቅላቅ ደንቦች የውርስ ምዕራፍ ቃል በቃል ወደ ግዕዝ የተተረጎመ ነው ። [73] እነዚህም ደንቦች በኢብን አል-አሳል የተረቀቁ ሊሆኑ ይችላሉ ። [74] ፍትሐ ነገሥቱም ውስጥ በድጋሚ የተጠቀሰው እነዚህ ክፍሎች የአባ ኮስማስ ምናልባትም በ፲፪፻፴፫ ያረፉት ፓትርያርክ ኩዝማን ሳልሳዊ ሊሆኑ ይችላሉ ፤ ጽሑፎችና ከላይ ከተጠቀሱት የባዛንታይን ምንጮች ተመሳሳይ የሆኑ በውል ባልታወቁ አንዳንድ የሕግ መጻሕፍት የተመሠረቱ ናቸው ።

የፍትሐ ነገሥቱ አባሪ [75] የአማርኛ ማብራሪያ ከኮስማስ ሌላ አባ ገብርኤል የሚባል ሰው ሲጠቅስ ፡ ይህም የውርስ ዝርዝር ዓይነቶችንና ደረጃዎችን (ለንጉሠ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ) የሚሰጠውን እና በተለይም "የነገሥታቱን ደንብ" እንደምንጩ የሚያመለክተውን የኮፕት ፓትርያርክ ገብርኤል ዳግማዊ ኢብን ታሪክን (፭፻፭፴፭-፭፻፭፶፭) የውርስ ሕግጋት መጥቀሱ ሊሆን ይችላል ። [76]

የእስልምና አዝማሚያ

በመጨረሻም የሕግ መጽሐፍ ደራሲ የኖረበትንና የጻፈበትን ፖለቲካዊና ባሕላዊ አካባቢ ፡ ይህም የኮፕት ማኅበረ ሰብ ከሰባተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ሲጎዛ የቆየበትን የእስልምና ሥልጣኔ ያንጸባርቃል ። በታወቁ የትምህርተ ሃይማኖት ምክንያቶች ኢብን አል-አሳል የእስልምና ምንጮቹን ባይጠቅስም [77] በተለይም ሽያጭን ፡ ጉልትን ፡ ፍችን ፡ የወንጀል ቅጣትንና ሥነ ሥርዓትን [78] የሚመለከቱት የሕግ መጽሐፍ ድንጋጌዎች በቀጥታ ከእስልምና ሕግ የተወሰዱ (በይበልጥ ከመለካውያን ትምህርት ቤት [79]) መሆናቸው ተረጋግጧል ። የእስልምናና የሮማ ሕግጋት ጎን ለጎን ሲታዩ ፡ ለምሳሌም ከጥንታዊው የውርስ ሕግ በፊት እንደነበረው ሕጋዊ ድርሻ (portio legitma) በእስላም የኑዛዜ ሕግ [80] እንዳለው "የሚተው ሩብ (ድርሻ)" እና በሽያጭ ሕግ እንዳለው "በጋራ መኖር" ዓይነት አልፎ አልፎ ይገኛሉ ። [81]

ፍትሐ ነገሥቱ መሠረታዊ ድንጋጌዎችን ከአረብኛ ከመቀበሉም በላይ የሕግ ቲየሪ አቀራረቡም የአረብኛ መሠረት እንዳለው በግልጽ ያንጸባርቃል ። የአርዕስቱ ዝግጅት ከሮማውያን ይልቅ የእስልምናን ሥርዓት እንደ ሚከተል ፣ ምግብንና ልብስን የሚመለከቱ ክፍሎችም መጨመር ከሮማውያን የፍትሐ ብሔር ሕግ (ius civilie) ይልቅ ፊቅን (fiqh) እንደሚቀርብ ናሊኖ[82] አመልክቷል ። ሕግን እንደ ሃይማኖት ክፍል መቁጠር በእስልምና የተለመደ ሲሆን[83] ይህ ለሮማውያን የሕግ ሊቃውንት እንግዳ ነገር ነው ። የፍትሐ ነገሥቱም የአጻጻፍ ዘዴ የእስልምና የሕግ ሊቃውንት አቀራረብ ባሕርያዊ ገጽታዎች ይታዩበታል ። ኢብን አል-አሳል ለሕግ መጽሐፍ ያበረከተው አስተዋጽኦ ከታመኑ ምን ጮች በማውጣት በማውረድና በማመሳሰል መሆኑን በመግቢያው ገልጾአል ። ይህም የኩያ (quiyas) የእስልምና የሕግ ሊቃውንት የአሠራር ስልት በግልጽ የሚከተል ሲሆን ስለውርስ የሚደነግገው አባሪውም "የእስክንድርያው ፓትርያርክ አባ ቄርሎስ ከጳጳሳት ፣ ከዳኞችና ከባላባቶች"[84] ጋር ያበጁትን ሕጎች መጨ መሩ ከኢጅማ (ijma) የእስልምና ሕግ ቲዎሪ ባል ተለየ መንገድ ሥልጣኑን ከተባበረ ስምምነት ያገኘ መሆኑን ያመለክታል ።[85]

የሮማ ሕጎችን በእስልምና ሥርዓት ማበጀቱ የተሳ ካው አረብኛ የሮማን የሕግ ቃላት ለመገልበጥና ለማ ዘጋጀት በማመቸቱ ነው ።[86] ይህን አሠራር ከውርስ ሕግ ቃላት ምሳሌ በመጥቀስ ማሳየት ይቻላል ። የግሪኩ-ሮማን የሕግ ጽሑፎች ፋልኪደን (falkidion) በሮማውያን "ሌክስ ፋልሲዶያ" (Lex Falcidia) ከሚለው የተወሰደ በኑዛዜ መሠረት በሚደረግ ውርስ ስለሚኖር የማይቀር ድርሻ የሚያመለክት የግሪክ መጠ ሪያ ነው ።[87] የአረብ ትርጓሜዎችም በአረብኛው የፕ ሮቸሮን (Procheiron) ቅጅ መጨረሻ ልዩ ማስታወሻ ላይ ፋልኪዲዮን (falkidion) ወይም ፋልኪድ (ffalkid) በማለት ቃል በቃል ተርጉመውታል ።[88] የኢብን አል አሳል የሕግ መጽሐፍ ይህን ዓይነቱን ማብ ራሪያ በድጋሚ ያልጠቀሰው ጽንሰ ሐሳቡ በዘመኑ በሚ ገባ "አረባዊ" ስለሆነ የግብፅ የሕግ ባለሞያዎች ይረዱ ታል በሚል ግምት ሳይሆን አይቀርም ። ሆኖም መጽ ሐፉን ወደ ግዕዝ የተረጉመው ሰው ፋልኪደን (falki-dion) የሚለውን ቃል በቀጥታ ያለማብራሪያ መገል በጡ ቃሉን ትርጉም ሳያሳጣው አልቀረም ። በ፲፱፻፷፯ በወጣው የፍትሐ ነገሥት እትም የአማርኛ ማብራሪያ ይህን እንግዳ የሆነ ቃል "ውርስን የሚያስተላልፍ" ማለትም አውራሽ ሲል ገልጾታል ።[89]

በሮማ ንጉሠ ነገሥት ግዛት ምሥራቅ አውራጃዎች እንደሚታወቀው በሮማውያንና በእስልምና ሕግጋት መሐከል የነበረው በይነ ግብር (interaction) በዚህ የሕግ መጽሐፍ ይዘትና የጽንሰ ሐሳብ አደረጃጀት ተጽ ዕኖ ኖሮት ይሆናል ።[90] ሀበርላንድ በማጠቃለያው ፍትሐ ነገሥቱ "በእስልምና ሕግ የተመሠረተ ነው ፤ ይህም የእስልምና ሕግ ከሮማና የግሪክ ሕግ[91] (ius gentium) የመነጨ ነው " ሲል የሰጠው አስተያየት መሠረታዊ የሆነውን ነገር ያዛባል ። ያም ሆነ ይህ የዌ ንገርን ዝነኛ አባባል ማጤን ብልህነት ሳይሆን አይ ቀርም ።[92] "በአረብኛ ሰነዶች የሮማንና የባዛንታይንን የሕግ ቅርስ ወይም በሮማና በባዛንታይን ቅርስ አረብኛ ያለውን ተጽዕኖ ለማመልከት የሚሞክር ሰው የሮም ፣ የባዛንታይንና የአረቦች ታሪክ ፣ ቋንቋና ሕግ ሊቅ መሆን ይገባዋል ወይም ብዙውን ጊዜ በሚደራረቡ በነዚህ ሳይንሳዊ የትምህርት ክፍሎች ነፃ አስተያየቱን መሥ ንዘር የሚችል መሆን አለበት ። ለቀረነው ግን ከምርምር ተዛምዶ ያለው ብሩህ ሕሊና ብቻ ይተርፈናል ፤ ይህም ጥቂት የሥነ ጽሑፍ ማገናዘቢያዎችን ማቅረብ ብቻ ይሆናል ።"

ማጠቃለያ

በፍትሐ ነገሥቱ ሁለተኛ (ሥጋዊ) ክፍል ተጽዕኖ ስለነበራቸው ምንጮች የተገኙት የሥነ ጽሑፍ ማስ ረጃዎች ሲጠቃለሉ የሮማ የፍትሐ ብሔር በተለይም ፕሮሸሮን (Procheiron) ዋነኛው ሆኖ ይገኛል ።

ይህ ማጠቃለያ የሸርማንና የዊግሞርን[93] ግምት በከ ፊል ቢያቅፍም ፍትሐ ነገሥቱ ከጀስቲንያን መጽሐፍ (Corpus Iuris civilis) በጣም የተለየ መሆኑ ግልጽ ነው ። የተለያዩ ሦስት የግሪክና የሮማውያን የሕግ መጻሕፍት ወደ አንድ የሕግ መጽሐፍ ማቀናጀት ቅራኔዎች መፍጠሩ ግድ ሲሆን ይህም አንድ ወጥ የነ በረውን ሥርዓት አፍርሶታል ።[94] ሮማዊ ይዘቱ በየ ዘመኑ ከወጡ የነገሥታት ሕጎች ለምሳሌ በሲርያና ሮማ በሕግ መጽሐፍ ከታወቁት "ሕገ መንግሥቶች"[95] የተለያዩ አሻል (layers) የተወሰደ ነው ። በተጨ ማሪም ፍትሐ ነገሥቱ በክርስትና የመለወጥን የተለያዩ ደረጃዎች የሚያንጸባርቅ በተለይም በኤኮልጋ የሚታ ይና የፕሮሸሮንን ተጻራሪ አቅጣጫ የሚከተል ነው ።[96] በዚህም ዓይነት በምሥራቅ (የሮማ) የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት የተደረገው ቁንጽል አጻጻፍና ቀላል ትምህርታዊ ዘይቤ መልኩን ለውጦታል ።[97] የመጀመሪያዎቹ ሕጎች ኢትዮጵያ ከመድረሳቸው በፊት እንኳን በተከታታይነት ሁለት ጊዜ የተተረጐሙ ፣ በባዛንታይን ግሪክና በኮፕት አረብኛ "ባህል የታነጹ" ፤ በመንፈሳዊም ረገድ በኮፕት አርቶዶክስ ፤ በግዛትና አስተዳደርም በእስልምና ሥር ስለወደቁ ምንጫቸው ከሆነው የሮም ሥልጣኔ ተለ ያይተው ቀርተዋል ።

ከላይ ከተመለከቱት የማያመቹ ሁኔታዎች አንጻር ሲታይ የዚህ ቁንጽል የሮማ ሕግ ፍጹም የተለየ ማኅ በራዊ አካባቢ ባለው በኢትዮጵያ የተሳካ አቀባበል ማግኘትና እንደሚስማማ መገልበጥ አስደናቂ ነው ። ከ፲፯ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በሚገባ የተጠናቀረውና በአሁኑ ጊዜ ለሚካሄድ ጥናት መሠረት የሆነው ፍትሐ ነገሥት ሕልውናና የማያቋርጥ ዕድገት (ለውጥ) የሕግ ሥርዓቶች በተለያዩ ባሕላት ለመጓዝና ለመዋሃድ ስላ ላቸው ችሎታ ምሳሌ ይሆናል ።

የሶሻሊስት ኢትዮጵያ የሥራ ክንውኖች በመሠረታዊ ሕጎች እንደታየው ።

በፋሲል ናሆም *

አብዮቱ ፤ ወሳኝ ወቅትነቱ ።

ኢትዮጵያ በዓለም ውስጥ ጥንታዊ ከሆኑት አገሮች አንዷ ናት ። ከክርስቶስ ልደት በፊት ከብዙ ምዕተ ዓመታት ጀምሮ አስደናቂና ያልተቋረጠ የነፃነት ታሪክ ይዛ የቆየች አገር ናት ።[1] ስለዚህም ከቅኝ አገዛዝ መንጋጋ በሃይል በመላቀቅ በጣም በቅርብ ጊዜ ሕልውናቸውን ከአገኙት ከአብዛኛዎቹ የአፍሪካ እና ሌሎች ታዳጊ አገሮች መካከል ጎላ ብላ ትታያለች ። በሌላው ረገድ ግን ፤ ኢትዮጵያ ገና በማደግ ላይ ያለች ሀገር ናት ፤ በዚህም የተነሳ የታዳጊ አገሮች ልዩ ምልክት የሆነውን አስከፊ የሶስዮ ኢኮኖሚ ኋላ ቀርነት አብራ ተካፍላለች ። ኢትዮጵያ ረዘም ያለ የነፃነት ታሪክ ፣ ኩሩና ወኔ ያለው ሕዝብና ገና ያልተነካ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ቢኖራትም ፤ ባለመታደል እስከአሁን ድረስ ሕዝቦችዋ በድህነትና በኋላ ቀርነት የሚማቅቁበት አገር ሆና መቆየቷ ነው ። በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለረጅም ጊዜ እንደ ቀንበር ሆኖ ሲያስጨንቀው የቆየው የፊውዳሉ ሥርዓት ፣ መንግሥታዊ መዋቅሩና አስተዳደሩ በመሠረቱ ይህን ለመሰለው ሁኔታ ተጠያቂ ነው ። እንግዲህ ለብዙ ጊዜ የተጠበቀውን ሕዝባዊ አብዮት መፈንዳት ዋነኛ ምክንያት የሆነው ይህ ሁኔታ ነበር ።

ሕዝባዊ አብዮት አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸም ድርጊት ወይም ሁኔታ አይደለም ፤ ረዥምና አስቸጋሪ የሆነ ሂደት እንጂ ። ይህ አብዮት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይም በ፲፱፻፷፭ና በ፲፱፻፷፮ ዓ/ም መካከል ባሉት ዓመታት ውስጥ በሠርቶ አደሩ ፣ በወታደሩ ፣ በአርሶ አደሩ ፣ በተማሪውና በምሁሩ የለውጥ ፍላጎት ምክንያት በተደረጉት ትግሎች አያሌ ያለፉ ታሪኮች አሉት ። ይህም ጽሑፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ የአብዮቱ ሂደት ገና በመጀመሪያ ገጽታው ላይ ስለሆነ የአብዮቱን ውጤቶች በትክክል ለመገምገምና ለመጨበጥ በቂ ጊዜ አይደለም ። ይሁንና ፣ በዚህ የመጀመሪያ ገጽታም ቢሆን ፍጹም መሠረታዊ የሆኑ የሥራ ክንውኖች ጎልተው ይታያሉ ። የዚህችም አጭር መቅድማዊ ጽሑፍ ዓላማ ባለፉት ዓመታት ውስጥ የአብዮቱ ዋና ዋና የሥራ ክንውኖች በመሠረታዊ ሕጎች ውስጥ እንዴት እንደተፈነጠቁ ለማየት እንጂ ዝርዝርና ጥልቅ ትንተና ለማድረግ አይደለም ።

የኢትዮጵያ አብዮት "የሕግ አብዮት" በመሆኑ ፣ በአብዮቱ ሂደት ውስጥ የተፈጸሙትን ዋነኞቹን የኢትዮጵያን የሥራ ክንውኖች ፣ የወጡትን መሠረታዊ ሕጎች በመመርመር ከሞላ ጎደል ትክክለኛ መልካቸውን ማቅረብ ይቻላል ። "የሕግ አብዮት" የሚለውን ሐረግ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እንዴት እንደተጠቀምን በት በአጭሩ መግለጽ ያስፈልግ ይሆናል ። ይኸውም ሁለት ትርጉም ያዘለ ነው ። መጀመሪያ "የሕግ አብዮት" የሚለው ሐረግ ቴክኒካዊ አገላለጽ ነው ። ይህም ማለት የኢትዮጵያ አብዮት አንዱ መለያ ጠባዩ መሠረታዊ ለውጦችን ለማምጣት በሕግ መጠቀሙ ነው ። እስካሁን የተደረጉት መሠረታዊ ለውጦች ሁሉ አግባብ ያለው ሕግ ተመክሮበት ሳይወጣ ወይም ሳይታወጅ አልተፈጸሙም ።[2] ይሁንና "የሕግ አብዮት" የሚለው ሐረግ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተሰጠው ሁለተኛው ትርጉም ጥልቅ የሆነ ፍሬ ነገር ያዘለ ነው ። ይኸውም አብዮቱ አብዛኛውን ፊውዳላዊ በነበረው የኑሮ ሥርዓት ውስጥ ሲከማች በቆየው አጠቃላይ ጭቆናና በደል ላይ የተመሠረተ ፍንዳታ ነበር ። ዓላማውም አዲስ ፍትሕን ለመቀዳጀት ነው ። ፍትሕ ሲባልም ውስጉ ከሆነው ከግለሰብ አንጻር የሚታይ ሳይሆን ፣ ለጥቂቶቹ የከፍተኛው መደብ አባላት ልዩ መብት ማጎናጸፊያም ሳይሆን ፣ ሥርዓትን በተከተለና ሰፋ ባለ አስተሳሰብ ፣ ፍትሕ ለሰፊው ሕዝብ በሚል አንባር እንጂ ። ዓላማቸው ብዝበዛና ጭቆና የሆኑትን የቀድሞ ግንኙነቶችን በመለወጥ የሰውን ልጅ ማንነት በሚያረጋጣጡ ሰብአዊ ግንኙነቶች በመተካት እውነተኛውን ማህበራዊ ፍትሕ በማስገኘት ነው ። ይህ ማኅበራዊ ፍትሕ አዲስ የሆነና ከቀድሞ ሁኔታ የተላቀቀ ግለሰባዊ ፍትሕ ጭምር ማስገኘቱ አይጠረጠርም ። ሕግ ልዕልናን በሚቀዳጅበት በማንኛውም በከፍተኛ ደረጃው በተለይም የሕብረተሰባዊ ሕጋዊነት ፣ (ሶሻሊስት ሌጋሊቲ) ፣ ሁል ጊዜ የሚያልመው ከፍተኛውንና ከሁሉም ይበልጥ

---

* ዲንና ረዳት ፕሮፌሰር ፣ ሕግ ፋኩልቲ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ።

1 ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ከተጻፉት መጻሕፍት በጥቂቱ እነዚህን መመልከት ይቻላል ። ኮንቲ ሮሲኒ ስቶሪአ ደ ኢትዮጲያ (ሮማ ፲፱፻፳፰ እ ኤ አ) ፣ ጃን ዶረስ ለቴዮር (ፓሪስ ፲፱፻፶፩ እ ኤ አ የእንግሊዝኛ ትርጉም ፲፱፻፶፱ እ ኤ አ) ፣ ኢ ደብልዩ ባድጀ ኤ ሂስቶሪ አፍ ኢትዮጲያ ኑቢያ ኤንድ አቢሲኒያ (ዋራዝ ሁለት ለንደን ፲፱፻፷፫ እ ኤ አ) ። በተለይ ደግሞ ኤስ ፍበንሶን ዘ ሳርቫይቫል አፍ ኤትዮጲያን ኢንዲፓንደንስ (ለንደን ፲፱፻፷፭ እ ኤ አ) ፣ ማኅተመ ሥላሴ ወ/መስቀል ዝክረ ነገር (አዲስ አበባ ፲፱፻፶፭ እ ኤ አ) እና ተክለጻዲቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ልብነ ድንግል እስከ አጼ ቴዎድሮስ (አዲስ አበባ ፲፱፻፶፯ እ ኤ አ) መመልከት ይቻላል ።

2 ሕጋዊ በሆኑ ዘዴዎች ብቻ በመጠቀም አዲአዊውን ሕገ መንግሥታዊ ተቋም በተለይ በመጀመሪያው ወቅት ወደ ህብረተሰብአዊ ተቋም ማዛወር እንዳልተቻለ ግልጽ ነው ። ይህም የሆነበት ምክንያት የሥልጣን አያያዙ በማይነቃነቅ ሁኔታ ታስሮ ስለ ነበር ነው ።

የተሟላውን ፍትሕ ለማግኘት በመሆኑ ሁለቱ ማለትም ሕግና ፍትሕ በቲዎሪ የተሳሰሩ ናቸው ። የኢትዮጵያን አብዮት እንደ ‘‘የሕግ አብዮት’’ የቆጠርነውም በዚሁ ምክንያት ነው ። አብዮቱ የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ማሻሻልና ይህንንም ለማስፈጸም የሚያስችሉ ውሳኔዎች ለመስጠት አመች የሆኑ ዘዴዎችን ለመፍጠር ዓላማ ያላቸው መመሪያዎች እንዲወጡ አስችሏል ። እነዚህም የተከናወኑት በመሠረታዊ ሕጎች አማካይነት ነው ። እነዚህም መሠረታዊ ሕጎች የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ፍላጎት እንዲገልጹ ፣ ሕብረተሰብአዊ አስተዳደር ግቡን ይመታ ዘንድ ማኅበራዊ ግንኙነቶችን እንዲቆጣጠሩ ፣ ብሎም የኢትዮጵያ የማኅበራዊና የመንግሥታዊ ሥርዓት መሠረቶች እንዲሆኑ የታሰቡ የሕግ መሠረታዊ አሳቦች ድምር ውጤት ናቸው ።

‘መሠረታዊ ሕጎች’ ሲባል በአንዳንድ ሰዎች አእምሮ ውስጥ የሕገ መንግሥትን ሀሳብ ሊያሳድር ይችል ይሆናል ። የሕግ ሰዎችም በመሠረታዊ ሕጎችና በሕገ መንግሥት መካከል ስላለው ግንኙነት መመራመር ይጀምሩ ይሆናል ። ሕገ መንግሥት ሲባል የሚታሰበው አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ጽሑፍ ተወስኖ የቀረበ የመንግሥትን መሠረታዊ መመሪያዎች የያዘ መሠረታዊ ሕግ ነው ከተባለ ፣ ኢትዮጵያ እስከአሁን ድረስ ይህን የመሰለ በአንድ ጽሑፍ የተወሰነ በኦፊሴል የጸደቀ (de jure) ሕገ መንግሥት የላትም ። ይሁን እንጂ ይህ አባባል አንድን ሰው ኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የላትም ወደሚለው የተሳሳተ አቅጣጫ ሊመራው አይገባም ፤ ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ተግባራዊ (de facto) ሕገ መንግሥት አላትና ። ይህንንም የምንልበት ምክንያት ፣ ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከታቸው ልዩ ልዩ መሠረታዊ ሕጎች ሕገ መንግሥታዊ ይዘት ያላቸው በመሆናቸው ነው ።[3]

እነዚህ መሠረታዊ ሕጎች እንደ ቅድመ ሕገ መንግሥት ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች (constitutional acts) መታሰብ ይኖርባቸዋል ። ከዚህም በላይ እነዚሁኑ ከሁለት ቦታ መክፈሉ ተገቢና አመቺም ነው ። የመጀመሪያዎቹ ዓይነቶች ጊዜያዊ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች (provisional constitutional acts) ናቸው ። እነዚህም የቀድሞ ያረጀ ያፈጀ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ለማስወገድና አዲስ ሕገ መንግሥታዊ መመሪያዎችን ፣ እንዲሁም አዲስ የውሳኔ አሰጣጥና የሥነ ሥርዓት ጥርጊያ መንገዶችን ለማውጣት ሲባል ሆን ተብሎ የታወጁ ጊዜያዊ ፣ ክፍት ቦታን የሚያሟሉ ፣ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች ናቸው ። እነርሱም በተፈጥሮአቸው ጊዜያዊ በመሆናቸው በኦፊሴል የፀደቀ (de jure) ሕገ መንግሥት የሚያስፈልግበት የፖለቲካ ወቅት ሲደርስ አዲስ ሕብረተሰብአዊ ሕገ መንግሥት ይተካቸዋል ። ስለዚህ እነዚህን ጊዜያዊ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እንመለከታቸውም ።

እዚህ ላይ የ፲፱፻፷፮ አዋጅ ቁጥር ፩ እና ተከታታይ ማሻሻያዎቹ የጊዜያዊ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች ጥሩ ምሳሌዎች መሆናቸውን ማስታወሱ ብቻ ይበቃል ።[4]

ሁለተኛዎቹ ዓይነቶች ይበልጥ ቀዋሚና መሠረታዊ የሆኑ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች ናቸው ። እነዚህን ደንቦች እንደ ቀዋሚ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች መቁጠር ዋነኛና (substantive) ሥነ ሥርዓታዊ ሕጎችን በሚመለከት ረገድ ተጨማሪ ዕድገትና ለውጥ አይኖርም ማለት አይደለም ። ነገር ግን አዲሱ ሕብረተሰብአዊ ሕገ መንግሥት በቀዋሚ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች ውስጥ ያሉት መሠረታዊ መመሪያዎች እንዲጠናከሩና በከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲጠበቁ ያደርጋል ። በዚህ ጽሑፍም ትኩረት የሚሰጠው ለነዚሁ ለሁለተኞቹ ዓይነቶች ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች ነው ።

ለዚህም ፣ አምስት መሠረታዊ ሕጎች በሕገ መንግሥታዊ ደንቦች መደብ ውስጥ በግልጽ የሚገቡ በመሆናቸው ሆን ተብሎ ተመርጠዋል ። እነዚህም አንድ ፣ የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ፤ ሁለት ፣ የገበሬዎች ማህበራትን ለማደራጀትና ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ፤ ሦስት ፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የወጣ አዋጅ ፤ አራት ፣ የከተማ ነዋሪዎች የህብረት ሥራ ማህበር ማጠናከሪያ የማዘጋጃ ቤቶች አዋጅና ፤ አምስት ፣ የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ናቸው ።

የገጠሩ መለወጥ ።

በአንዳንድ የምሁራን አካባቢዎች ስለ ‘‘መሬት ይዞታ መሻሻልና’’ ስለ ‘‘መሬት ይዞታ ማሻሻያ ሕጎች’’ በሚነገርበት ጊዜ የመሬት ይዞታ ለውጥ የመጠን ለውጥ ብቻ ይመስል ፣ መሠረታዊ የዓይነት ለውጥ መኖሩን በመዘንጋት ፣ የተለያዩ ሕብረተሰቦች ያገኙአቸውን የመሬት ይዞታ ለውጥ ልምዶች አቀላቅሎ ማየት የተለመደ ነው ። የገጠርን መሬት የሕዝብ ለማድረግ የወጣውን አዋጅ[5] እንደ መሬት ይዞታ ማሻሻያ አዋጅ ብቻ መቁጠር ያልሆነ ስም መስጠት ብቻ ሳይሆን ፣ የአዋጁን ቁም ነገር መናቅና የሰጠውን አገልግሎት መርሳት ይሆናል ። አዋጁ የሚደነግገው ጥገናዊ ለውጥን ሳይሆን የቀድሞውን የገጠሩን ሥርዓት ፍጹም መለወጥ ነው ። አዋጁ[5] ከአዲስ መሠረት በመነሳት በአዲስ የታሪክ ገጽ ላይ እንድንጀምር ያደርጋል ። እንግዲህ ይህ አዋጅ ያለ ጥርጥር የአብዮቱ ወሳኝ ገጽ በመሆኑ ፣ አብዮቱ ከወለዳቸው በጣም መሠረታዊ ከሆኑት ሕገ መንግስታዊ ደንቦች መካከል አውራ ሆኖ ሊታይ ይገባል ።

ይህ አዋጅ የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት በማድረግና የፊውዳሉን የምርት ግንኙነቶች ፈጽሞ በማቋ

---

3 ከመሠረታውያን ሕጎች ሌላ መሠረታውያን የሆኑ የፖሊሲ መግለጫዎች እንዳሉ መዘንጋት አያስፈልግም ። ከወጡት መግለጫዎች ከፍተኛው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮታዊው መለስተኛ ፕሮግራም ነው ። ይህ መግለጫ ለአብዮቱ አጠቃላይ መመሪያ ቢሆንም ፣ ከዚህ ማለትም ስለመሠረታዊ ሕጎች ብቻ ከሚያወሳ ጽሑፍ ወጣ ብሎ ይገኛል ።

4 ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትን የተቋቋመበት አዋጅ ቁ ፩ የ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፭ኛው ዓመት ቁጥር ፩ ። ይህ አዋጅና ማሻሻያዎቹ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ኃላፊነት እንዲገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ ፩፻፲ የ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፮ኛ ዓመት ቁጥር ፲፫ ተጠቃልሎአል ።

5 የገጠር መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቁ ፴፭ የ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፬ ዓመት ቁ ፭፯ ።

ረጥ የፌውዳሉን መዋቅር ከመሠረቱ በመምታት ለወደፊቱ እንዳይንሰራራ አድርጎታል ። በገጠራቱ ኢትዮጵያ ለመሬት የሚሰጠው ክብርና ከፍተኛ ግምት በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። በአዋጁ መግቢያ ላይ እንደ ተመለከተው "እንድ ሰው በህብረተሰቡ ውስጥ ሊኖረው የሚችለው የኑሮ ደረጃ ፣ መብት እንዲሁም ክብርና ማዕረግ የሚወሰነው ከመሬት ጋር ባለው ግንኙነት" ነው ። ከዚህም በላይ ገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል ከመቶ ዘጠና የሚሆነውን የኢትዮጵያን አካል ስለሚያጠቃልል በትክክል ዋነኛው ኢትዮጵያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

እዚህ ላይ ነው የፊውዳሉ ሥርዓት ሥረ መሠረቱ ፣ ሰውን በሰው መበዝበዝ ላይ የተመሠረተው የእርሻ ኤኮኖሚ ፣ በጣም ጥቂት በነበሩ ግለሰቦች እጅ የነበረውና ከትውልድ ሲተላለፍ የቆየው የመሬት የግል ባለ ሀብትነት ፣ እንዲሁም በኤኮኖሚ ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካ መስክ በሰፊው ሕዝብ ላይ የሚደርሰው በደል በዘዴ እንዲስፋፋ ያደረገው ። ስለዚህ ነው ቡተወሳሰበ መንገድ የተደራረበውና ብዙ መልኮች ያሉት የጭሰኛውና የባላባቱ ግንኙነቶች ባጠቃላይም በእርሻው መስክ የነበረውን ግንኙነት መመታትና ፈጽሞ መለወጥ የነበረበት ። የአዋጁ መግቢያ በግልጽ እንደሚያስረዳው የተፈለገው የፊውዳሉን የመሬት ይዞታ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ መደምሰስና በቦታውም አዲስ ሥርዓት መተካት ነው ። ይህ አዲስ ሥርዓት ሰፋ ያለ የኤኮኖሚ ፣ የማኅበራዊና የፖለቲካ ውጤት ይኖረዋል ። ለትክክለኛ የመሬት ድልድል ፣ ለገጠሩ ሕዝብ አስተማማኝ ሥራ ለማስገኘት ፣ በፊውዳሉ ሥርዓት ታፍኖ የነበረውን የሰው ጉልበት ወደ ኢንዱስትሪው ክፍለ ኤኮኖሚ እንዲሰማራ ለማድረግ ፣ የራስን በራስ አስተዳደር ለመመስረትና በዚህም ማኅበራዊ ፍትሕን የሚያስገኝ ሥርዓት ለመገንባት መሠረት ይሆናል ።

እነዚህን ግቦች ለመምታት የተወሰዱት እርምጃዎች ቀጥተኛ ነበሩ ። ከዚህ እንደሚከተለውም ባጭሩ እንጠቅሳቸዋለን ።

አንደኛ ፣ ከየካቲት ፳፭ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ጀምሮ የገጠር መሬት ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ንብረት እንዲሆን ተደረገ ።[6] በሌላ አነጋገር ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የመሬት የግል ንብረትነት በመቅረቱ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የገጠርን መሬት ለመግዛት ፣ ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ መብት አይኖረውም ማለት ነው ። ሁለተኛ ፣ የገጠር መሬት በዘር ፣ በጾታ ፣ በቋንቋና በሃይማኖት ምንም ልዩነት ሳይደረግ በግሉ ለማረስ ፈቃደኛ ለሆነ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ በይዞታ እንዲከፋፈል ተደነገገ ። በይዞታ የሚመደበው መሬት በተቻለ መጠን እኩል እንዲሆን ከመደረጉም በላይ በማንኛቸውም ጊዜ ከፒ ሄክታር እንዳይበልጥና የይዞታው መጠን እንደአካባቢው ሁኔቴና እንደመሬቱ ለምነት እንዲወሰን ተደረገ[7] ። ሦስተኛ ፣ አዋጁን በሥራ የመተርጎሙ ተግባር በየፒ፱ ሄክታር ክልል ውስጥና እንዲሁም በወረዳና በአውራጃ ደረጃ ለተቋቋሙት የገበሬ ማህበራት ተሰጠ ።[8]

የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣው አዋጅ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ መገለጽ የማያስፈልጋቸውን በግል ባለሀብትነት ያልተያዙት የወል ርስትና የዘላን መሬቶችን የሚመለከቱ የሕግ አንቀጾችን ጨምሮ ልዩ ልዩ ዝርዝር ዘዴዎች አቅርቧል ።[9] ማህበራትን የማቋቋም ኃላፊነት ለእርሻና ሕዝብ ማስፈር ሚኒስቴር (የዛሬው ግብርና ሚኒስቴር) ከአገር አስተዳደር ሚኒስቴር ጋር በመተባበር እንዲሠራ የተሰጠ መሆኑን መጥቀሱ በቂ ነው ።[10]

የገበሬ ማህበራትን በሚመለከት ረገድ ሕገ መንግሥታዊ ትኩረት የሚሰጠውና ከገጠር መሬት አዋጅ ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው ሌላው ሕግ በታኅሣሥ ወር ፲፱፻፷፰ ዓ/ም የወጣው ፣ የገበሬዎች ማህበራት ማደራጃና ማጠናከሪያ አዋጅ ነው ።[11] አርእስቱ ራሱ እንደሚያመለክተው አዋጁ ለገበሬዎች ማህበራት ተጨማሪ ህልውና የሚሰጥና የሚያጠናክራቸው ነው ። አዋጁ በተጨማሪም የአገልግሎት የህብረት ሥራ ማህበራትን ፣ የአምራቾች የህብረት እርሻ ሥራ ማህበራትን ፣ የሴቶች ማህበራትንና የገበሬዎች ጥበቃ ጓዶችን ያቋቁማል ። ከዚህም በላይ አዋጁ ስለገበሬዎች ማህበራት የፍርድ ሸንጎዎች ሰፋ ባለ ሁኔታ ይዘረዝራል ። የገበሬዎች ማህበራት የፍርድ ሸንጎዎች የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ባደረገው አዋጅ ቀደም ብለው ተቋቁመዋል ። አዲስም ሆነ በቀጠሮ ላይ የነበሩትን የመሬት ክርክሮች የመዳኘቱ ተግባር ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ውጭ ተደርጎ በወረዳና በአውራጃ ደረጃ ለሚገኙት የገበሬ ማህበራት የፍርድ ሸንጎዎች ተሰጥቷል ።

የህብረት ሥራ ማህበራትን በየደረጃው ማቋቋምና ማስፋፋት የተፈለገው አርሶ አደሩ በጋራ ከመሥራት የሚመነጩትን ጥቅሞች የሚያገኝበትን የህብረተሰብ አዊ እርሻን መሠረት ለመጣል ታስቦ ነው ።[12] እንግዲህ የህብረት ሥራ ማህበራት ተቋም በማህበራዊ ፣ በኤኮኖሚና በፖለቲካ መስኮች ከፍተኛ ቦታ ይዞ ይገኛል ። በዓይነታቸው የሚለያዩትንና በልዩ ልዩ የሥልጣን ደረጃ የሚገኙትን የህብረት ሥራ ማህበራት የማስተዳደሩ ሥራ በአርሶ አደሩ እጅ የሚገኝ በመሆኑ እነዚህ ተቋሞች የኤኮኖሚ እድገት ማግኛ መንገዶች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ፣ የመማሪያ ፣ ራስን በራስ የማስተዳደሪያና የአካባቢን ችግር የመፍቻ ፣ በልማት እንቅስቃሴዎች የመሳተፊያ ትምህርት ቤቶች በመሆን በተጨማሪ የሚያገለግሉ መሆናቸውም መጠቀስ ይገባዋል ።

---

6 የገጠር መሬት አዋጅ አንቀጽ ፫ (፩-፪) ።
7 የገጠር መሬት አዋጅ አንቀጽ ፬ ።
8 የገጠር መሬት አዋጅ አንቀጽ ፭ እስከ ፲፭ ።
9 የገጠር መሬት አዋጅ አንቀጽ ፲፱ እስከ ፳፯ ።
10 የገጠር መሬት አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ።
11 የገበሬ ማህበራት ለማቋቋምና ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፴፭ የ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፭ኛ ዓመት ቁ ፲፭ ።
12 የገበሬ ማህበራት አዋጅ አንቀጽ ፮ እና ፯ ።

የሴቶች ማህበራት መቋቋም በአብዮቱ ውስጥ የሴቶች የተደራጀ ተሳትፎ ለህብረተሰብአዊ ድል ፍጹም አስ ፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ላይ የተመሠረተ ነው ። ሴቶች በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ ሆነው ቆይተዋል ። እንዲህ ያለው ሁኔታም መቃናት ብቻ ሳይሆን ጨርሶ መለወጥ አለ በት ። ሴቶች እንደወንዶች በአገራቱ የፖለቲካ ፣ የኤ ኮኖሚና የሶሻል እድገት ውስጥ በእኩል የመታየት መብት ሊኖራቸው ይገባል ። በሕግ የሰውነት መብት እንዲሁም ሰፋ ያለ ሥልጣንና ተግባር ያለው የሴቶች ማህበርን ማቋቋም በአንድ አብዮት ውስጥ ያለ የአንድ ማኅበራዊ ለውጥ ሂደት ዓይነተኛ ምልክቱ ነው ።

በመጨረሻም የገበሬዎች ማህበራት አዋጅ ገበሬዎ ችንና የገበሬዎችን ማህበራት ፣ እንዲሁም አብዮቱንና የወደፊት እድገቱንም ጭምር ለመጠበቅ የሚያስችሉ የጥበቃ ጓዶችን ያቋቁማል ። የጥበቃ ጓዶችም የየራሳ ቸውን አካባቢ የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው ። የጥበቃ ጓዶች በተጨማሪም የሕዝባዊ ጦር (ሚሊሺያ) አስኳል ናቸው ፤ ስለሆነም አብዮቱን ከውስጥና ከውጭ ጠላ ቶች የመጠበቅ ከፍተኛ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል ።

የከተማው መለወጥ ።

ሕገ መንግሥታዊ ትኩረት የሚሰጠው ሌላው ሕግ የከተማን ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ንብረት ለማ ድረግ ሐምሌ ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የወጣው አዋጅ ነው ።[13] ይህ አዋጅ የገጠርን መሬት ለሕዝብ ያደረገው አዋጅ ጓደ ኛና ማሟያ ነው ። የገጠር መሬት አዋጅ በፊውዳሉና በበዝባዥ የገጠር ግንኙነት ላይ ያስከተለውን መሠረ ታዊ ለውጥ ሁሉ ይህም አዋጅ በከተማው የፊውዳልና የበዝባዥ ግንኙነት ላይ አስከትለዋል ። አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ የከተማ ቦታ የመንግሥት ሀብት ሆኗል ።[14] ስለዚህም የከተማ ቦታ የግል ንብረትነቱ በማክተሙ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የከተማን ቦታ የመግ ዛት ፤ የመሸጥ ወይም የመለወጥ መብት እንዳይኖረው ያደርጋል ። አዋጁ በመሬት ክበርቴና ጭሰኛ መካከል የነበረውን ግንኙነት ያጠፋል ። በተጨማሪም አዋጁ የኢትዮጵያ ዜጎች ለሆኑ ሁሉ የመኖሪያ ቤቶችን መሥ ሪያ የሚሆን እስከ ፭፻ ካሬ ሜትር የሚደርስ የከተማ ቦታ ፣ እንዲሁም በሚፈለገው መጠን ለመሥሪያ ቤት የሚሆን የከተማ ቦታ የይዞታው መብት ለመስጠት እንዲቻል አግባብ ላለው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሥልጣን ይሰጣል ።[15]

ቤቶችን በሚመለከት ረገድ ማንኛውም ሰው ወይም ቤተሰብ ከአንድ መኖሪያ ቤት በላይ በባለቤትነት እን ዳይዝ ተከልክሎ ማናቸውም ትርፍ ቤቶች ሁሉ ወዲ ያውኑ ወደ መንግሥት እጅ እንዲዛወሩ ተደርገዋል ።[16] ከዚህም በላይ የመኖሪያና የመሥሪያ ቤቶችን ለማከ ራየት መብት ያለው አካል መንግሥት ብቻ መሆኑን የቤት ኪራዮችም በግል ጥቅም ላይ በተመሠረተው አኳኋን ሳይሆን በቴክኒካዊ ግምት ይወሰናሉ ።[17]

አዋጁ የከተማ ነዋሪዎች የህብረት ሥራ ማህበራትን ያቋቁማል ። ይህም በመስከረም ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ወደ ታወጀው የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ማጠናከሪያና የማዘጋጃ ቤቶች አዋጅ ያመጣናል ።[18] አዋጁ በየደረጃው የተቋቋሙትን የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት የሕግ ሰውነት እንዲኖራቸው ያደርጋል ። በተጨማሪም አዋጁ የከተማ ነዋሪዎችን ጉዳይ በማስ ፈጸም እንዲሁም አብዮቱን በመጠበቅና በማጠናከር ረገድ ለቀበሌ ፣ ለከፍተኛና ለአጠቃላይ የከተማ ነዋሪ ዎች ማህበራት ከፍ ያለ ሥልጣንና ተግባር ይሰጣል ። የከተማ ነዋሪዎች ማህበራትም የፖሊሲ አውጭ ኮሚቴ ዎች የሕዝብ ደህንነት ኮሚቴዎችና የፍርድ ሸንጎዎችን ያቋቁማሉ ።[19] የፖሊሲ አውጭ ኮሚቴዎች የከተማ ነዋሪዎችንና የአብዮቱን ጥቅም ለመጠበቅና ለማራመድ የሚያስችሉ አጠቃላይ የአስተዳደር ሥልጣኖች አሏ ቸው ። የሕዝብ ደህንነት ኮሚቴዎች የየአካባቢያቸውን ጸጥታ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የሕዝባዊ ጦር አባሎች ሊመለመሉ የሚችሉባቸው ምንጮች በመሆን ያገለ ግላሉ ። የፍርድ ሸንጎዎች የከተማ ቦታና ቤቶችን በሚ መለከት ረገድ የሚነሱ ክርክሮችን እንዲሁም አንስተኛ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችንና ቀላል ጥፋቶችን በዳኝነት ያያሉ ።[20] ጉዳዩ የሚመለከተው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ከአጠቃላይ የማዘጋጃ ቤት ባለሥልጣኖች ጋር በመተባበር ለከተማ ነዋሪዎች ማህበራት ሥራ አስፈ ላጊ መመሪያዎችን ይሰጣል ፤ ሥራቸውንም ይቆጣጠ ራል ።

የሠራተኛ ጉዳይን በሚመለከት ረገድ የተደረገ ለውጥ ።

ልንመለከተው የሚገባ የመጨረሻው መሠረታዊ ሕግ በኅዳር ወር ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የወጣው የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ነው ።[21] ይህ አዋጅ የኅብረተሰብአዊ የሶሻልና የኤኮኖሚ ዋና ዋና መሠረታዊ አሳቦችን ያረጋግጣል ፤ የሠራተኛውንም መብቶችና የሥራ ሁኔታዎች በሚ ገባ ለመጠበቅ የሚያስችሉትን ሕጋዊ መዋቅሮች ይፈ ጥራል ። የአዋጁ መግቢያ "ሥራ ለሰው ልጅ ክብሩ ነው" በማለት መሠረታዊ መመሪያ ደንግጎልናል ፤ እንዲሁም በማያወላውል አኳኋን ማንኛውም ግለሰብ "የመሥራት መብትም ሆነ ግዴታ" እንዳለው ያስገ ነዝባል ። አዋጁ ሠራተኛውን የምርት ሁሉ ምንጭና መሠረት አድርጎ ይመለከተዋል ፤ ስለዚህም ክብዝበዛ ነፃ በመውጣት ደኅንነቱንና ጤንነቱን በትክክል በመ ጠበቅ ፣ እንዲሁም ትክክለኛ ክፍያ ማግኘቱን በማረ

13 የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቁ ፬፮ ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፭ኛ ዓመት ቁጥር ፬፩ ።
14 የከተማ ቦታ አዋጅ አንቀጽ ፫ ።
15 የከተማ ቦታ አዋጅ አንቀጽ ፭ ።
16 የከተማ ቦታ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ ።
17 የከተማ ቦታ አዋጅ አንቀጽ ፳ ።
18 የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት ማጠናከሪያና የማዘጋጃ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ፭፻፱ የ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፭ኛ ዓመት ቁ ፭ ።
19 የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት አዋጅ አንቀጽ ፲ ።
20 የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት አዋጅ አንቀጽ ፲፭ ።
21 የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፭፱ የ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፭ኛ ዓመት ቁ ፲፩ ።

ጋገጥ የሠራተኛውን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ወሳኝ ነው ብሎ ይቆጥራል ። በተጨማሪም ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በዘር ፣ በጎሣ ፣ በጾታና በሃይማኖት ምንም ልዩነት ሳይደረግ እኩል የሥራ ዕድል እንደሚሰጥ ይደነግጋል ። ይህንንም ለማድረግ አዋጁ የሥራ ዕድሎችን በማስፋፋትና የሥራ ፈትነት ችግሮችን በማስወገድ ዓላማ የተመሠረተ ስለ አገሪቱ የሰው ኃይል መጠንና ሙሉ አጠቃቀም ጥናት ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን ያምናል ።

አዋጁ በትክክል እንደሚያስረዳው ፣ ህብረተሰብአዊ ነትን መገንባትና ይህንንም ውጤት ለማስገኘት የሠራተኛውን ንቃተ ሕሊና ማሳደግ ፣ እንዲሁም ሠራተኛውን በአገሪቱ ዕድገት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ነው ። አዋጁ የሚደነግጋቸው መሠረታዊ ዓላማዎች ሊገኙ የሚችሉት ሠራተኞች በየሙያ ማኅበሮቻቸው ሲደራጁና የህብረተሰባዊ መመሪያዎችን መስመር በመከተል ተግባሮቻቸውን በሥነ ሥርዓት ሲከታተሉ ብቻ ነው ። የሞያ ማህበራት በልዩ ልዩ ደረጃ ሥልጣን ተሰጥቶአቸው የተቋቋሙ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ናቸው ። ሠራተኞች በአዋጁ እንደ ተገለጸው የሠራተኛ ማህበር አባላት መሆን ይችላሉ ። በአንድ ድርጅት ውስጥ ከሕ ያላነሱ ሠራተኞች እስካሉ ድረስ በዚህ ድርጅት ውስጥ አንድ የሙያ ማህበር ማቋቋም ይቻላል ። ከሕ በታች ሠራተኞች ባሏቸው ትናንሽ ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ ሠራተኞች ደግሞ ከሌሎች በተመሳሳይ ድርጅቶች ውስጥ ከሚሠሩ ሠራተኞች ጋር በአንድነት ሆነው ጠቅላላ ማህበርን ሊያቋቁሙ ይችላሉ ። እነዚህ በመጀመሪያ ደረጃ የሚገኙ ጠቅላላ ማህበራትና የሙያ ማህበራት በአሁኑ ጊዜ ቁጥራቸው ዘጠኝ የደረሰውን የኢንዱስትሪ ማህበራት እንዲያቋቁሙ በየኤኮኖሚ የሥራ ዘርፋቸው ይመደባሉ ። በመጨረሻም ዘጠኙ የኢንዱስትሪ ማህበራት በአንድነት ሆነው አገር አቀፍ የሆነውን መላው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር ያቋቁማሉ ። መላው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት ሠራተኞች ሁሉ ከመወከሉም በላይ በዓለም አቀፍ የሠራተኞች ማህበራትም ውስጥ ወካይና ተጠሪ ይሆናል ።[22]

አዋጁ ሠራተኞች በአስተዳደር ሥራ እንዲሳተፉ ፣ የሥራ ቅልጥፍና እንዲጨምርና ሰላምና መተሳሰብ የተሞላበት የሥራ ግንኙነት እንዲፈጠር ባሉት ዓላማዎች መሠረት እነዚህን ዓላማዎች ከግቡ ለማድረስ የሚያስችሉትን የረቀቀ የሕግ ዘዴንና የተለያዩ ተቋሞችን ይፈጥራል ። እነዚህም ቁጥራቸው ከአሥር የማያንስ ሠራተኞች በሚገኙበት በእያንዳንዱ ድርጅት ውስጥ ከድርጅቱና ከሠራተኛው እኩል በኩል ተወካዮች ተገኝተውበት የሚቋቋመውን የሥራ ክርክር ኮሚቴን ይጨምራሉ ። እንደዚህ ያለው የሥራ ክርክር ኮሚቴ የግል የሥራ ክርክርን በሚመለከት ረገድ በመጀመሪያ ደረጃ የማየት ሥልጣን ያለው ሲሆን የውል የሥራ ክርክርን በሚመለከት ረገድ ጉዳዩ በስምምነት እንዲፈጸም የማድረግ ሚና ይጫወታል ።[23] አዋጁ በሌሎች ደረጃዎች የሠራተኛን ጉዳይ የሚመለከቱ ችሎቶች በአውራጃና በከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ ያቋቁማል ።[24] በተጨማሪም አዋጁ ስለ መሠረታዊ የሥራ ሁኔታዎች ፣ ስለሀብረት ስምምነቶች ፣ ስለ ለማጅ ሠራተኛ የሥራ ውልና አቀጣጠር እንዲሁም ተገቢ ስላልሆኑ የሥራ አፈጻጸሞች በዝርዝር ይደነግጋል ።

የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የሥራንና የሠራተኛን ክቡርነት በማወጁና በሥራ አማካይነት ህብረተሰብአዊ ነትን ለመገንባት የሚያስችሉ ዓላማዎችን በመያዙ በሕጎች ዓለም ውስጥ ሕገ መንግሥታዊ ትኩረት ይሰጠዋል ፤ ስለሆነም እንደ ሕገ መንግሥታዊ ደንብ ሊቆጠር ይችላል ።

ከመደንገግ በሥራ ወደ መተርጎም ።

ከዚህ በላይ የመረመርናቸው መሠረታዊ ሕጎች ሁሉ ሕገ መንግሥታዊ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው ። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በሕግ (በአፌሴል) የጸደቀ (de jure) ሕገ መንግሥት በሚወጣበት ጊዜ እዚህ ላይ የተነጋገርንባቸውን ሕጎች መሠረተ አሳብ አዝሎ የሚወጣና በከፍተኛ ጥንቃቄም የሚያስጠብቃቸውን ይሆናል ። ከዚህም በላይ እነዚህ መሠረታዊ ሕጎች ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በጣም ጠቃሚ የሆነ "የሕግ አብዮት" ምልክት መሆናቸው ግልጽ ነው ። ይሁን እንጂ በጽሑፍ የሚገኙትን ግቦች በሥራ ለመተርጎም የሚያስችሉ ዘዴዎችን የማውጣቱ አስፈላጊነት መፍትሔ የሚያሻው አሁንም ያለና ወደፊትም ያለማቋረጥ ጥረት የምናደርግበት ተግባር ነው ። በሌላ አነጋገር በጽሑፍ የቀረቡት ዝርዝር ጉዳዮች ሁሉ ዘለቄታው በሥራ መተርጎም ይኖርባቸዋል ማለት ነው ። ዓላማዎችንና መመሪያዎች አሳቦችን በሥራ መተርጎም ቀላል ተግባር አይደለም ። አስቸጋሪ ጉዳዮችን ውጤት ለማስገኘት ፍቱን በሆነ መንገድ ፕሮብሌሞችን ተንትኖ ማየትና ውሳኔ መስጠት ያስፈልጋል ። ከዚህም በላይ እነዚህ የፕሮብሌም ትንተናዎች ፣ የሕግ አስፈጻሚው የመንግሥት ዘርፍ በልዩ ልዩ የሥልጣን ደረጃዎች ዝርዝር ደንቦች እንዲያወጣላቸው ያስፈልጋል ። ይህም ማለት ባጠቃላይ ሁኔታ የሚገኙትን ደንቦች ደምና ሕይወት መስጠት ይሆናል ። እነዚህም ብዙውን ጊዜ የሕግ ማስታወቂያ እየተባሉ ሊታወጁ ይችላሉ ። ከዚህም በኋላ ለእነዚህ ደንቦች ዝርዝር የሥራ ፕሮግራምና መመሪያ ሥነ ሥርዓት በማውጣት ዓላማዎችን በሥራ ለመተርጎም ይቻላል ። ከዚህም በላይ ይህን የመሰለው በሥራ የመተርጎሙ ተግባር ተፈላጊውን ውጤት የማያስገኙትን ፣ እንደገና መመርመር የሚያስፈልጋቸውን ችግር አዘል ሕጎች ካሉ ለመጠቆም ያስችላል ። እንግዲህ በሥራ የማዋሉ ተግባር ለሕጎች ይበልጥ መሻሻል ጠቃሚ መሣሪያ የሚሆኑ መረጃዎችን በመስጠት ሊያገለግል ይችላል ። ለዚህም አግባብ ያለው ምርምር የማያቋርጥ ሂደት በሚታይባቸው በጽሑፍ ባሉት ደንቦችና ሁኔታዎች ላይ ባጠቃላይ በማተኮር ወደ ተረጋገጠ ውሳኔና ውጤት ሊደርስ ይችላል ።

---

22 የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ ፵፱ እስከ ፶፪ ።

23 የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ ፫፱ እስከ ፵፰ ።

24 የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ እስከ ፩፪ ።

የኢትዮጵያን የመወለድ ሕግ በሚመለከት የተደረገ ተጨማሪ * ጥናት

ሕግ ፋካልቲ
Faculty of Law
ADDIS ABABA UNIVERSITY

ለልዩ ልዩ ሕጐች አጥኝ ዓለም አቀፍ አካዳሚ

ዘጠነኛ ጠቅላላ ጉባኤ በጆርጅ ክሽችኖቪች* የቀረበ

የልዩ ልዩ አገር ሕጎች አጥኝ ዓለም አቀፍ አካዳሚ

ለዘጠነኛው ዓለም አቀፍ አካዳሚ ጠቅላላ ጉባኤ የቀረበውን ጽሑፍ ከመመልከታችን በፊት ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ፋኩልቲ ከአካዳሚው ጋር ስለ አደረጋቸው ግንኙነቶች አጭር መግቢያ መስጠቱ ተገቢ ይመስለኛል ።

የአካዳሚው ጠቅላላ ጉባኤዎች በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ይደረጋሉ ። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ፤

እ ኤ አ በ፲፱፻፷፪ ዓ/ም ሐምቡርግ ላይ ተደርጎ በነበረው በስድስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ፣ የኢትዮጵያን ፓርላማ የተግባር ክልሎች (ይህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ጥናቶች መጽሔት ፫ኛ ቮልዩም ገጽ ፭፭ ላይ በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም እ ኤ አ ወጥቷል) ፤

እ ኤ አ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ኡፕሳላ ላይ ተደርጎ በነበረው በሰባተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ፣ በኢትዮጵያ ከጋብቻ ውጭ መወለድን የሚደነግጉ ሕጎችን (ይህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት ፫ኛ ቮልዩም ገጽ ፭፻፲፭ ላይ በ፲፱፻፷፮ እ ኤ አ ቀርቧል) ፤

እ ኤ አ በ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ፒስካራ ላይ ተደርጎ በነበረው በስምንተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ፣ በኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ ርትዕ ስላለው ሚና (ይህ ጽሑፍ በአፍሪቃ የሕግ መጽሔት ፫ኛ ቮልዩም ገጽ ፭፻፸፭ ላይ በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም እ ኤ አ ወጥቷል) የሚያወሱ ሪፖርቶችን በማ ቅረብ የሕግ ፋኩልቲውን ወክዬ ተሳትፌአለሁ ።

እንዲሁም አካዳሚው እ ኤ አ በ፲፱፻፸፬ ዓ/ም ቴህራን ላይ ባደረገው በዘጠነኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ፋኩልቲው በዶ/ር ፋሲል ናሆም አማካይነት ሦስት ጽሑፎችን በማቅረብ የተሳተፈ ሲሆን ፣ በመጨረሻም እ ኤ አ በ፲፱፻፸ ዓ/ም ቡዳፔስት ላይ ተደርጎ በነበረው በአሥረኛው ጠቅላላ ጉባኤ እኔ ተገኝቼ አንድ በእኔ የተጻፈና ሌላ አቶ የኔካአል የኋላ እሸት በተባሉ የሕግ ባለሙያ የተዘጋጀ ጽሑፍ በማቅረብ ተሳትፌአለሁ ።

ሪፖርቶች ሁሉ በአካዳሚው መዝገብ ቤት ውስጥ በሚገባ የተቀመጡ ሲሆን ፣ ዝርዝራቸውም በአካዳሚው እትሞች ውስጥ ተጠቅሶአል ።

አካዳሚው የሚያወጣቸውን እትሞች መከታተልና ከአካዳሚው ጋር ግንኙነት ማድረግ ፣ ሕጎቻቸው ከተ ለያዩ የሕግ ሥርዓቶች ተቀናጅተው ለተነደፉና በአንድ በተወሰነ የሕግ ሥርዓት (ለምሳሌ በእንግሊዝ ወይም በፈረንሳይ) አቅጣጫ የተቀየሰ የሕግ ሥርዓት ለሌላቸው የአፍሪቃ አገሮች የተለየ ጠቃሚነት አለው ። የኢትዮ ጵያ የሕግ ሥርዓት ከተለያዩ የሕግ ሥርዓቶች መመን ጨቱ ጎልቶ የሚታይና በማደግም ላይ ያለ መሆኑ ፣ ከነዚህ አገሮች መካከል ኢትዮጵያን አንዲና ዋነኛዋ ያደርጋታል ። አካዳሚው በጠቅላጮቹና በሪፖርቶቹ አማካይነት የሚያደርጋቸው ጥናቶች እና ምርምሮች ይህን በአገር የማይወሰነውን የሕግ ሳይንስ እድገት ያፋጥኑታል ።

ባለፉት ሁለት ጉባኤዎች ካቀረብሁዋቸው ጽሑፎች አንደኛው በዚህ እትም የሚወጣ ሲሆን ሌላው ደግሞ በሚቀጥለው እትም ይወጣል ። ሁለቱም ሪፖርቶች ወቅታዊ ርዕሶችን የሚመለከቱ ናቸው ። በቅርቡ ያሻሻ ልሁት አንደኛው ጽሑፍ በፍርድ ቤቶች አካባቢም ሆነ ከፍርድ ቤቶች ውጭ አከራካሪ የሆነውን መወለድን የሚመለከት ነው ። ይህ ጽሑፍ አዲስ አቅጣጫዎችን በሚጠቁም እ ኤ አ በ፲፱፻፸፱ ዓ/ም በተዘጋጀው ማክ ያና ከተወሰነ ዘግየት ባለ አስተያየት የተሰጠበት ፍርድ የተደገፈ ነው ። እ ኤ አ በ፲፱፻፸፰ ዓ/ም የቀረበው ሁለ ተኛው ጽሑፍ ደግሞ ከኤኮኖሚ እድገት ጋር አብሮ የሚመጣውንና አዲስ የሕግ ችግሮች የሚያስነሳውን በተመረቱ ዕቃዎች መነሾ የሚመጣ ኃላፊነትን የሚመ ለከት ነው ።

---

* የሕግ ፕሮፌሰር ፣ ሕግ ፋኩልቲ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

አሁን የማቀርበው ሪፖርት መሠረተ ሐሳብ ከዚህ ቀደም በሰባተኛው ጠቅላላ ጉባኤ "ከጋብቻ ውጭ መወለድን የሚደነግጉ ሕጎችን" በሚመለከት ከተወ ያየንበት ርእስ ጋር ይዶራረባል ። በሰባተኛው ጠቅላላ ጉባኤ የተገኘሁት እኔው በርእሱ[1] ላይ በወቅቱ ሰፋ ያለ ሪፖርት ያቀረብሁ ስለሆነ ፣ መደጋገም እንዳይሆን[2] በማለት በዚህ ጽሑፍ ርእሱን ከተለየ አቅጣጫ እመለ ከተዋለሁ ።

ሌላው ችግር የርዕሱን ስያሜ የሚመለከት ነው ። በኢትዮጵያ ሕግ በሰፊው የሚሠራበት "አባትነትና እናትነት የሚታወቅበት መንገድ" (ሕጋዊ ግምት) በጋ ብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ መወለድን ለማስረዳት ያገ ለግላል ። የመወለድን ማስረጃ የሚመለከተው ክፍል ድንጋጌዎችም ቢሆኑ ፣ ለሁሉም ልጆች በተመሳሳይነት የሚያገለግሉ ናቸው ።[3] የመወለድ ውጤቶችም እንደ ዚሁ በማንኛውም ሁኔታዎች ተመሳሳይ ናቸው ። ስለ ሆነም ልጆችን በመከፋፈል በሰባተኛው ጠቅላላ ጉባኤ "የተፍጥሮ ልጆች" መባሉ ወይም በዘጠነኛው ጠቅላላ ጉባኤ "ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆች" መባሉ ፣ ለኢትዮጵያ ሕግ ምንም ልዩነት አያስካከትልም ። በዚህ ምክንያት በዋና ሪፖርተሩ[4] የተነደፈውን የሪፖርቱን አቀራረብ ስልትና የሪፖርቱን ርእስ ለመለወጥ ተገድ ጀለሁ ።

በመሠረቱ ልጅነት ስለሚያስከትላቸው ውጤቶች ከመነጋገሩ በፊት የማን ልጅ መሆን ስለሚረጋገጥባቸው ሁኔታዎች መነጋገሩን ማስቀደም ያስፈልጋል ። እንደ ዚሁም የእናትነት መረጋገጥ በዚሁ ላይ የሚመሠረ ተውን የአባትነትን መረጋገጥ ይቀድማል ። የዚህ ጽሁፍ አቀራረብም በዚህ መሠረት የተዘጋጀ ነው ። "መወለድ" የሚለውን ቃል የምንጠቀመው በልጅና በእናቱ ወይም በአባቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ወይም መተሳሰር ለማመልከት ሲሆን ፣ "አባትነትና እናትነት" የሚታወቅበት መንገድ የሚለውን ደግሞ የመወለድን ግንኙነቶች (መተሳሰሮች) የሚፈጥሩትን ወይም የሚ መሠርቱትን ሁኔታ/ዎች ለማመልከት ነው ።

ሀ/ እናትነት

በዚህ ርእስ የተመለከተውን ጉዳይ (፩) አመሠራረ ቱን (፪) የማያከራክር ማስረጃን (፫) አከራካሪ ማስረ ጃንና (፬) ክርክርን በተከታታይ እንመለከታለን ።

፩/ አመሠራረት

"በመወለድ ብቻ እናትነትን ለማስረዳት ይቻላል" (አንቀጽ ፯፻፴፱)[5]። በእናትና በልጅ መካከል ያለው ግንኙነት አንድ የአገባችም ሆነ ያላገባች ሴት ልጅ በመ ውለዷ ብቻ ይመሠረታል ። እዚህ ላይ ወሳኙ ጉዳይ ልጁ ከስዋ መወለዱ ብቻ ነው ።

የእናትዬዋ ስምምነት ወይም እናትነቷን መቀበል በኢትዮጵያ ሕግ አስፈላጊ አይደለም (በአንዳንድ አገ ሮች ሕጎች ከጋብቻ ውጭ የተወለደን ልጅ በሚመለ ከት እናትነትን በሙሉ ለማስረዳት የእናትዮዋ ስም ምነት ወይም እናትነቷን መቀበል አስፈላጊ ነው[6]) ።

፪/ የማያከራክር[7] የልጅነት ማስረጃ

አስተማማኝ የሆነ የልደት ማረጋገጫ መኖር ለግልም ሆነ ለአስተዳደር ሥራ ጠቃሚ ነው ። በዚህም ምክን ያት የፍትሐ ብሔር ሕጋችን እናትነት እና አባትነት በሕግ እንደታዘዘው ስለመወለድ ማስታወቂያ ሰነዋ (አንቀጽ ፭፻፭-፪) "በቅድሚያ በተዘጋጀ[8]" ለዚሁ ተግ ባር በተሾመ ሹም (አንቀጽ ፵፮ እና ተከታዮቹ) አማካ ይነት በሕዝብ ክብር መዝገብ (አንቀጽ ፲፭ እና ተከታ ዮቹ) በተመዘገበ የልደት ምስክር ወረቀት[9] (አንቀጽ ፭፻፭፱) መረጋገጥ እንዳለበት ይደነግጋል ። ይሁን እንጂ እነዚህና ሌሎች የሕዝብ ክብር መዝገብን የሚመለከቱ የሕግ አንቀጾች ፣ ልደት[10] መረጋገጥ ያለበት (በቅድ ሚያ ያልተዘጋጁ) "የታወቁ ጽሑፎችን" (አንቀጽ ፫ሺ፫፻፭፭-፪) በማቅረብ መሆኑን በሚገልጸው የመሸ ጋገሪያ አንቀጽ (አንቀጽ ፫ሺ፫፻፭፭-፭) ላልተወሰነ ጊዜ ታግዶዋል[11] ። ይሁን እንጂ እነዚህን የመሰሉ የታወቁ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ተግባር የሰለጠኑ ባለሙያዎች ስለሌሉ[12] ፣ ይህም አንቀጽ በሥራ ሊተረጐም አይ ችልም ። በዚህ ተግባር የሰለጠኑ ባለሙያዎች ቢኖሩም ኖሮ እንኳን ፣ ቋሚ የሆነውና ያልታገደው የሕግ አን

• ለዘጠነኛው ጉባኤ ቀርቦ የነበረው ይህ ሪፖርት እዚህ መጽሔት ላይ የቀረበው በመጠኑ ተሻሽሎና አዲስ ሁኔታዎችን የሚመለከት ማከያ ተጨ ምሮበት ነው ።

1 ይህ ሪፖርት "የቅድሞው ሪፖርት" ተብሎ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሚጠቀስ ሲሆን ይዘቱም ከጉባኤው ወዲህ ከተጨመረበት ማከያ ጋር እ ኤ አ በ፲፱፻፷፮ ዓ/ም በኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት ፫ኛ ቮልዩም ከገጽ 511-523 ድረስ ታትሞ ወጥቷል ። እንዲሁም በዚህ ሪፖርት ላይ የተጨመረበት ማከያ በዚህ ጽሑፍ ማጠቃለያ ላይ ተጨምሮአል ።

2 በዚህ ርዕስ ላይ አዲስ ሕግ አልወጣም ።

3 በመድፈር ሥራ ወይም በመዋለፍ የሚፈጠሩ ሁኔታዎችን አይጨምርም (ከታች ይመልከቱ) ።

4 ፕሮፌሰር ጋብርኤል ካንቴሮ ከ ቨላደልድ ዩኒቨርስቲ ።

5 እንዳይደለ ካልተገለጸ በስተቀር "አንቀጽ" ሲባል የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ማለት ነው ።

6 እ ኤ አ በ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ለሰባተኛው ጠቅላላ ጉባኤ በአውፊሊያን ጆንሴኮ የተረበውን አጠቃላይ ሪፖርት ገጽ ፰ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር ፪ ይመልከቱ ።

7 "የማያከራክር" ሲባል "አከራካሪ ከሆኑት ውጭ" ያሉትን ለማለት ነው ። "ስለሚያከራክሩ" የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 17 እና የቀድሞውን ሪፖርት ገጽ 519 ይመልከቱ ።

8 የማስረጃው አስፈላጊነት ከመፈጠሩ በፊት የተዘጋጀ ።

9 "አክት ደ ኔሳንስ" ።

10 የጋብቻና የሞትም እንደዚሁ ።

11 በነጋሪት ጋዜጣ ትእዛዝ ታትሞ እስካልወጣ ድረስ በሥራ ላይ ሊውሉ አይችሉም ።

12 ሴሎችን ሰዎች ስለመሾም ለአገር አስተዳደር ሚኒስቴር የተሰጠው አማራጭ (አንቀጽ ፫ሺ፫፻፭፭-፪) ሥራ ላይ የዋለ አይመስልም ። ከጣሊያን ወረራ የተነሳ ባለሙያዎች ኤርትራ ውስጥ በመጠኑ ያሉ ይመስላል ። እ ኤ አ በ፲፱፻፶፭ ዓ/ም "የማዘጋጃ ቤቶች አዋጅ" መሠረት ስለሚደረጉት የመወ ለድ ምዝገባዎች ሕጋዊ ተቀባይነት የቀድሞውን ሪፖርት የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር ፷፪ ይመልከቱ ።

ቀጽ (አንቀጽ ፯፻፫) ፥ የልደት የምስክር ወረቀት በሌ ለበት ጊዜ መወለድ መረጋገጥ ያለበት የታወቁ ጽሑ ፎችን በማቅረብ ሳይሆን "የልጅነት ሁኔታ" መኖሩን በማሳየት ነው ስለሚልና ይህም አንቀጽ ከመሸጋገሪ ያው አንቀጽ[13] ቅድሚያ ያለው ስለሆነ ፥ የታወቁ ጽሑ ፎችን በማቅረብም ቢሆን መወለድን ማረጋገጥ አይ ቻልም ማለት ነው ። ይህ አመለካከት ከፍርድ ቤቶች አሠራር ጋር ይመሳሰላል ።

በብዙ የውጭ አገሮች ሕጎች እናትነት የሚረጋገጠው በቅድሚያ የተዘጋጀውን የልጁን የልደት የምስክር ወረቀት በማቅረብ ነው ። ይሁን እንጂ ከላይ በተጠቆ ሙት ምክንያቶች የተነሳ በኢትዮጵያ ብዙኛና ትክክ ለኛ የሆነው የማያከራክር የእናትነት (የአባትነትም እንደዚሁ ፥ ከታች ይመልከቱ) ማረጋገጫ ዘዴ ፥ የልጅ ነት ሁኔታ መኖር ይመስላል ። ልጁ በወላጁ ፥ በወላጁ ዘመዶችና በሕብረተሰቡ እንደወላጁ ልጅ ተደርጎ መያዙን ማሳየት (በአራት ምስክሮች) ያስፈልጋል (አን ቀጽ ፯፻፫-፪) ። እናትነትን በሚመለከት ረገድ ይህ የማያከራክር የልጅነት ማስረጃ በሚገባ ይሠራል ።

"በሁኔታ መኖር" እናትነት የሚረጋገጠው በመሠ ረቱ በቃልና በተዘዋዋሪ መንገድ[14] ቢሆንም ፤ ይህንን "የሁኔታ መኖር" መቃወም የሚቻለው የሕጋዊ ሁኔታ ዎችን[15] አለመሟላት የሚያስረዱ አራት ምስክሮች አቅርቦ በማስመስከር ብቻ ነው (አንቀጽ ፯፻፫፩-፪) ። እናትነትን በሚመለከት ተቃውሞ የቀረበበት አንድም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳይ[16] አላጋጠመኝም ።

፫/ አከራካሪ[17] ማስረጃ

እንደላይኛው ሁሉ በዚህም ረገድ እናትነትን በመ ቃወም[18] የቀረቡ ክርክሮች ያላጋጠሙኝ ቢሆንም ፥ ከአንቀጽ ፯፻፫፪-፯፻፫፫[19] ድረስ የተመለከቱትን ተቃ ውሞ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑትን ሕጋዊ ሁኔታዎች መጥቀሱ ተገቢ ነው ።

የእናትነትን ሁኔታ መኖር "ለመጠየቅ" ክስ ሊቀርብ የሚችለው ጠያቂው የሁኔታው መኖር የሌለው እንደሆነ ወይም በዚሁ ሁኔታ መኖር ላይ ሕጋዊ ክርክር የተነ ሳበት እንደሆነ ብቻ ነው (ከላይ ይመልከቱ)[20] ። ከዚ ህም በላይ ጥያቄውን ተቀባይ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መኖራቸውን አይቶ ፍርድ ቤት በቅድሚያ ፈቃድ ካል ሰጠ በስተቀር ፤ ክሱ ሊመሠረት አይችልም ። እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ከተሟሉ ፥ "ልደቱን" እና "ማንነ ቱን" (በተወለደው ልጅና በጠያቂው መካከል) የሚ ያስረዱት ወይም የሚያመለክቱት ተጨባጭ ሁኔታዎች ፍርድ ቤቱን ሊያሳምኑ በሚችሉ በማናቸውም ዘዴዎች ሊረጋገጡ ይችላሉ ።[21]

፬/ ክርክር

በአንቀጽ ፯፻፫፬ መሠረት በቅድሚያ የፍርድ ቤት ፈቃድ ከተሰጠ (የሁኔታ መኖር ሳይኖር በአከራካሪ ማስረጃ ጊዜ እንደሚሰጠው ዓይነት)[22] ፥ አለ ቸብሎ በሚታመን የእናትነት ሁኔታ ላይ በማንም ጉዳዩ በሚ ያገባው ሰው (አንቀጽ ፯፻፫፭) ክርክር ሊቀርብ ይችላል ። ፈቃዱ ከተገኘ በኋላ ፥ ተከራካሪው[23] የሁኔታው መኖር ባለው ሰው[24] ላይ ይህን ሁኔታ ሊፈጥሩ የሚችሉት ተጨባጭ ሁኔታዎች (ልደት ፥ ማንነት) ያለመኖራቸ ውን በማናቸውም ዘዴዎች ሊያረጋግጥ ይችላል ።

በእናትነት ሁኔታ መኖር ላይ (ማለትም ተከሳሽ ሁኔታውን ለማግኘት ስለሚኖረው "መብት") በከ ፍተኛው ፍርድ ቤት የቀረበ ክርክር አላጋጠመኝም ። በአጠቃላይ አነጋገር ፥ እናትነት በክርክር ደረጃ የሚያ ስከትላቸው ችግሮች ቢኖሩ በጣም ጥቂቶች ናቸው ።

ለ/ አባትነት

በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች[25] እናት ነትን ከማረጋገጥ ይልቅ አባትነትን ማረጋገጥ የበለጠ ያስቸግራል ። ይኸንኑ የሚደነግገው ሕግ ግልጽ አይ ደለም ፤ ይኸን በሚመለከት ረገድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች ብዙ ከመሆናቸውም በላይ የተሰጡት ፍርዶችም አብዛኛውን ጊዜ አከራካሪና በሕግ አተረጓ ጐማቸው የተለያዩ ናቸው ። ከዚህም በላይ ራሱ ግልጽ ያልሆነው የውርስ ሕግ ጉዳይ አብሮ ይነሳል ።

---

13 ያልተስተካከለው አጻጻፍ ከችኮላ የተነሳ የመጣ ይመስላል ። ስለዚሁ "ስለኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ አንዳንድ ጥያቄዎች" የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት ቮልዩም ፱ ገጽ 205 እና የቤተሰብ ሕግ ጥያቄዎች ቁጥር 245 (ሕግ ፋኩልቲ ፤ አዲስ አበባ) በፕሮፌሰር ክሽችቢች ይመልከቱ ።

14 በቅድሚያ የተዘጋጀ የልደት የምስክር ወረቀትም ሆነ ሀ ከ ለ ለመወለዱ ቀጥተኛ ማስረጃ አስፈላጊ አይደለም (ከላይ ስለአመሠራረት የተጻፈውን ይመልከቱ) ።

15 በተለመደው ሁኔታ እንደልጅ ተደርጎ መያዙና እንደልጅ ተደርጎ መታወቁ ። በኢትዮጵያ የቤተሰብ ስም ባለመኖሩ የመጀመሪያው የተለመደ ሁኔታ ፥ ስም ፥ ለኢትዮጵያ ሕግ አሠራር አያገለግልም ።

16 ሁሉም በፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች በሕግ ፋኩልቲ የማይታተሙ ወይም የማይመዘገቡ መሆናቸውን ማወቅ ይገባል ።

17 "አከራካሪ" ሲባል በልጅነት ሁኔታ መኖር ሳይሆን በሌሎች ቀዳሚ ሁኔታዎች የእናትና የልጅ ግንኙነት መኖሩን በማረጋገጥ የሚቀርብን ክስ ለማመልከት ነው ።

18 በፈረንሳይኛ "አክሲዮን አን ሪሰርሽ ደ ማተርኔቴ"

19 ከትርጉም ስህተት የተነሳ የእንግሊዝኛው ቅጅ በአመልካችነት ሊቀርቡ የሚችሉ ልጆች ብቻ እንደሆኑ ያስመስላል ። እናትም (አባትም) ሊሆኑ እንደሚችሉ አንቀጽ ፯፻፫፭ (፪) ያመለክታል ።

20 ይህ አመለካከት ትክክል ነው ። በንብረት ሕግም ሆነ (ተንቀሳቃሽ ንብረት አንቀጽ ፭ሺ፭፻፶፫) በመውለድ ሕግ (አንቀጽ ፯፻፫) ፥ ባለአጅ ወይም ባለ ይዞታ የሆነው ሰው "መጠየቅ" ሳያስፈልገው ፥ ባለአጅ ወይም ባለይዞታ መሆኑ ብቻ ባለመብት ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው ።

21 በዚህ ረገድ "ስለባለሥልጣን ጽሑፍ" አሰጣጥ በአንቀጽ ፯፻፫፪ የተመለከተው ፥ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 12 በሚያብራራው የዚህ ጽሑፍ ክፍል በቀረበው ማብራሪያ ምክንያት ሊሠራ አይችልም ።

22 ከላይ ይመልከቱ ።

23 ለተጨማሪ ማብራሪያ የቀድሞውን ሪፖርት ገጽ 521 ይመልከቱ ።

24 እዚህ ላይ ክርክር የሚቀርብበት የእናትነት ሁኔታ በመኖሩ ላይ ሳይሆን በዚህ ሁኔታ መኖር መብት ላይ መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው ።

25 ስለ አባትነት ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ለመሆን አለመቻሉ በሚገባ የሚታወቅ ከመሆኑም ሌላ ።

እናትነትን ለማስረዳት እንዳደረግነው ሁሉ አሁንም ፤ (፩) አመሠራረቱን (፪) የሚያከራክር ማስረጃን (፫) አከራካሪ ማስረጃን እና (፬) ክርክርን በቅደም ተከተል እንመለከታለን ።

፩/ አመሠራረት

እናት አንድን ልጅ በቀጥታ አርግዛ የምትወልድ በመሆኑ እናትነትን በመወለድ ማረጋገጥ የሚቻል ሲሆን ፤ አባት ግን በተመሳሳይ ሁኔታ የማይወልድ በመ ሆኑ ፤ አባትነትን በተመሳሳይ መንገድ ማረጋገጥ አይ ቻልም ። መወለድን ''በተፈጥሮ ሕቅ'' የማስረዳትን ዘዴ ደጋፊዎች እንኳን ቢሆኑ ፤ መወለድን ለማረጋገጥ ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙት ሰውየው አባት ሊሆን የሚችል መሆኑን በሚያመለክቱት በሕጋዊ ''ግምት'' ወይም ''አባትነትን በማወቅ'' ነው ። እነዚህ ሁለት ዘዴዎች ሥር ሰደው የሚገኙት ''ከተፈጥሮ ሕቅ'' ሁኔታዎች[26] ይልቅ ከጥንት ጀምሮ በባልና ሚስት መካከል ''የሙተ ማመን ግዴታ'' ወይም ''ተስማሞቶ መቀበል'' መወ ለድን[27] በማረጋገጥ ረገድ አመዝነው በሚታዩባቸው ሕብረተ ሰቦች ነው ። የኢትዮጵያ ሕግ በነዚህ በሁለቱ አመለካካቶች መካከል ያለው የቲዎሪ ውዝግብ ሳያግ ደው የራሱን የተለየ አቋም ይዞ ይገኛል ። ቀጥሎ እንደ ሚታየው ሁለቱም አመለካከቶች ቢሆኑ ለኢትዮጵያ ሕግ አሠራር ሙሉ መፍትሔ ሊሰጡ አይችሉም ።

በኢትዮጵያ የአባትነት አመሠራረት ዓይነቶች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ፤—

(ሀ) ሕጋዊ ግምት (ለ) አባትነትን ማወቅ (ሐ) አንዳንድ ጊዜም በፍርድ የሚደረግ አባትነትን ማወቅ ።

፩ ፤ ሀ/ ሕጋዊ ግምት[28]

(፩) መሠረቱ

በብዙ የሰለጠኑ አገሮች የሚሠራበት ''በጋብቻ የተሳሰረ አባት ነው''[29] የሚለው ሕጋዊ ግምት የኢትዮጵያ ሕግ አካል ነው (አንቀጽ ፭፻፵፭) ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ይህ ሕጋዊ ግምት ሰፋ በማለት ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት የሚ ኖርንም ይጨምራል (አንቀጽ ፭፻፵፭) ። ስለሆነም በኢትዮጵያ ይህ ሕጋዊ ግምት ፤ ''በጋብቻ የተ ሳሰረም ሆነ ከጋብቻ ውጭ እንደባል የሚኖር አባት ነው'' ሊባል ይችላል ማለት ነው ። ዝቅ ብሎ እንደሚገለጸው[30] ይህ ሕጋዊ ግምት ብዙ ውን ጊዜ ሊለወጥ (ሊፈርስ) የማይችል በመሆኑ (አንቀጽ ፭፻፭)[31] ፤ በጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ እንደ ባልና ሚስት መኖር[32] በነዚህ ሁኔታዎች የተረገዘና የተወለደን ልጅ አባትነት በማስረዳት ረገድ ተመሳሳይ ናቸው ። ይህ ሁኔታ ከተሟላ አባትነት በቀጥታ ''ከእናትነት'' መረጋገጥ ይገ (ከላይ ይመልከቱ) ።

(፪) የተለየ ሁኔታ

ከላይ የተመለከተው የአባትነት ግምት ጋብ ቻው ከፈረሰበት ወይም ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት መኖሩ ከቀረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ፫፻ ቀን ድረስ የሚወለዱትን ልጆች ይጨምራል (አን ቀጽ ፭፻፶፫-፩ እና ፭፻፶፭-፪) ። ይሁን እንጂ ልጁ የተወለደው ጋብቻው ከፈረሰ ወይም እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖሩ ከቀረ ከ፪፻፲ ቀናት በኋላ ከሆነ ፤ የልጁ ሕጋዊ አባት አባትነቱን ልጁን ለማወቅ (ለመቀበል) ለሚፈልግ ለሌላ ሰው አሳ ልፎ ለመስጠት በመዋዋል የአባትነቱን ግምት ለማስቀረት እንደሚችል ተመልክቷል ።[33] ስለ ልጁ ጥቅም መጠበቅ በሕጉ በግልጽ ያልተጠቀሰ ቢሆንም ፤ የአባትነቱን መተላለፍ ፍርድ ቤት ስምምነቱን እናትዮዋን ከሰማ በኋላ የሚያጸድ ቀው በመሆኑ መንፈሱ የተጠበቀ ይመስላል (አን ቀጽ ፭፻፭፯) ።[34]

የሁለት ሰዎች የአባትነት ግምት ሲኖር አባ ትነትን በውል ማስተላለፉ በሁለት በሕግ አባት ናቸው ተብለው በሚገምቱ ሰዎችም መካከል ሊደ ረግ ይችላል (አንቀጽ ፭፻፭፱) ። ይህ የሚፈጠረው አንደኛው ሰው በጋብቻ ምክንያት አባት እንደሆነ በሚገመትበትና ሴትዮዋ በዚሁ ጊዜ ከሌላ ሰው ጋር ከጋብቻ ውጭ እንደሚስት አብራ በመኖሯ[35] የተነሳ አባት እንደሆነ በሚገመትበት ጊዜ ነው[36] ። በሁለቱ ሰዎች መካከል የሚፈጠረውን ጥያቄ ለመፍታት የሚደረገውን ውል (የልጁን ጥቅም ለመጠበቅ ይመስላል) ፤ እናትዮዋን ከሰማ በኋላ (አንቀጽ ፭፻፭፫) ፍርድ ቤት ሊያጸድቀው ይገባል ። ጥያቄው በውል በማይፈታበት ጊዜ ቅድሚያ በጋብቻ ምክንያት አባት እንደሆነ ለሚ ገመተው ሰው እንዲሰጥ አንቀጽ ፭፻፭፬-ሀ ይደነ ግጋል ።

---

26 በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 6 የተጠቀሰውን አውራሊያን ጆኢስኩን ይመልከቱ ።

27 ከጋብቻ (መተማመን) ወይም ከስምምነት (ማወቅ) እንደሚመነጩት ።

28 ሰፋ ላለ ማብራሪያ የቀድሞውን ሪፖርት ገጽ 513 ይመልከቱ ።

29 ፓተር ኤዝ ኤስት ኪም ኑፕታይ ዴሞንስትራንት ።

30 ከዚህ በታች አከራካሪ የልጅነት ማስረጃ የሚለውን ይመልከቱ ።

31 በተለይም እናትዮዋ ከሌላ ወንድ ጋር ግንኙነት ነበራት ብሎ በመካራከር ለማፍረስ አይቻልም (አንቀጽ ፭፻፹፮) ።

32 አንድ ወንድና አንድ ሴት የጋብቻ ውል ሳይኖራቸው እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ የሚፈጠር ሁኔታ ነው (አንቀጽ ፭፻፹) ።

33 አንቀጽ ፭፻፷፭ እና የዚህን ሪፖርት መደምደሚያ ይመልከቱ ።

34 የቀድሞውን ሪፖርት ገጽ 518 ይመልከቱ ።

35 እንዲህ ያለው ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት መኖር በተለይም ባልዮው ለረዥም ጊዜ በማይኖርበት ወይም ባልና ሚስቱ አብረው በማይኖሩበት ሁኔታ ይዘወተራል ።

36 የአባትነትን መደራረብ በሚመለከት በቀድሞው ሪፖርት ገጽ 518 የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 61 ሌላ ምሳሌ ተሰጥቷል ።

፩ ፤ ለ/ማወቅ

ይህ ርዕስ በቀድሞው ሪፖርት[37] በሚገባ ተብራርቶ የቀረበ ስለሆነ ፥ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አንዳንድ ሁኔታ ዎችን ብቻ እንመለከታለን ።

ማወቅ የልጅነት ማረጋገጫ የሚሆነው አባትነትን በሚመለከት ብቻ ነው ።

በልጅነት ሊታወቅ የሚችል ፥ በሕጋዊ ግምት ወይም ቀደም ሲል በተደረገ መታወቅ (አንቀጽ ፯፻፶፯) [38] ሕጋዊ አባት የሌለው ልጅ ብቻ ነው (አንቀጽ ፯፻፶፯) ። ይህ ሁኔታ ከላይ ከተጠቀሰው ዓይነት በስተቀር ሌላ የአባትነት መደራረብ እንዳይኖር ይከላከላል ።

አንድ ሰው አንድ ጊዜ አባትነቱን አውቆ ከተቀበለ መቀበሉ የሚያስከትለውን ውጤት የማይፈልገው ቢሆ ንም እንኳን ማወቁ የጸና ይሆናል ። ተቀባዩ አባትነቱን በማወቁ የተነሳ ጥቅማቸው የሚነካ[39] ቢሆንም እንኳን የአዋቂው ዘመዶች ማወቁን ለመቃወም አይችሉም ።

አባትነትን ማወቅ በጽሑፍ መደረግ ያለበት ይሁን እንጂ (አንቀጽ ፯፻፶፰) ፥ በባለሥልጣን እንዲረጋገጥ አስፈላጊ አይደለም ።

የልጁ አባት የሞተ ወይም ሐሳቡን (ፈቃዱን) ለመ ግለጽ በማይቻልበት ሁኔታ ላይ የሆነ እንደሆነ የልጁ መታወቅ በአባቱ ወላጆች ሊደረግ ይችላል (አንቀጽ ፯፻፶፱) ።

የአባትዮው ልጁን ማወቅ በእናትዮዋ[40] ወይም እስዋ በሌለችበት ጊዜ በወላጆችዋ ተቀባይነት ካላገኘ በስተ ቀር ዋጋ አይኖረውም (አንቀጽ ፯፻፶፩) ። እንዲሁም የአ ባትዮው ልጁን ማወቅ ልጁ አካለ መጠን የደረሰ ሆኖ ካልተቀበለው ዋጋ አይኖረውም (አንቀጽ ፯፻፶፪) ። [41] ታዋቂው ተቃውሞ እስካልሰነዘረ ድረስ መታወቁን እንደተቀበለው ይቆጠራል (አንቀጽ ፯፻፶፫) ።

ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ተክቶ የሞተን ልጅ ማወቅ ይቻላል (አንቀጽ ፯፻፶፬) ።

ልጂ ነው ሲል አባት የሰጠውን ቃል ለመለወጥ አይ ችልም ። ሆኖም ይኸንን ቃል የሰጠው አሳዳሪው ሳይ ስማማ አካለ መጠን ያላደረሰ አባት ከሆነ ፥ ይኸንኑ ቃሉን አካለ መጠን ከደረሰ በኋላ በአንድ ዓመት ውስጥ ሊለውጥ ይችላል (አንቀጽ ፯፻፶፭) ።

ማወቁ የተደረገው ኃይል በመጠቀም ከሆነ ፈራሽ ሊሆን ይችላል ። ልጁ ልጂ ነው ብሎ የተቀበለው ሰው ልጁ ከሱ ሊጸነስ የማይችል መሆኑን በግልጽ ካላስረዳ በስተቀር ፥ በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው በማለት ለማፍረስ አይችልም (አንቀጽ ፯፻፶፯) ። ስለዚህ ታማኝነት በሌላት ወዳጁ ልጁ ያልሆነውን ልጁ አድ ርጎ በመቀበል ስህተት የፈጸመም ሆነ በመታለል ልጁ ያልሆነውን ልጁ አድርጎ የተቀበለ ሰው በኋላ ቢጸጸት[42] የመካድ ክስ ከማቅረብ በስተቀር ምንም መፍትሔ የለ ውም ማለት ነው ።

በሕጋዊ ግምትም[43] ሆነ በማወቅ የተመሠረተ ሕጋዊ አባትነት ፥ ከአባትዮው በስተቀር በሌላ ሰው ክርክር ሊነሳበት አይችልም ።

፩ ፤ ሐ/በፍርድ ስለሚደረግ የአባትነት ማወቅ

አንድ ልጅ ሕጋዊ አባት የሌለው ሲሆንና የልጁ መጸነሻ ነው ተብሎ በሚታመነው ጊዜ ውስጥ[44] የልጁ እናት የመጠለፍ ወይም የመደፈር ሥራ ደርሶባት የወ ለደች እንደሆነ ፥ በተለየ ሁኔታ[45] "አባትነት በፍርድ እንዲታወቅ" ሊደረግ መቻሉን ሕግ ይደነግጋል (አንቀጽ ፯፻፶፰) ።

በእናትዮዋ መቅረብ የሚገባው[46] የዚህ ክስ የጊዜ ገደብ ልጁ ከተወለደበት ወይም በመጥለፉ ወይም በመ ድፈሩ ሥራ ላይ የወንጀል ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ አን ስቶ ሁለት ዓመት ይሆናል (አንቀጽ ፯፻፶፱) ። የመጥ ለፉ ወይም የመድፈሩ ሥራ ተረጋግጦ ፍርድ ከተሰጠና ጠላፊው ወይም የመድፈሩን ሥራ ፈጻሚው ልጁ ከእሱ[47] ሊፀነስ የማይችል መሆኑን በግልጽ ሊያስረዳ ካልቻለ በስተቀር አባትነቱን በፍርድ እንዲያውቅ መደ ረግ አለበት (አንቀጽ ፯፻፷) ።

ከዚህ በላይ ለተመከተው የአባትነት ማረጋገጫ ዘዴ ያለው ምክንያት ለሌሎቹ የአባትነት ማረጋገጫ ዘዴ ዎች ካለው ምክንያት የተለየ ይመስላል ። አንድ ሴትና ወንድ አብረው ከመኖራቸው የተነሳ[48] የአባት ነት ሕጋዊ ግምት መደረጉ ፥ ወይም ይህ በማይኖርበት ጊዜ በፈቃደኝነት አባትነት መታወቁ ፥ አብዛኛውን ጊዜ በእርግጥ የአባትነቱን መኖር በይበልጥ ያመለክ ታል ። አባትነቱን ተገዶ እንዲቀበል በተደረገ ጠላፊ ወይም የመድፈር ሥራ ፈጻሚ ረገድ ግን ይህ እውነት

---

37 የቀድሞውን ሪፖርት ገጽ 514-517 እና የዚህን ሪፖርት መደምደሚያ ይመልከቱ ።

38 ወይም ከዚህ በላይ በልዩ ሁኔታ በ/ሀ- ii ወይም ከዚህ በታች በ/ሐ ልጅነትን መወሰን ።

39 ለምሳሌ ቀለብ በመስጠት ግዴታ ወይም በውርስ ሕግ ረገድ ።

40 ይህ የእናትዮዋን ማንነት በቅድሚያ ማረጋገጥን ይፈልጋል (ብዙውን ጊዜ የእናትነት ሁኔታ መኖርን በማሳየት) ። እንደምንጊዜውም ሁሉ በዚህም ሁኔታ የአባትነት መረጋገጥ ከእናትነት መረጋገጥ ይከተላል ።

41 የአካለ መጠን መድረሻ ዕድሜ ፲፰ ዓመት ነው (አንቀጽ ፩፻፶፰) ።

42 የዚህን ሪፖርት መደምደሚያ ይመልከቱ ።

43 ከታች ስለክርክር የተጻፈውን ይመልከቱ ።

44 ከመጥለፉ ወይም ከመድፈሩ ሥራ በኋላ ከ፪፻፹-፫፻ ቀናች (አንቀጽ ፯፻፶፫ እና ፯፻፶፫) ።

45 አንቀጽ ፯፻፷፩ ይመልከቱ ።

46 እናትዮዋ ከሞተች ወይም ሐሳቧን ለመግለጽ በማትችልበት ሁኔታ ላይ ካለች በልጁ አሳዳሪ ።

47 ለምሳሌ ለመውለድ የማይችል መሆኑን በማሳየት ።

48 ጋብቻ ወይም ኪጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት መኖር ።

ሊሆን አይችልም ። ተገዶ አባትነቱን እንዲቀበል ማድረጉ ለፈጸመው የወንጀል ሥራ በተለየና[49] የግል ካሣ ዓይነት መልክ ባለው ቅጣት እንዲቀጣ ማድረግ ነው ። ይህንንም ፥ የመወለድ ውጤቶች በሁሉም ሁኔታዎች አንድ ዓይነት ናቸው ከሚለው መሠረተ ሐሳብ ውጭ ፥ በዚህ ሁኔታ አባትነቱን እንዲቀበል የተደረገው አባት ልጁን ሊያሳድገውና ሊደግፈው ግዴታ ያለበት ሆኖ ሳለ (አንቀጽ ፷፪፱-፩) ፥ ልጁ ግን በዚህ ሁኔታ የተቀበለውን አባቱን ''የመጦር'' ግዴታ የሌለበት በመሆኑ (አንቀጽ ፷፪፲) ለመገንዘብ ይቻላል ።[50]

የጠለፋ ወይም የመድፈር ሥራ ካልተፈጸመ በስተቀር አባትነት በፍርድ እንዲታወቅ ማድረግም ሆነ እንዲደረግ መጠየቅ አይቻልም (አንቀጽ ፷፭)[51] ። ይህ ገደብ ፥ በጋብቻ ወይም ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብረው ከሚኖሩ በስተቀር ፥ በአንድ ሴትና በአንድ ወንድ መካከል ያሉ ሌሎች ግንኙነቶች ሕጋዊ ውጤት የሌላቸው መሆኑን በሚገልጸው በአንቀጽ ፶፪፳፭ በተጨማሪ የተደገፈ ነው ። ከእነዚህ ሌሎች ግንኙነቶች (''አንዳንድ ጊዜ'' የሚደርሱ) የሚወለዱ ልጆች ሕጋዊ መተሳሰር ያላቸው ከእናትየዋ ጋር ብቻ ነው ።[52] የሚመለከታቸው ወገኖችም ሆነ ሌሎች ለማንኛውም ጉዳይ ቢሆን (ለምሳሌ ጥፋት በሌለበት ሁኔታ ከውል ውጭ በሆነ ግዴታ ካሣ ለመጠየቅ) እነኝህን ግንኙነቶች በማንሳት በፍርድ ቤት ሊጠቀሙባቸው አይችሉም በሚል የተደነገገው[53] ይህን ገደብ ይበልጥ ያጠነክረዋል ።[54]

በመጀመሪያ የተጠቀሱት ገደቦች ከ፲፱፻፶፲፱ ዓ/ም በፊት የነበረውን ''አባትነትን መፈለግ የተከለከለ ነው'' የሚለውን የፈረንሳይ ሕግ መሠረተ ሐሳብ[55] በጉልህ ያንፀባርቃሉ ።[56] ይህ አመለካከት በአሁኑ ጊዜ ብዙ አገሮች[57] አባትነትን መፈለግ እንዲቻል ሰፋ ያለ መንገድ[58] በመክፈት ከወሰዱት አዝማሚያ የሚቃረን ሆኖ ይታያል ። ከ፲፱፻፷ ዓ/ም በፊት በኢትዮጵያ አባትነትን የመፈለጊያ መንገዶች ሰፊ ነበሩ ። የአሁኖቹ ገደቦች ''ለመውረስ ዓላማ ብቻ መወለድን ለማረጋገጥ የሚቀርቡ መሠረተ ቢስ ክሶችን'' ለማስቀረት የተደረጉ ናቸው ።[59] እነዚህ ገደቦች ባሕላዊ ልምዶችን ስለሚቃረኑ አንዳንድ ጊዜ የሚያልፉዋቸው ፍርድ ቤቶች አይታጡም ። ስልዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ የመወለድን ሕግ በሚመለከት ረገድ በፍርድ ቤቶች በኩል (ሕጉን በማላላት) ቀድሞ ወደነበረው ሁኔታ የመመለስ አዝማሚያ ይታያል ። በሕጉ ውስጥ የተተኮረባቸውን ጽንሰ ሐሳቦችና የሕጉን አቀራረብ በሚገባ አለመረዳት ለዚህ አመች ሁኔታን ፈጥሮዋል ። በተለይም አብዛኛውን ጊዜ ፍርድ ቤቶች ፥ በአባትነት አመሠራረት ዘዴዎችና (ለምሳሌ ማወቅ) በአባትነት ማስረጃ ዘዴዎች (ለምሳሌ የሁኔታ መኖር) መካከል ልዩነት አያደርጉም ።

፪/ የማያከራክር[60] ማስረጃ

ቀደም ሲል እናትነትን በማስረዳት ረገድ ስለማያከራክር ማስረጃ ሲወሳ በተጠቆሙት ምክንያቶች ፥ አባትነትንም በቅድሚያ በተዘጋጀ ''የልደት የምስክር ወረቀት'' (እንደሕጉ ትርጉም) ወይም ''በታወቁ ጽሑፎች'' አማካይነት ለማስረዳት የማይቻል ስለሆነ ፥ ብቸኛና ትክክለኛ የሆነው የማያጠራጥር የአባትነት ማረጋገጫ ዘዴ ፥ የልጅነት ሁኔታ መኖር ነው ።

ይህ ሁኔታ በሕጋዊ የአባትነት ግምት[61] እና በማወቅ[62] ረገድ የመወለድ ማረጋገጫ ዘዴዎች ያላቸው ድክመት የሚያስከትለውን ውጤት በጣም ይቀንሰዋል ። አንድ ልጅ በአንድ ሰው ፥ በሰውየው ዘመዶችና በሕብረተሰቡ እንደሰውየው ልጅ ተደርጎ ከተቆጠረና (አንቀጽ ፶፪፭-፪) ሰውየው ያለኑዛዜ ከሞተ ፥ ልጁ ወራሽነቱን ለማረጋገጥ የሚያስፈልገው በሚመለከታቸው ሁሉ እንደልጅ ተደርጎ መቆጠሩን በአራት ምስክሮች ማረጋገጥ ብቻ ነው (አንቀጽ ፶፪፭-፩) ።[63] ከዚህ በኋላ ማንም ተቃዋሚ ቢሆን በቅድሚያ በአራት ምስክሮች (አንቀጽ ፶፪፭-፪) ልጁ ''የልጅነት ሁኔታ'' የሌለው መሆኑን ለማረጋገጥ ካልቻለ በስተቀር ፥ ልጁ ልጅነቱን

---

49 በአንቀጽ ፪፲፮፭ እና ፪፲፯፭ ላይ ያልተመሠረተ ።

50 ሬኔ ዳቪድ ፥ ሉ ድርዋት ዱ ላ ፋሚል ዳን ሉ ኮድ ሲቪል ኢትዮጲን ፥ ሚላኖ ፥ ጉፍሬ ፥ 1967 ፥ ገጽ 66 ።

51 ይህ ሁኔታ በጋብቻ ፥ ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት በመኖር ወይም በማወቅ የተረጋገጠ አባትነት ''በፍርድ እንዲታወቅ የተደረገ አባትነት'' አለመሆኑን እንድንቀበል ያስገድደናል ።

52 ሆኖም በኋላ የሚደረግን የማወቅ ውጤት አያስቀረውም ።

53 ከፈረንሳይ ሕግ አሠራር የሚታረን ይመስላል (በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 56 የተጠቀሰውን ይመልከቱ) ።

54 ጆርጅ ክሽችኖቢች ፥ ''የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 758-761 ፥'' የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት ፮ልዩም ፪ (፲፱፻፷፰) ፥ ገጽ 185 እንዲሁም አንቀጽ ፭፻፵፱ ይመልከቱ ።

55 ''የኖቬምበር ፲፱ ፲፱፻፲፱ ዓ/ም'' የፈረንሳይ ሕግ በዚህ ረገድ ያለውን አመለካከት አሻሽሎታል ። እንዲሁም በቅርቡ ''በጃንዋሪ ፮ ፲፱፻፸፱፪ ዓ/ም ሕግ'' የበለጠ መሻሻል ተገኝቷል ።

56 በጠለፋና በመድፈር ሥራ ሳቢያ ከሚሆነው በስተቀር ። ከዚያ ወዲህ ስለተደረጉ ለውጦች ፤
ጆ ቫይላል ፥ ለ ኢ፫ሉሲየን ዶ ላ ሴፎስላሲዮን ሱር ላ ፊሊየሽን ናቱሬል ፥ (ፓሪስ ፥ ኩጆስ ፥ ፲፱፻፷፮) ይመልከቱ ። እንዲሁም ስለ ፲፱፻፸፪ ዓ/ም ሕግ ፥ ዳኮት ኤንድ ሲፒተሪ ፥ ለ ነዙ ድርዋ ዶ ላ ፊሊየሽን ላይብራሪ ቴክኒክ ፥ ፲፱፻፸፪ ይመልከቱ ።

57 በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በአውሬሊያን ጆናስኮ ተገልጾአል (በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 6 ተጠቅሶአል) ።

58 ለምሳሌ በማሳት አስወለደ ተብሎ ሲጠየቅ ወይም በሌላ ሁኔታ አባትነቱን ሲያምን ።

59 የዚህን ጽሑፍ መደምደሚያ ይመልከቱ ።

60 ለዚህ ቃል ትርጉም የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 7 ይመልከቱ ።

61 ጋብቻን ወይም ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን በሚመለከት ።

62 በጠለፋ ወይም በመድፈር ሥራ (አንቀጽ ፶፪፭) አባትነት በሕግ የሚመሠረትበት ሁኔታ በጣም ጥቂት ነው ፤ በዚህ ረገድ ፍርድ ቤት የሚቀርብ ጉዳይ የለም (በባሕልና በልምድ የዚህ ውጤት ብዙ ጊዜ ጋብቻ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የበቀል እርምጃ ወይም ቅጣት ይሆናል) ። ሆኖም በአንቀጽ ፶፪፭ የተመለከተውንና በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 38 የተጠቀሰውን የተለየ የአባትነት አመሠራረት ዘዴ መገንዘብ ይገባል ።

63 እንዲሁም ብዙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡት ምስክሮች አያንዳንዳቸው ለልጅነት ሁኔታ መኖር አስፈላጊ የሆኑትን ሁኔታዎች በሙሉ እንዲያረጋግጡ የማያስገድዱ ስለሆነ ፥ አንዲሚላ የሚጠይቀውን ይቀንሱታል ።

በአባትነት አመሠራረት ዘዴዎች እንዲያረጋግጥ ሊያ ደርገው አይችልም ። ተቃዋሚው በዚህ ሁኔታ ካረጋ ገጠ ብቻ ነው ልጁ በሕጉ መሠረት እንደ "ማወቅ" ያሉትን የመወለድ ማረጋገጫ ዘዴዎች በመጠቀም ልጅነቱን ማስረዳት የሚገባው ። ፍርድ ቤቶች አንዳንድ ጊዜ በነዚህ ሁለት ደረጃዎች መካከል ያለውን ልዩነት አይረዱም ። በአንዳሩ ግን "ማወቅ" አለ ሊያሰኙ የሚ ችሉት ሕጋዊ ሁኔታዎች በሙሉ ሳይሟሉ ፣ ለምሳሌ ሰውየው ብቻ ልጁን እንደልጅ አድርጎ መቁጠሩን ብቻ "ለልጅነት ሁኔታ"[64] እንደበቂ ማስረጃ በመቁ ጠር ለልጁ ሲያደሉ ይታያል ።

"ለመሆኑ እናቱ ያልታወቀች ልጅ የልጅነት ሁኔታ በመኖሩ ብቻ አባቱ እንዲታወቅለት እንዲያረጋግጥ ሊፈ ቀድለት ይችላል ወይ ?"[65] በቀድሞው ሪፖርት እንዳ ብራራሁት የዚህ መቻል ትርጉም የለሽ ይመስላል ። ይሁን እንጂ በአንቀጽ ፮፻፫-፪[66] አጻጻፍ ይህን ማድረግ በግልጽ የተከለከለ አይደለም ።

፫/ አከራካሪ[67] ማስረጃ

የልጅነት ሁኔታ የሌለው ልጅ አባትነትን[68] ለመ ጠየቅ ሲፈልግ ፤

ሀ/ በጋብቻ የተፀነሰ ወይም የተወለደ መሆኑን ፣ ወይም

ለ/ ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት በመኖር የተፀ ነሰ ወይም የተወለደ መሆኑን ፣ ወይም

ሐ/ የታወቀ መሆኑን የሚያስረዱ የመወለድ ሁኔታዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ አለበት ።[69]

እናትነትን በሚመለከት የመወለድ ሁኔታዎች በማና ቸውም ዘዴ ሊረጋገጡ የሚችሉ ሲሆኑ ፣ ጋብቻን ፣ ከጋ ብቻ ውጭ እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖርንና መታ ወቅን በሚመለከት ግን ይኸንኑ ለማረጋገጥ የሚቻልባ ቸው በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸው ለአካራካሪ የል ጅነት ማስረጃ መሠረት የሆኑ የየራሳቸው የማረጋገጫ ዘዴዎች አሏቸው ።

፫-ሀ/ ጋብቻ

"የጋብቻ የምስክር ወረቀት" (በሕጉ መሠረት)[70] ወይም "የታወቁ ጽሑፎች" ቀዳሚ ሲል በቀረ ቡት ምክንያቶች ለመወለድ ማረጋገጫ ሊሆኑ እንደማይችሉ ሁሉ ፣ ለጋብቻም እንደዚሁ በሕግም ሆነ (አንቀጽ ፫፻፫፻፭፭-፩) በሌላ ሁኔታ (አንቀጽ ፫፻፫፻፭፭-፪) ማረጋገጫ ሊሆኑ አይችሉም ። ይህም "የባልና የሚስትነትን ሁኔታ መኖር"[71] (በባልና በሚስት መካከል) ብቸኛና ትክክለኛ የሆነ የሚያከ ራክር የጋብቻ ማረጋገጫ ዘዴ እንዲሆን ያደረገው ይመስላል ።

ይህም ሲባል ፣[72] የባልና የሚስትነቱ ሁኔታ መኖር ልጁ ከሚወለድበት ወይም ከሚጸነስበት ሕጋዊ ጊዜ ጋር የተያያዘ መሆን አለበት (አንቀጽ ፮፻፵፫) ። በልጁ እናትና የልጁ አባት በተባለው ሰው መካከል ክርክር ያልተነሳበት የባልና የሚስትነት ሁኔታ[73] ከሌለ (አን ቀጽ ፮፻፫) ፣ ጠያቂው ወገን (ልጅ ወይም አባት-አንቀጽ ፮፻፫፭) በጉዳዩ ለመቀጠል በቅድሚያ የፍርድ ቤት ፈቃድ[74] ማግኘት ይገባዋል ። የፍርድ ቤት ፈቃድ ካገኘ በኋላ ጋብቻው መፈጸሙን ማረጋገጥ ይችላል (አንቀጽ ፭፻፫፯-፭፻፹) ። አባትነትን ለማስረዳት በሚ ቀርብ ክስ ፣ ጋብቻው ልጁ ከመጸነሱ ወይም ከመወለዱ በፊት የተፈጸመ መሆኑን ማስረዳት ያስፈልጋል ። በሌላ በኩል ግን ልጁ ከመጸነሱ ወይም ከመወለዱ በፊት ጋብቻው ፈርሶአል የሚባል እንደሆነ ይኸንኑ የማስረ ዳቱ ኃላፊነት የተከሳሹ ነው ። የጋብቻ መፍረስ በጋ ብቻው ጊዜ የተገኘውን የመወለድ ግንኙነት ወይም መተሳሰር የማይለውጠው መሆኑን መግለጹ ተገቢ ይመስላል ።[75]

፫-ለ/ ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት መኖር

እንደጋብቻ ሁሉ (የምስክር ወረቀት ያለመኖሩ ሳይነሳ) ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ ለመኖርም የሚያከራክር ማስረጃው የዚሁ ሁኔታ መኖር ነው ።[76] በሁለቱም ሁኔታዎች የሚገ

---

64 ለምሳሌ እንደልጅ ተደርጎ ለማይያዝና ለማይታይ ልጅ ለመኖሪያና መማሪያ የሚያስፈልገውን ወጭ በመክፈል ።

65 የቀድሞውን ሪፖርት ገጽ 520 ይመልከቱ ።

66 "በአንድ ሰው ወይም በአንዲት ሴት እንደልጅ ተደርጎ መያዙ" የሚለውን ይመልከቱ ።

67 ለዚህ ቃል ትርጉም የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 17 ይመልከቱ ።

68 አወዛጋቢ የሆነውንና በልጅ የሚቀርብ የመወለድ ጥያቄ መቅረብ ያለበት በእናትየዋ ላይ ነው የሚለውን የአንቀጽ ፮፻፫፭-፪ ትርጉም በሚመለከት "ስለኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ አንዳንድ ጥያቄዎች" የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት ፫ልዩም 9 ገጽ 207 እና "የቤተሰብ ሕግ ጥያቄ" ቁጥር 24 (ሕግ ፋኩልቲ ፣ አዲስ አበባ) በፕሮፌሰር ክሽኖቢች ይመልከቱ ።

69 በኢትዮጵያ ሕግ አባትን መፈለጊያ ዘዴዎች ሰፊ አይደሉም ። በእንዳንድ አባትን መፈለጊያ ዘዴዎች ሰፊ በሆኑባቸው አገሮች ይኸው የሚመሠረተው በቅድሚያ ለምሳሌ ማሳሳት የተፈጸመ መሆኑ ወይም የታመነ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው (በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 56 የተጠቀሰውን ጀ ቫይዳልን ይመ ልከቱ ።) በኢትዮጵያ የአባትነት ማረጋገጫ ዘዴዎች በሕግ የተወሰኑ ናቸው ።

70 አንቀጽ ፮፻፶፭ ይመልከቱ ።

71 በመወለድ ሕግ በሚደረገው ዓይነት የሚተረጉምና በዚያው ሁኔታ የሚረጋገጥ ወይም የሚፈርስ (አንቀጽ ፮፻፶፱-፮፻)

72 በ"አከራካሪ" የልጅነት ማስረጃ አባትነትን ማስረዳት ለሆነው ።

73 አንቀጽ ፮፻፭ ፣ ቀደም ሲል በተሰጡት ምክንያቶች (የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 12 የሚያብራራውን ክፍል ይመልከቱ) ፣ ከእሁን ወዲያ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ "የታወቁ ጽሑፎች" አይጠቀሱም ።

74 የሃይማኖት የጋብቻ የምስክር ወረቀትን (አንቀጽ ፭፻፫፱) ፣ "የጋብቻ ውልን" (አንቀጽ ፮፻፹፫-፭) ፣ ወይም ጠንካራ የሆኑ የአካባቢ ማስረጃዎችን መሠረት በማድረግ ።

75 አንቀጽ ፮፻፶፭-፫ እና በዚህ እትም ውስጥ የሚገኘውን የጀ. ክሽችኖቢች የፍርድ ትችት ያገናዝብ ።

76 በእኔ አስተያየት ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን ለማረጋገጥ የሁኔታን መኖር መጠየቁ ማረጋገጡን በጣም ከባድ ስለሚያደርገው አስፈላጊ አይመስለኝም ። የኢትዮጵያ ቤተሰብ ሕግ ጥያቄ ቁጥር 17 (አዲስ አበባ ፣ ሕግ ፋኩልቲ) ጀ ክሽችኖቢች ይመልከቱ ።

ኘው መወለድ የሚያስከትለው ውጤት አንድ በመሆኑ ፥ ለዚህ ጽሑፍ ዓላማ ሁለቱ ሰዎች በሕግ ባልና ሚስት ሆነው መኖራቸውን (አንቀጽ ፯፻፺፱) ወይም ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት አብረው (አንቀጽ ፯፻፲፰) መኖራቸውን ለይቶ ማስረዳቱ አስፈላጊ አይደለም ።[77] ይልቁንስ አስፈላጊው ጉዳይ አብሮ መኖሩ ከልጁ መወለጃ ወይም ሕጋዊ መነፀሻ ጊዜ ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው ።

ሕግ አውጭው በዚህ ደረጃ ላይ ማቆም ሲገባው ፥ ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት በመኖር ሁኔታ ላይ (አንቀጽ ፯፻፳፭ እና ፯፻፲፰) ክርክር ሲነሳበትና አራት ምስክሮች ቀርበው ስለአለመኖሩ ሲመሰክሩ (አንቀጽ ፯፻፲፱) ሁኔታው ስለመኖሩ ለማስረዳት የሚቻልበትን ሁለተኛ መንገድ በአንቀጽ ፯፻፳፭ ደንግጓል (ይህ በጋብቻ ሁኔታ መኖር ላይ ክርክር ሲነሳ የሚደረገውን የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ያላግባብ በመከተል የተነደፈ ነው ፥ - አንቀጽ ፯፻፲፪-፯፻፲፭) ። ይሁን እንጅ ይህ አንቀጽ በሥራ ላይ ሊውል የማይችል በመሆኑ ፍርድ ቤቶች አይጠቀሙበትም ።[78]

፫-ሐ/ ማወቅ

አባትነትን ማወቅ በጽሑፍ መደረግ ያለበት ሲሆን፥ "በምስክሮች ሊረጋገጥ አይችልም"[79] (አንቀጽ ፯፻፶፫) ። ማወቅን ለማስረዳት ጽሑፉ ራሱ በማስረጃነት መቅረብ ይኖርበታል ።[80] በአንቀጽ ፭፻፶፯ የተገለጸውን "የታወቁ ጽሑፎችን" አሠራር በማገናዘብ የተጠቆመው ልዩ ሁኔታ ቀደም ሲል በቀረቡት አጠቃላይ ምክንያቶች የሚሠራ አይመስልም ።[81]

፬/ ክርክር

በጋብቻ ወይም ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር[82] በሚመሠረት አባትነት ላይ ክርክር ሊነሳ የሚችለው በሕጋዊ አባትዮው በራሱ[83] ብቻ እና በቀድሞው ሪፖርት በተገለጹት ምክንያቶች ብቻ ነው ። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ምክንያቶች ሰውየው በልጁ ሕጋዊ የመፀነሻ ጊዜ ሁሉ ከእናትዮዋ ጋር ለመገናኘት አለመቻሉ (አንቀጽ ፯፻፹፫) ወይም ልጁ ፈጽሞ ከሱ ሊወለድ የማይችል መሆኑ (ለምሳሌ ለመውለድ የማይችል በመሆኑ) ናቸው (አንቀጽ ፯፻፹፮) ።[84] እናትዮዋ ከሌላ ወንድ ጋር ግንኙነት ማድረጓ ወይም እምነት አጉዳላ ልጇን ከሌላ ሰው የወለደችው መሆኗን ማመኗ አባትነትን ለመቃወም በቂ ምክንያቶች አይደሉም (አንቀጽ ፯፻፹፮) ።

በአንድ በታወቀ ከጋብቻ በመነጨ የአባትነት ጉዳይ አባት የተባለው ሰው የተከሳሽ ለመሆኑ የሕክምና የምስክር ወረቀት ቢቀርብም ፥ አባትዮው እያለ ልጇ አይደለም ያላላውን ልጅ እሱ ከሞተ በኋላ ልጇ አይደለም በማለት የቀረበውን ክርክር የከፍተኛው ፍርድ ቤት በተገቢ ሁኔታ ውድቅ አድርጎታል ።[85]

ሐ/ የመወለድ ውጤቶች

በማንኛውም ሁኔታ ቢመሠረትም የሕጋዊ መወለድ ውጤቶች ለሁሉም ልጆች አንድ ናቸው ።[86] ለምሳሌ ሁሉም ልጆች ከአባትዮው ወይም ከእናትዮዋ ቀለብ የማግኘትም ሆነ (አንቀጽ ፭፻፵፭-፪) አባትዮውን ወይም እናትዮዋን የመውረስ (አንቀጽ ፭፻፸፪) መብታቸው እኩል ነው ።

በአንጻሩ ግን በሕግ ያልተመሠረተ ሆኖም ግን ግልጽ የሆነ የዲቃላ ልጅነት ጋብቻን በማስከልከል ረገድ[87] ብቻ በቂ የመሆን ውጤት አለው (አንቀጽ ፭፻፹፬) ።

መደምደሚያ

፩/ በጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆችን በሚመለከት ረገድ በውጭ ሀገሮች የሚደረጉ አዳዲስ የሕግ ለውጦች አንዳንዶቹ በቅርቡ ሕጋዊ እኩልነትን ያስገኙ ሲሆን ፥ ሌሎቹ ደግሞ ቀስ በቀስ ይህን እኩልነት ለማምጣት በመሞከር ላይ ናቸው ። ይህ እኩልነት በኢትዮጵያ ውስጥ ሥር ሰዶ የቆየ ነው ።

፪/ በጋብቻና ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆችን ሕጋዊ እኩልነት በተግባር ለመተርጎም የመወለድ ግንኙነቶች የሚረጋገጡባቸውን ዘዴዎች ሰፋ ማድረግ ያስፈልጋል ። ይህን አመለካከትና አቅጣጫ የውጭ ሀገሮች የሕግ አሻሻዮች የሚከተሉት ይመስላል ። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የተለየ አቅጣጫ ስትከተል

---

77 የበላይነት በሌለው በዚህ አንቀጽ (እና በአንቀጽ ፯፻፳፭) የእንግሊዝኛ ቅጅ ሳይጋቡ እንደባልና ሚስት መባሉ ቀርቶ እንደባልና ሚስት ስለተባለ ልዩ ነቱን መገንዘብ የበለጠ አስቸጋሪ ነው ።

78 የቤተሰብ ሕግ ጥያቄዎች ቁጥር 18 (አዲስ አበባ ፥ ሕግ ፋኩልቲ) በጅ. ክሽችኖቢች ይመልከቱ ።

79 ለምሳሌ አይተነዋል ወይም በአንቀጽ ፭ቪ፯፻፭፯(፪) መሠረት በፊርማችን አጽድቀነዋል በሚሉ ።

80 ስለሆነም እነዚህን መሰል ሰነዶችን በፍርድ ቤት ማስመዝገብ ይጠቅማል ።

81 እንዲሁም ይህ ማገናዘብ ከአንቀጽ ፭፻፸፮ መንፈስ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ።

82 አንቀጽ ፯፻፹፭ "ራሱ ለአወቀ" አባት የሚሠራ ቢሆንም ፥ ከአንቀጽ ፯፻፸፮-፪ ጋር ይጋጫል ።

83 "ልጇ አይደለም" በማለት የሚቀርብ ክስ ።

84 ሌላው ምክንያት ደግሞ ክርክሩን ከሚያቀርበው ሰው ሚስት ወይም ከጋብቻ ውጭ እንደሚስት አብራ ከምትኖር ሴት አንድ ልጅ እናትነትን በሚጠይቅበት ጊዜ የሚነሳ ነው ። ይህ ሁኔታ በአንቀጽ ፯፻፹፬ ፥ ፯፻፹፯ (፪-ቸ) የሚሸፈን ይመስላል ።

85 በዚህ እትም ውስጥ የሚገኘውን በጅ. ክሽችኖቢች የቀረበውን የፍርድ ግምገማ ይመልከቱ ።

86 በጠለፋ ወይም በመድፈር ሥራ ከሚመነጨው ልዩ ሁኔታ በስተቀር (ከላይ ይመልከቱ) ።

87 "ፖፐሊካይ ኦነስታቲስ" — ፖፐሊክ ኦነስቲ

ትታያለች ። ምክንያቱም በአንድ በኩል በጋብቻና ከጋብቻ ውጭ በተወለዱ ልጆች መካከል ያለውን ልማዳዊ እኩልነት አጥብቃ የያዘች ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ግን ከ፲፱፻፷ዓ/ም ወዲህ ቀደም ሲል ሰፊ የነበሩትን የመወለድን ማረጋገጫ ዘዴዎች አጥብባለችና ነው ። ለዚህ የማጥበብ እርምጃ መነሻ ምክንያቱ ለመውረስ ዓላማ ብቻ መወለድን ለማረጋገጥ የሚቀርቡ መሠረተ ቢስ ክሶችን መከላከል ነው ። ሊወረሱ የሚችሉ የግል ንብረቶች አነስተኛ በሆኑባቸው አገሮች ከላይ የተጠቀሰው ምክንያት የሚያስከትለው ተጽእኖ እምብዛም ስለሆነ ፣ በሶሻሊስት አገሮች መወለድን የማረጋገጫ ዘዴዎች ሰፊ ናቸው ። በኢትዮጵያ እነኝህ ዘዴዎች በሕግ ሰፊ ባይሆኑም ፣ በፍርድ ቤቶች የላላ አተረጓጎም ምክንያት ለቀቅ ብለው ይታያሉ (የግርጌ ማስታወሻ ቁጥሮች ፷፬-፷፭ እና የሚያብራሩትን ክፍል ይመል ከቱ ።)

ፒ/ በኢትዮጵያ አባትነትን የማረጋገጫ ዘዴዎች የተ ወሰኑ ናቸው ።

ከዚህ ቀጥለን በዘጠነኛው ጠቅላላ ጉባኤ በሌ ሎች አገሮች ሪፖርቶች ያልተጠቆሙ የኢትዮ ጵያን ሕግ የተለዩ ሁኔታዎች እንጠቁማለን ፤

ሀ/ ኢትዮጵያ ከእናትዮዋ ጋር ከጋብቻ ውጭ እንደባል በሚኖር ሰው ላይ ሕጋዊና ተቃራኒ ማስረጃ ሊቀርብበት የማይችል የአባትነትን ግምት ትጥላለች ። ለዚህ ዓላማ እንዲህ ዓይ ነቱ ሰው እንደ ባል ይቆጠራል ።

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ እናትነት ብቻ ሳይሆን አባትነትም በሁኔታ መኖር ብቻ ሊረጋገጥ ይችላል (በሕጉ የተገለጹት የመወለድ ማረጋገጫ ዘዴዎች መኖራቸውን ማሳየት ሳያስፈልግ) ። በዚህ ረገድ በሁኔታ መኖር መወለድን በማረጋገጥ እና (አንቀጽ ፯፻፫-፩-፪) የተንቀሳቃሽ ንብረቶች ባለይዞታ በመሆን ባለንብረትነትን በማረጋገጥ (አንቀጽ ፩ሺ ፩፻፺፫ እና ፩ሺ፩፻፺፬) መካከል ግልጽ የሆነ ተመሳሳይነት አለ ።

ሐ/ ማወቅ በእናትዮዋ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት በሚደነገጉ የአንዳንድ አገሮች ሕጎች ፣ እናትዮዋ ሳትቀበል ከሞተች ወይም ሐሳቧን ለመግለጽ በማትችልበት ሁኔታ ከሆነች ማወቁ ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም ። በኢትዮጵያ ግን እናትዮዋ በዚህ ሁኔታ ብትሆንም መቀበሉ በእናትዮዋ ወላጆች ወይም በልጁ ሞግዚት ሊደረግ ይችላል ።

መ/ ኢትዮጵያ ውስጥ "በመታለል" አባትነቱን ያወቀን[88] ሰው አባትነት ፣ ማወቁን ያደረገው ሰው ራሱ አባት ሊሆን የማይችል መሆኑን በማያወላውል ሁኔታ ካላረጋገጠ በስተቀር[89] አባትነቱን ማወቁን ማፍረስ አይቻልም ።

ሠ/ በተፈጥሮ ሐቅ ወይም አንድ ሰው ያለውን ሁኔታ አሳልፎ መስጠት የለበትም በሚለው መሠረተ ሐሳብ ላይ በሚያተኩሩ አገሮች አንጻር ፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች በኢትዮጵያ ውስጥ አባትነት ከሕጋዊ ወላጁ ልጁን ልጁ ነው ወደሚል ሌላ ሰው በውል ለማስተላለፍ ይችላል ። የሁለት ሕጋዊ አባቶች መደራረብ በሚኖርበትም ጊዜ መደራረቡ በሁለቱ አባት ተብለው በሚገመቱት ሰዎች መካከል በውል ሊፈታ ይቻላል ።

፬/ ቀደም ሲል ከተገለጸው የእኩልነት "መሠረተ ሐሳብ" ሌላ ፣ የኢትዮጵያ የመወለድ ሕግ ግልጽ የሆኑ አዝማሚያዎች እንደሚከተለው ሊጠቃለሉ ይችላሉ ፤

ሀ/ ምንም የማያከራክር የልጅነት ማስረጃ (በሁኔታ መኖር) እና በመጠኑ ሊያከራክር የሚችል[90] በመወለድ ሐቅ የሚመሠረት አከራካሪ የእናትነት ማስረጃ ፤

ለ/ ምንም የማያከራክር የአባትነት ማስረጃ (በሁኔታ መኖር) ፤

ሐ/ ፩/ አከራካሪ ማስረጃን ፤ ፪/ አባትነትንና ፫/ ከጋብቻ ውጭ ተወልደው ያልታወቁን ወይም ከጋብቻ ውጭ እንደ ባልና ሚስት በመኖር ሁኔታ ባለመወለዳቸው አባት የሌላቸውን ልጆች በሚመለከት ጠንካራ ገደብ አለው ። ከዚህ በላይ በተጠቆሙት ሦስት ማብራሪያዎች ምክንያት የእነኝህ ገደቦች ውጤት በአንቀጽ ፯፻፷፩ ከሚነበበው መለስተኛ ሆኖ ይገኛል ።

መ/ በፖሊሲ አንፃር የኢትዮጵያ መወለድ ሕግ ዓላማ የውርስ ክርክሮችን በመቀነስ ሰላማዊ ቤተሰቦች እንዲኖሩ ማድረግ ነው ።[91] ይህ ዓላማ ፣

፩/ የልጁን ጥቅም ከመጠበቅና[92] የተፈጥሮ ሐቁን ከማውጣቱ ዓላማ ጋር የተመጣጠነ ሲሆን[93] ፤

---

88 አንዳንድ ጊዜም "ከማክበርና ሰውን ላለማስከፋት ሲባል" ወይም በሌላ ምክንያት ማወቁ ሊደረግ ይችላል ።

89 አንቀጽ ፯፻፶፮(፪) ፣ ሆኖም ልጁ ሌላ ሕጋዊ አባት ካለው ማወቁ ከመጀመሪያው ፈራሽ ነው (አንቀጽ ፯፻፵፯) ።

90 "በመጠኑ ሊያከራክር የሚችል" መባሉ በጉዳዩ ለመቀጠል በቅድሚያ የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት አስፈላጊ መሆኑን ለመጠቆም ነው ። (አንቀጽ ፯፻፭፫-፯፻፵፬) ። ከዚያ በኋላ የመወለዱ የተፈጥሮ ሐቅ በማንኛውም መንገድ ሊረጋገጥ ይችላል (የአባትን ወላጅነት ለማረጋገጥ ይህን ማድረግ አይቻልም ።)

91 በአባትነት አመሠራረትና አንዴ ከተመሠረተ በኋላ ልጁ አይዶለም በማለት ሊቀርብ በሚችል ክርክር ላይ በተጣሉት ገደቦች የተደገፈ ዓላማ ።

92 ለምሳሌ በመቀበል አስፈላጊነት (አንቀጽ ፯፻፶፩-፯፻፶፪) ወይም በፍርድ ቤት መጽደቅ አስፈላጊነት (አንቀጽ ፯፻፷፫ እና ፯፻፷፯) የተደገፈ ዓላማ ።

93 ሁለቱ ዓላማዎች ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት በሚመሠረት አባትነት ረገድ የሚገናኙ ይመስላሉ (አንቀጽ ፯፻፵፮) ።

፪/ አንድ ሰው ያለውን ሁኔታ አሳልፎ መስጠት የለበትም[94] ከሚለው መሠረተ ሐሳብ ርቆ ይገኛል ።

አዲስ አዝማሚያዎችን የሚጠቁም ተጨማሪ መግለጫ ፤ ፲፱፻፸፱ እ. ኤ. አ.

ሀ/ በፍርድ ቤቶች በኩል ስላለው አዝማሚያ

የመወለድ "ማረጋገጫ" ደንቦችን[95] ላላ አድርጎ በመተርጎም በመወለድ "አመሠራረት" ረገድ ያሉትን ጠበቅ ያሉ ደንቦች ላላ ባለ ሁኔታ እንዲሠራ ባቸው የማድረጉ አዝማሚያ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ በፍርድ ቤቶች አካባቢ ጎልቶ ይታያል ። በሕብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ የመወለድ ጥያቄን ለውርስ ዓላማ የማንሳቱ አዝማሚያ እየቀነሰ የሚሄድ በመሆኑ ፤[96] በርከት ያሉት ክሶች የሚነሱት ለልጃቸው ቀለብ እንዲቆረጥላቸው በሚፈልጉ ያላገቡ እናቶች ነው ። በመወለድ ሕግ ረገድ ለወጥ ለማድረግ ከመታቀዱም[97] በፊት ቢሆን ፥ ፍርድ ቤቶች ያላገቡ እናቶች ያለባቸውን ችግር በመመልከት ፥ አባት በተባለው ሰው ላይ "ቀለብ የመስጠት" ትእዛዝ (አንቀጽ ፷፱፮-፩) ለማስተላለፍ ሲሉ "ለሁኔታ መኖር" ወይም /እና "ለማወቅ" አስፈላጊ የሆኑትን ሕጋዊ ሁኔታዎች ላላ አድርገው እንዲተረጉሙ ይገደዱ ነበር ። ይኸውም ከዚህ በሚከተሉት መንገዶች ይደረጋል ፤

፩/ አራቱም ምስክሮች እያንዳንዳቸው (አንቀጽ ፸፱፫፩-፩) ለሁኔታ መኖር አስፈላጊ የሆኑትን ሦስቱንም ሁኔታዎች (አንቀጽ ፸፱፫-፪) ማለትም ልጁ (፩) አባቱ በተባለው ሰው ፤ (፪) በዚሁ ሰው ዘመዶችና (፫) በሕብረተሰብ እንደልጁ ተደርጎ መታየቱን እንዲያረጋግጡ ባለመጠየቅ ፤

፪/ ማወቅ ተቀባይነት እንዲኖረው "በጽሑፍ መደረግ ያለበት" (አንቀጽ ፸፱፵፮-፩) ሆኖ ሳለ ባይሆንም ለሁኔታ መኖር አስፈላጊ ከሆኑት ሁኔታዎች መካከል የመጀመሪያው (ልጁ በሰውየው እንደልጁ ተደርጎ መታየቱ) ከተሟላ ማወቅ እንዳለ በመቁጠር ፤

፫/ የሁኔታ መኖር ፈራሽ ሲሆን የሚችል የአባትነት ማስረጃ ሲሆን ፥ ማወቅ ደግሞ ሊሻር የማይችል የአባትነት መመሥረቻ ዘዴ ሆኖ ሳለ እነዚህን ሁለት የተለያዩ ድንጋጌ ሐሳቦች በማሳከርና ባለመለየት ናቸው ።

ከዚህ በላይ የተጠቆሙትን አዝማሚያዎች የሚያረጋግጡ ፍርዶችን በሌላ የዚህ መጽሔት እትም ለማቅረብ ሙከራ ይደረጋል ።

ለ/ በሕግ መሻሻል ረገድ ስላሉት አዝማሚያዎች

በሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ሥር በተቋቋመው የሕግ አሻሻይ በኩል ሕጉን ግልጽ የማድረግና ከሕብረተሰብአዊነት ፍልስፍና ጋር እንዲስማማ የማድረግ ዓላማ አለ ። የመጀመሪያው ደረጃ የሕግ ማሻሻሉ ሥራ በተለያዩ ንኡሳን አጥኚ ኮሚቴዎች አማካኝነት ተጠናቅቋል ። አንደኛው ንኡስ ኮሚቴ የፍትሐ ብሔር ሕግን የመጀመሪያ ሦስት መጽሐፎች የሠራ ሲሆን ፥ ይህ ጽሑፍ የሚመለከተው ክፍልም በሁለተኛው መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ ነው ። ከዚህ በታች "ሕግ አሻሻይ" ሲባል የፍትሐ ብሔር ሕግ ፭ኛ ፥ ፮ኛ ፥ እና ፫ኛ መጻሕፍትን ረቂቅ ያዘጋጀው (ጁን ፲፱፻፸፮ ፥ አዲስ አበባ) የሕግ አሻሻይ ፭ኛው ንኡስ ኮሚቴ ማለት ሲሆን ፥[98] "ረቂቅ ሕግ" ማለት ደግሞ ይኸው ንኡስ ኮሚቴ ያዘጋጀው የመወለድ ሕግ ረቂቅ ምዕራፍ (የአራተኛው አንቀጽ ረቂቅ አካል) ማለት ነው ።

በረቂቁ ሕግ ላይ ሰፋ ያለ ግምገማ ለማድረግ ጠለቅ ያለ ምርምር ማድረግ ያስፈልጋል ። ከዚህም በላይ የሕግ አሻሻዩ ኮሚቴ ሥራ የዋናውን ኮሚሽን አመለካከት የሚያንፀባርቅ መሆኑ ስለ ማይታወቅ ፥ በዚህ ደረጃ ግምገማ ማድረጉ አጉል ችኩልነት ይሆናል ። ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ አንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮችን ብቻ እንመለከታለን ። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሦስት ጥያቄዎች መመለስ ይሆናል ፤

፩/ ረቂቁ ሕግ የመወለድን ሕግ ችግሮች ምን ያህል ያቃልላል ?

፪/ ረቂቁ ሕግ ከጋብቻና ከጋብቻው ውጭ በተወለዱ ልጆች መካከል ያለውን እኩልነት ምን ያህል ይጠብቃል ?

፫/ ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆችን ጥቅም ለመጠበቅ ፍርድ ቤቶች የሚከተሉትን ላላ ያለ የአሠራር አዝማሚያ ረቂቁ ሕግ ምን ያህል ያንፀባርቃል ወይም ይቃረናል ?

ለ — ፩ ማቃለል ወይም ግልጽ ማድረግ

የሕግ አሻሻይ ኮሚቴው አንዱ ትልቁ አስተዋጽኦ እርስ በርሱ የሚቃረንና የተወሳሰበ ከመሆኑ የተነሳ ግልጽ ለማድረግ ችሎታ ያላቸው እንኳ ዳኞች የተቸገሩበትን የመወለድን ሕግ ማቃለሉና ግልጽ

---

94 አንቀጽ ፸፱፷፪ እና ፸፱፷፭ ።

95 ከላይ የመደምደሚያውን ቁጥር 2 ይመልከቱ ።

96 ከላይ የመደምደሚያውን ቁጥር 2 ይመልከቱ ።

97 ከዚህ በታች (ለ)ን ይመልከቱ ።

98 "አንቀጽ" ሲባል የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ማለት ሲሆን "ረቂቅ አንቀጽ" ማለት ደግሞ የረቂቁ ሕግ አንቀጽ ማለት ነው ።

ማድረጉ ነው ።[99] በረቂቁ የመወለድ ሕግ ፡ ‘‘የአባት ነትን መደራረብ’’ የሚመለከተው ክፍል ፡ ወይም ‘‘መወለድን ማረጋገጥን’’ ከሚመለከተው ክፍል ብዙዎቹ አንቀጾች (አንቀጽ ፯፻፸፪-፯፻፸፯)[100] እንዲቀሩ በመደረጉ ወይም ሌሎች ክፍሎች አጠር ባለ ሁኔታ በመዘጋጀታቸው ቅር የሚሰኝ የሕግ ባለሙያ አይኖርም ።

ለ — ፪ እኩልነት

አሁን ባለው ሕግ በጋብቻና ከጋብቻ ውጭ በተ ወለዱ ልጆች መካከል ‘‘እኩልነት’’ ያለ መሆኑን በግልጽ የሚጠቁም አንቀጽ የለም ። አባታቸው ለተረጋገጠላቸው ልጆች የዚህ መገለጽ አስፈላጊ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ (፩) በቀለብ መቀበልም ሆነ (አንቀጽ ፭፻፷-፩) በውርስ ሕግ (አንቀጽ ፭፻ ፹፬) በሁለቱ መካከል ያለው እኩልነት የማያ ወላውል (ልዩነት አይደረግም) በመሆኑ እና (፪) የአባትነት አመሠራረት በጋብቻም (አንቀጽ ፯፻፵፭) ሆነ ከጋብቻ ውጭ (አንቀጽ ፯፻፵፮) ለተወለዱ ልጆች በተመሳሳይነት የሚሠራ በመሆኑ በሁለቱ መካከል ያለውን እኩልነት ስለሚያረጋግጥ ነው ። እንዲሁም (፫) ላላ ያሉትም ሆኑ (አንቀጽ ፯፻፫-፯፻፫፩) ጠበቅ ያሉት (አንቀጽ ፯፻፫፪-፯፻፫፯) የመ ወለድ ማረጋገጫ ደንቦች ለሁሉም ልጆች በእኩ ልነት የሚሠሩ ናቸው ። በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የእኩልነትን መሠረተ ሐሳብ በግልጽ መጠቀሙ አስፈላጊ አልነበረም ።

በአንጻሩ ረቂቁ ሕግ በጋብቻና ከጋብቻ ውጭ በተወለዱ ልጆች መካከል ‘‘እኩልነት’’ አለ (ረቂቁ ሕግ አንቀጽ ፪፻፸፫)[101] በማለት ይጀምርና በሚቀጥለው ክፍል (የአባትነት አመሠራረት) ግን ይሽን መሠረት ሐሳብ በመጻረር ‘‘በጋብቻ የተወለዱ ልጆች’’ እና ‘‘ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆች’’ በማለት በሁለት ከፋፍሎ ተመሳሳይ ባል ሆነ ሁኔታ ይመለከታቸዋል (ከታች ለ—፫—፭ ይመልከቱ) ። ይህ ክፍፍል አሁን ባለው ሕግ አሠ ራር ምንም አግባብ የለውም ፤ ለውጥም አያ መጣም ።[102] በረቂቁ ሕግ በጋብቻና ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆችን መወለድ በማረጋገጥ ረገድም ተመሳሳይ ባልሆነ መንገድ ይታያሉ (ከታች ለ— ፫-፪ ይመልከቱ) ። ከቀለብ መቁረጥ ግዴታና ከው ርስ ረቂቅ ሕግ በግልጽ (ረቂቅ ሕግ አንቀጽ ፫፻፫[103]) እንደሚታየው መወለዳቸው (ልጅነታቸው) በተረ ጋገጠላቸው ልጆች መካከል ያለው እኩልነት ግን እንደተጠበቀ መሆኑን መገንዘብ ይገባል ።

ለ - ፫ ላላ ያለ አመለካከት ? ፭/ በመወለድ አመሠራረት

የመወለድን ሕግ (፭) በአመሠራረቱ (፪) በማስረ ዳቱ ለማላላት ይቻላል ። ሁለቱ ጽንሰ ሐሳቦች አብዛኛውን ጊዜ ተሳክረው የሚታዩ ቢሆንም ፡ ለየብቻ እንመለከታቸዋለን ።[104] ከዚህ በታች (ሀ) በሕጋዊ ግምት ፡ (ለ) በማወቅ እና (ሐ) በፍርድ እንዲታወቅ በማድረግ አባትነት እንዴት እንደ ሚመሠረት እንመለከታለን ።

ሀ/ ሕጋዊ ግምት

ረቂቁ ሕግ በሕጋዊ ግምት የአባትነትን መመሠረት ቀላል ከማድረግ ይልቅ ከጋብቻ ውጭ ባሉ ሁኔታ ዎች[105] ሕጋዊ ግምት እንዳይሠራ በማድረግ የበ ለጠ አጥብቦታል (የአንቀጽ ፯፻፵፭ መንፈስ ተሠ ርዞአል) ።

ለ/ ማወቅ

ፍርድ ቤቶች የረቂቁን ሕግ አንቀጽ ፪፻፷፪(፭)[106] በመተርጎም ረገድ እንደሚወስዱት አቋም ፡ በማ ወቅ አባትነትን መመሠረት ቀላል ወይም ከባድ ሊሆን ይችላል ። ብዙኃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ መጻ ፍና ማንበብ የማይችል በመሆኑ አብዛኛው በል ማድ የሚደረግ ማወቅ በጽሑፍ አይሆንም ። በተ ጨማሪም አብዛኛውን ጊዜ በልማድ ማወቅ ፡ ካል ተሟላ የሁኔታ መኖር እንደሚገኝ ተደርጎ ይወ ሰዳል (ከላይ ሀ-፪ ይመልከቱ) ። ሆኖም ይህ ልማ ዳዊ አመለካከት ወይም ሌሎች በጽሑፍ ያልተ ደረጉ ማወቆች ‘‘ተቀባይነት የሚያገኙ’’ ከሆነ ፡ ማወቁ የተደረገበት የጽሑፍ ‘‘ስነድ’’ መቅረብ ያለበት መሆኑን የሚደነግገው ማስረጃን የሚመ ለከተው የረቂቁ ሕግ ክፍል (ከታች ለ-፫-፪-ለ ይመልከቱ) በሥራ ላይ ሊውል አይችልም ።

ሐ/ በፍርድ የሚደረግ አባትነትን ማወቅ

የረቂቁ ሕግ አንቀጽ ፪፻፷፯[107] የጠለፋ ወይም

---

99 የቤተሰብ ሕግ ጥያቄዎች (አዲስ አበባ ፡ ሕግ ፋኩልቲ ፡ ፲፱፻፹፯) በጆ ክሸችኖቢች ይመልከቱ ።

100 ከላይ የተመለከተውን ቁጥር 24-25 ይመልከ ፡ ።

101 ‘‘አንቀጽ ፪፻፸፫. የልጆች እኩልነት፡-በጋብቻ እና ከጋብቻ ውጭ በተወለዱ ልጆች መካከል ልዩነት አይደረግም ።’’

102 የዚህን ሪፖርት መግቢያ ይመልከቱ ።

103 ‘‘አንቀጽ ፫፻፫. የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች’’፡-

(፩) ሚችን ለመውረስ ቅድሚያ ያላቸው ልጆቹ ናቸው ።

(፪) የሚቹ ልጆች ከሚቹ ንብረት እኩል ድርሻ ይኖራቸዋል ።’’

104 ባለው ሕግ ‘‘ዲተርሚኔሽን’’ የሚለው ቃል ‘‘አስረተይንሚንት’’ እንደሚለው ቃል ተደርጎ በስህተት ከፈረስንጎሳይኛ የተተረጐመው እንዲለውጥ ባለመደረጉ በረቂቁ ሕግ (የእንግሊዝኛ ቅጅ) መመሰቃቀሉ (ኮንፊውሽን) ብሷል ። በረቂቁ ሕግ ክፍል ፪ የተመለከቱት ሁኔታዎች (ከዚህ በታች ሀ ለ እና ሐ ይመልከቱ) አባትነት የሚመሠረትባቸው ሲሆኑ ፡ የአባትነት መኖር ግን የሚረጋገጠው የመወለድን ማስረጃ በሚመለከተው በረቂቁ ሕግ ክፍል ፪ ነው ።

105 በኢትዮጵያ ውስጥ የተለመዱ ናቸው ።

106 ‘‘አንቀጽ ፭፻፷. ማወቅ የሚፈፀምበት ሁኔታ (ፎርም)፡-አባትነትን ማወቅ በጽሑፍ ወይም በታወቀ ባሕላዊ ሁኔታ መደረግ አለበት ።’’

107 ‘‘አንቀጽ ፪፻፷፯. በፍርድ ስለሚደረግ አባትነትን ማወቅ፡-ልጁ ተረዝ ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ የልጁ እናት የድፍረት ሥራ፡ ጠለፋ ወይም ማሳት የተፈጸመባት ከሆነ ፡ በዚሁ ወንጀል የተፈረደበት ሰው በፍርድ አባትነቱን እንዲያውቅ እንዲደረግ ክስ ሊቀርብበት ይችላል’’ (ሰረዝ የተጨመረ) ።

የመድፈር ሥራ በሚፈጸምበት ጊዜ አባትነት በፍርድ የሚታወቅ መሆኑን በመደንገግ ያለውን ሕግ (አንቀጽ ፮፻፹፰) ይዘት የሚያስተጋባ ከመሆኑም በላይ ፥ ይኸው "በማሳትም" ጊዜ ሊደረግ የሚችል መሆኑን ይገልጻል ። ሆኖም "ማሳት" የሚመለከተው "አካለ መጠን ያልደረሱ" ሴቶችን ለመጠበቅ የተደነገገውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ ፮፻፺፮ በመተላለፍ ወንጀል መፈጸምን ("በፍርድ መቀጣት") መሆኑ በግልጽ ስለተጠቆመ ፥ በዚህ ሁኔታ አባትነት በፍርድ እንዲታወቅ ማድረግ በጣም ጠባብ ነው ። ይህ ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት በመኖር በሕጋዊ ግምት አባትነት የሚመሠረት በመሆኑ ይጠቀሙ የነበሩትን አካለ መጠን የደረሱ ሴቶችንም ጭምር አያጠቃልልም (በዚህ ሁኔታ ሕጋዊ ግምት በረቂቁ ሕግ ተሰርዞአል ፥ ከላይ ሀ-፫ ይመልከቱ) ።

በብዙ አገሮች ሕጎች በሕግ የልጁ መፀነሻ ተብሎ በሚገመተው ጊዜ ከጋብቻ ውጭ እንደባል ከእናትዮዋ ጋር አብሮ መኖር (በብዙ ሕብረተሰባዊ አገሮች እንደዚህ ነው) ወይም በማንኛውም ሁኔታ ከእናትዮዋ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም (ወንጀል ቢሆንም ባይ ሆንም) ፥ በፍርድ አባትነት እንዲታወቅ ክስ ለማቅረብ በቂ ነው ። ለእንዲህ ዓይነት ክሶች ምን መከላከያዎች ለማቅረብ እንደሚቻል ወይም እንደማይቻል ከአገር ወደ አገር ይለያያል ።[108]

ለ - ፫ ላላ ያለ አመለካከት? ፪/ በመወለድ ማስረጃ

አሁን በሥራ ላይ እንዳለው ሕግ ሳይሆን "የመወለድን ማስረጃ" የሚመለከተው ረቂቅ ሕግ፥ "በጋብቻ የሚወለዱ ልጆችን" (ረቂቅ አንቀጽ ፪፻፫፻፮) እና "ከጋብቻ ውጭ የሚወለዱ ልጆችን" (ረቂቅ አንቀጽ ፪፻፫፻፯) ለየብቻ ያያል ። ሆኖም የሁለቱም አንቀጾች ንኡስ አንቀጽ (፩) ከዚህ በታች በ-ሐ በተጠቆሙት ምክንያቶች በሥራ ላይ ሊውል የማይችለውን የመወለድን ወይም የልደት ማረጋገጫ ጽሑፎችን በሚመለከት በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው ። እንዲሁም "የሁኔታ መኖር"[109] በመወለድ ማስረጃነቱ ከነበረበት የሁለተኛ ደረጃ ወደሦስተኛ ደረጃ ዝቅ የሚያደርጉት የነዚሁ አንቀጾች ንኡስ አንቀጽ (፫) ተመሳሳዮች ናቸው ። ስለሆነም የሁለቱ ረቂቅ አንቀጾች መሠረታዊ ልዩነት የሚመነጨው ከንኡስ አንቀጽ (፪) አጻጻፉ ነው ።

ሀ/ የረቂቁ አንቀጽ ፪፻፫፻፮ (በጋብቻ የተወለዱ ልጆች) ንኡስ አንቀጽ (፪)[110] ክስ አቅራቢው የአባትነት ሕጋዊ ግምት እንዲኖር በሚያደርጉ ሁኔታዎች አባትነትን እንዲያረጋግጥ ይፈቅድለታል ። እነዚህ ሁኔታዎች በጋብቻው ጊዜ መወለድ ወይም መፀነስ ናቸው (ረቂቅ አንቀጽ ፪፻፺፭-፩[111]) ። ሆኖም ሕግ አሻሻዩ "የሁኔታ መኖርን" (አንቀጽ ፮፻፺፱) ጨምሮ አሁን በሥራ ላይ ያሉትን የጋብቻ ማረጋገጫ ደንቦች (አንቀጽ ፮፻፳፰-፮፻፴፯) ሰርዞአቸዋል ። ይህ ሁኔታ ፥ ብዙውን ጊዜ እንደሚሆነው ሁሉ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ማቅረብ በማይቻልበት ጊዜ ፥ አባትነትን "በጋብቻ አማካይነት" ማረጋገጥን እንዳይቻል ያደርገዋል ።

ለ/ የረቂቁ አንቀጽ ፪፻፫፻፯ (ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆች) ንኡስ አንቀጽ (፪)[112] ክስ አቅራቢው አባትነትን ለማረጋገጥ ማወቅ የተደረገበትን "ሰነድ" (ማወቁ በባህላዊ መንገድ በቃል ቢደረግስ ? ለ-፫-፩-ለ ይመልከቱ) ወይም በፍርድ አባትነት እንዲታወቅ የተደረገበትን ሰነድ (ሆኖም በፍርድ አባትነት የሚታወቅባቸው ሁኔታዎች ጠባብና የተለዩ ናቸው ፤ ለ-፫-፩-ሐ ይመልከቱ) እንዲያቀርብ ይፈቅድለታል ።

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ችግሮች አንጻር ፥ በማስረጃነት ደረጃው በቲዎሪ ዝቅ የተደረገው "የሁኔታ መኖር" ፥ መወለድን በማረጋገጥ ረገድ በረቂቁ ሕግም ሰፊ ሚና መጫወቱን የሚቀጥል ይመስላል ።[113]

ሐ/ የሕዝብ ክብር መዝገብ

አሁን በሥራ ላይ ያለውም ሆነ (አንቀጽ ፮፻፴፱) ረቂቁ ሕግ (ረቂቁ አንቀጽ ፪፻፫፻፮ እና ፪፻፫፻፯) መወለድ መረጋገጥ ያለበት በልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ[114] መሆኑን በመሠረቱ ይደንገጉና ፥ ይኸው በሌለበት ጊዜ ግን መወለዱ በሌሎች ዘዴዎች እንዲረጋገጥ ይፈቅዳሉ ። በሌሎች አገሮች ብዙ ጊዜ የማያጋጥመው የልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ አለመኖር በኢትዮጵያ አብዛኛውን ጊዜ የሚያጋጥም ስለሆነ ፥

---

108 በዚህ ረገድ ያሉትን ልዩነቶች ለመመልከት የተለየ ጽሑፍ ማዘጋጀት ያስፈልጋል ። ለምሳሌ የፖላንድን የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 85-86 ይመልከቱ ። እንዲሁም የአንዳንድ ምዕራባውያን አገሮችን አመለካከት የሚጠቁመውን (ስለሶቭየት ሕግ የተጻፈው አሁን የሚሠራበትን የሚመለከት ስላልሆነ ማለፉ ይሻላል) በዲ. ላዛክ ፥ ፖሊሽ ፋሚሊ ሎው (ሎይደን ፲፱፻፷፰ ከገጽ 162-165) ይመልከቱ ። አዲስ የሕግ መሻሻሎች ከጋብቻ ውጭ ለተወለዱ ልጅና ለእናቱ ያደላሉ ፤ ለምሳሌ ፥ ፒ ሴዳዊን ፥ ሶቭየት ሌጅስሌሽን አን ማሬጅ ኤንድ ፋሚሊ (ሞስኮ ፥ ፲፱፻፷፫) ይመልከቱ ።

109 ለ "ሁኔታ መኖር" በረቂቁ አንቀጽ ፪፻፭፰ የተሰጠው ትርጉም አሁን በሥራ ላይ ባለው ሕግ አንቀጽ ፮፻፴ (፩) ከተሰጠው ትርጉም ጋር አንድ ነው ።

110 "የመወለዱን የምስክር ወረቀት ለማቅረብ የማይቻል ከሆነ መወለዱ የአባትነት ሕጋዊ ግምት እንዲኖር በሚያደርጉት ሁኔታዎች ሊረጋገጥ ይችላል ።" ይላል ።

111 "በጋብቻው ጊዜ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ያው የእናትዮዋ ባል ነው ። " ይላል ። ይህ አሁን በሥራ ላይ ካለው ሕግ አንቀጽ ፮፻፶፩ አጻጻፍ ጋር አንድ ነው ።

112 የልደቱን ማረጋገጫ ጽሑፍ ለማቅረብ የማይቻል ከሆነ ፥ መወለዱ ፥ ማወቁ የተደረገበትን ሰነድ ወይም አባትነትን ማወቁ በፍርድ እንዲደረግ የታዘዘበትን የፍርድ ቤት ሰነድ በማቅረብ ሊረጋገጥ ይችላል ።" ይላል ።

ይህ የሚሆነው ".....ሰነዶችን ላለማቅረብ በቂ ምክንያት ካለ መወለድ በሁኔታ መኖር ሊረጋገጥ ይችላል" (ረቂቁ አንቀጽ ፪፻፫፭-፫) የሚለውን ፍርድ ቤቶች በጠባቡ ካልተረጎሙት ነው ። ሰነዶቹ መጀመሪያውኑ ባይኖሩስ ?

114 በጥምቀት ማረጋገጫ አይደለም ።

መወለድን በሌሎች ይሽን ያህልም አስተማማኝ ባልሆኑ ዘዴዎች (በተለይም "በሁኔታ መኖር") ማረጋገጥ የግድ አስፈላጊ ነው ። መወለድን በል ደት ማረጋገጫ ጽሑፍ ማረጋገጥ የሞት ፣ የጋ ብቻና የመወለድ ሁኔታዎች በሚመዘገቡበት በሕ ዝብ ክብር መዝገብ ችግሮች መፍትሔ ማግኘት ላይ ይመሰረታል ።

የሕዝብ ክብር መዝገብን የሚመለከቱ ደንቦች አብዛኛውን ጊዜ የፍትሐ ብሔር ሕግ አካል አይ ደሉም ። የሕዝብ ደህንነትን (ጥቅምን) የሚመለከቱ ስለሆነ የአስተዳደር ሕግ አካል ናቸው ። አስተማ ማኝ የሆነ የመወለድ ፣ የጋብቻና የሞት ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚያብራራ መዝገብ መኖር አንድ ዘመናዊ ሕብረተሰብ የአስተዳደር ፣ የማህበራዊ ፣ የኤኮኖሚና የወታደራዊ ዕቅዶቹን በትክክል እንዲ ነድፍ ያስችለዋል ። ሆኖም ይህ በዚህ ሁኔታ ተመ ዝግበው የተያዙ ጽሑፎች በፍትሐ ብሔር ሕግ ላይ የሚኖራቸውን ጠቃሚ ሚና አያስቀረውም ። ምክንያቱም ውጤታቸው በአንድ ሰው መወለድ ፣ ጋብቻ ወይም ሞት ለሚወሰኑ የፍትሐ ብሔር ጉዳ ዮች እነዚህ ጽሑፎች በቅድሚያ የተዘጋጁ አስተ ማማኝ ማስረጃዎች ስለሚሆኑ ነው ። እ ኤ አ በ፲፱፻፵፭ ዓ/ም በወጣው "የማዘጋጃ ቤቶች አዋጅ" መጠነኛ ሙከራ ተደርጎ የነበረ ቢሆንም ፣[115] በ፲፱፻፶፪ ዓ/ም የፍትሐ ብሔር ሕጉ በታወጀበት ጊዜ አጠቃላይ የሆነ የሕዝብ ክብር መዝገብ አሠ ራር ለመፍጠር ተጨባጭ ሁኔታዎች የተሟሉ አል ነበሩም ። ይሁን እንጂ የፍትሐ ብሔር ሕጉ (አን ቀጽ/ታይትል/፩ ምዕራፍ ፫) የክብር መዝገብ ጽሑ ፎቹንና የክብር መዝገብ ሹሞችን የሚመለከቱ የተብራሩ ደንቦችን የያዘ ሲሆን ፣ እነዚህ ደንቦች ግን በመሸጋገሪያ አንቀጽ ፫፻፫፹፭-፩ አማካይነት "በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ትእዛዝ እስከሚወጣበት ቀን ድረስ" በሥራ ላይ እንዳይውሉ ታግደዋል ። በሥራ ላይ እንዲውሉ እስካሁን ያልተደረገ ሲሆን ወደፊትም በቅርቡ የሚቻል አይመስልም ። ሆኖም በቅርቡ በወጣው "የከተማ ኗሪዎች ማህበራትና የማዘጋጃ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ፭፻፬/፲፱፻፹፯" አማ ካይነት በተፈጠሩት ፍሬአማ እድገቶች አኳያ ለወደፊቱ ተስፋ ሊደረግ ይችላል ። በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶/፲፱ መሠረት "ከቀበሌ ኗሪዎች ማህ በራት ግዴታዎች አንዱ" በቀበሌው ውስጥ የሚ ሆኑትን መወለዶች ፣ ጋብቻዎችና ሞቶች የሚ መለከት መዝገብ መያዝ ነው ። በዚህ ሐረግ የተ ጠቆመው ዓላማ በሥራ ላይ እንዲውል ግን ከዚህ በታች ከተመለከቱት አቅጣጫዎች ባንዱ ተጨ ማሪ የአፈጻጸም ደንቦችን ማውጣት ያስፈልጋል ፤ ይኸውም ፤

— ወረዳ በወረዳና ቀስ በቀስ የታገደውን የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ /ታይትል/፩ ምዕራፍ ፫ አንዳንድ አንቀጾች በሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ ፤ ወይም

— የታገደውን የፍትሐ ብሔር ሕግ ክፍል በሌላ ተስማሚ ክፍል በመተካት ከላይ እንደተጠ ቆመው ቀስ በቀስ በሥራ ላይ እንዲውል በማ ድረግ[116] ሊሆን ይችላል ።

የሕዝብ ክብር መዝገብን የሚመለከተው ክፍል አለመሟላት ከሚያስከትላቸው ውጤቶች ፣ በተ ለይም የሚከተሉት በመወለድ ሕግ ተመራማሪ ዎች ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል ።

ቀደም ሲል እንደተጠቆመው ብቸኛና ትክክለኛ የሆነው የማያከራክር የእናትነት (የሪፖርቱን ሀ-፪ ይመልከቱ) እና የአባትነት (የሪፖርቱን ለ-፪) ማረጋገጫ ዘዴ (የሪፖርቱን የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር ፯ ይመልከቱ) የሁኔታ መኖር ነው ። በዚህ ደረጃ በአንቀጽ ፯፻፳፱ (እና አንቀጽ ፯፻፴-፩) ላይ "የልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ" የሚለው ሐረግ በታ ገደው የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ (ታይትል) ፩ ምዕራፍ ፫[117] የተመለከተውን ጽሑፍ እንጂ ሌላ ለማለት አለመሆኑን ማብራራት ያስፈልጋል ። "የልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ" የሚለው ሐረግ ከአጠቃላይ ሁኔታዎች ጋር መታየት አለበት ። በ"ሕግ" መሠረት በተዘጋጀ "ጽሑፍ" የጋብቻን መረጋገጥ የሚደነግገው አንቀጽ ፯፻፶፰ ፣ ለዚሁ አንቀጽ አፈጻጸም "ሕግ" ማለት የሕዝብ ክብር መዝገብን እና ሹሞችን የሚመለከተው የታገደው የምዕራፍ ፫ አንቀጾች መሆናቸውን ከሚጠቁሙት ከአንቀጽ ፯፻፭(፫) እና ፯፻፯ (፫) ጋር አብሮ እንደ ሚነበበው ሁሉ ፣ መወለድ በልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ መረጋገጥ ያለበት መሆኑን የሚደነግገው አንቀጽ ፯፻፳፱ እንደዚሁ ፣ የተባለው ጽሑፍ የታ ገዱት አንቀጾች ከታወጁ በኋላ በእነዚሁ መሠረት የተዘጋጀ መሆኑን ከሚጠቁሙት ከሌሎች የቤተ ሰብ ሕግ አንቀጾች ጋር አብሮ መታየት ይኖርበ ታል ። በእርግጥም "የልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ" በመጀመሪያ ደረጃ የሚገኝ የመወለድ ማረጋገጫ መሆኑ ትርጉም የሚኖረው ፣ ለዚሁ ሰነድ ከፍተኛ የአስረጅነት ድርሻ[118] የሚሰጠው የታገደው አን ቀጽ ፯፻ (ወይም ሌላ ተመሳሳይ አንቀጽ) ከሌሎች የሕዝብን ክብር መዝገብ ትክክለኛነት ከሚያረጋ

115 አዋጅ ቁጥር 74 ፣ አንቀጽ ፱ ። የማዘጋጃ ቤት ባለሥልጣን ጋብቻ በሚያስፈጽምበት ጊዜ እንኳን የጋብቻውን ውል በመዝገብ አይመዘግብም ።

116 የሕግ አሻሻጩ ከሚቴ የታገደውን ክፍል የሰረዘው ሲሆን በምትኩም ሌላ አሳስገባም (ጉዳዩን ለአስተዳደር ሕግ በመተው ይሆን ?)

117 አንቀጽ ፫፻፫፻፴፭(፩) ለምንነጋገርበት ርዕስ አግባብ የሌላቸውን አንቀጾች ፶፮ ፣ ፭፭ ፣ ፭፰ እና ፭፻፴፪ አያግድም ።

118 በአንቀጽ ፯፯ መሠረት ደንበኛ ሆነው የተመዘገቡ የክብር መዝገብ ጽሑፎችን ለመቃወም ማስረጃ ለማቅረብ "የዳኞች ፈቃድ ያስፈልጋል" ። ስለ ሆነም በእርግጥ አባት ሳይሆን በእናትየዋ አባት መሆኑ ተጠቅሶ ይኸው በደንበኛ በክብር መዝገብ የተመዘገበበት ሰው ይኸው የምዝገባ ስህተት እን ዲታረምለት ለመጠየቅ በመጀመሪያ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ማግኘት አለበት (አንቀጽ ፭፻፴፭) ።

ግጡ የታገዱ አንቀጾች ጋር አብሮ መታወጁን መግ
ንዘብ ሲቻል ብቻ ነው ። እነዚህም የሚገኙት ፤

— በአንቀጽ ፸፬-፹፱ (የሕዝብ ክርብ መዝገቦችን ይመለከታል) ፤

— በአንቀጽ ፺-፺፰ (በመዝገቦቹ የሚመዘገቡትን ጉዳዮች ይመለከታል) ፤

— በአንቀጽ ፺፱-፩፻፫ (በተለይም የልደትን ማረ
ጋገጫ ጽሑፍ ይመለከታል) ፤ እና

— በአንቀጽ ፩፻፬-፩፻፲፩ (በሕግ መሠረት አለ
መፈጸም የሚያስከትላቸውን ቅጣቶች ይመ
ለከታል) ነው ።

በተለይም ከዚህ የሚከተሉትን በጥሞና መመልከት ይገባል ፤

ሀ/ የልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ ሕጻኑ በተወለደ በሦስት ወራት ውስጥ በሕዝብ ክብር መዝገብ መመዝገብ አለበት (አንቀጽ ፷፱-ሀ) ። ይህ የሆነው ሁኔታውን የሚገልጹት ሰዎች በሕይወት እያሉና ነገሩን "ሳይዘነጉት" ምዝገባው የሚደረግ መሆኑን ለማ ረጋገጥ ነው ። ጽሑፉ በክብር መዝገብ ካልተመዘ ገበ ወይም በክብር መዝገብ እንዲገባ የተደረገው የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ከሆነ (በፍርድ መሠረት ካልሆነ በስተቀር) በመዝገቡ ውስጥ እንደተጻፉ ጽሑፎች ሳይሆን እንደተራ ማስረጃ ብቻ ይቆጠራል (አንቀጽ ፺፰ እና ፷፫) ።

ለ/ የልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ አባት እና እናትን መግ
ለጽ አለበት (አንቀጽ ፺፱-መ) ።

ሐ/ ሕፃኑ ሲወለድ ይኸው በአባቱ ፥ ወይም እሱ ይህን በማያደርግበት ጊዜ በእናቱ (ወይም በአሳዳጊው ወይም በጠባቂው) አለዚያም መወለዱን የሚያ ውቅ ከሆነ በሕዝብ ክብር መዝገብ ሹመ መገለጽ አለበት (አንቀጽ ፩፻፩) ። በሌሎች አገሮች እንደሚ ደረገው ሁሉ[119] ይህ ግዴታ በሌሎች የልጁን መወለድ ባዩ ሰዎች ላይም ቢኖር ጥሩ ነው ።

መ/ መወለዱን የመግለጽ ግዴታ ያለባቸው ሰዎች በተ ጠቀሰው የሦስት ወር ጊዜ ውስጥ መወለዱን ሳይገ ልጹ ቢቀሩ ፥ ወይም ለመግለጽ እምቢተኛ ቢሆኑ ፥ ወይም እያወቁ የተሳሳተ መግለጫ ቢሰጡ በሕግ ይቀጣሉ (አንቀጽ ፩፻፸፪-፩፻፸፫) ።

የእነዚህ ዓይነት አንቀጾች አለመኖር የሕዝብ ክብር መዝገብ ለመንግሥት ስታቲስቲክስ የሚያበረክተውን ዋጋ ላይነካው (ላይጎዳው) ይችላል ። ሆኖም መወለድን ማረጋገጥን ጨምሮ ፍትሐ ብሔር ሕግን በሚመለከት የሚያበረክቱትን የማስረጃነት ዋጋ በጣም ይቀንሰዋል (ይጎዳዋል) ። እንዲያውም ትክክለኛ ለመሆናቸው መጠ ባበቂያ ካልተደረገላቸው ከሕዝብ ክብር መዝገቦች የሚ ገኝ ሐሳብ በረቂቁ ሕግ አንቀጽ ፪፻፫፮-፪፻፫፯ የሁለተኛ ደረጃ ከተሰጣቸው ሰነዶች ከሚገኝ ሐሳብ ያነሰ ሊሆን ይችላል ።

በመጨረሻ የታከለ

በዚህ ሪፖርትም ሆነ በተጨማሪው መወለድን በሚ መለከት ረገድ መሠረታዊ የሆኑ አማራጭ የፖሊሲ ሐሳቦች አላቀረብሁም ። ይሁን እንጂ በዚህ የመጨረሻ ማከያ ላይ የኢትዮጵያ የመወለድ ሕግ በጣም ላላ ባለ አኳኋን መሻሻል ያለበት ስለመሆኑ (የማከያውን ለ-ኗ ይመልከቱ) ያለኝን አስተያየት በአጭሩ ብጠቁም እንደ ስህተት የሚቆጠር አይመስለኝም ። መሻሻል ያለበት መሆኑን የሚደግፉ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ/ ይህ ፖሊሲ በብዙ ሶሻሊስትና አንዳንድ ሶሻሊስት ባልሆኑ አገሮች[120] ግልጽ በሆኑ ሰብአዊ እና/ ወይም የእኩልነት ምክንያቶች በሥራ ላይ ውሏል ።

ለ/ በተለይም ይህ ፖሊሲ ብዙ አባት የለሽ ልጆች ባሉበትና እነዚህንም በድጋፍ ለማሳደግ (ሶሻል ዌልፌር) መንግሥት ሕግ ለማውጣት በማይችል በት በኢትዮጵያ ሁኔታ ተቀባይነት ሊኖረው ይገ ባል ።

ሐ/ አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ በልማዳዊ ሁኔታ ማሳደግ የሚያስከትለው ወጭ በኢትዮጵያ በጣም ቀላል ስለሆነ ፥ ከጋብቻ ውጭ የወለደ አባት ይኸ ንን ወጭ በቀላሉ ሊሸፍነው ይችላል ።

ስለዚህ የሚከተሉት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ሐሳብ አቀርባለሁ ።

ሀ/ በአንቀጽ ፺፱፬ የተደነገገው የአባትነት ሕጋዊ ግምት በአንቀጽ ፺፱፰ በተመለከተው ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርንም በሚመ ለከተው ረገድ ተፈጻሚነቱ እንደተጠበቀ እንዲ ቆይ ፤

ለ/ ከአንቀጽ ፺፱፬-፺፱፰ ያለውን በመሰረዝ በም ትኩ ልጁ ከተወለደበት ጊዜ በፊት ከ፫፱ እስከ ፩፻፹ ቀኖች ባለው ጊዜ ውስጥ ከእናትዮዋ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በፈጸመ ሰው ላይ በፍርድ አባትነቱን እንዲያውቅ ክስ ለማቅረብ የሚያስችሉ አንቀጾች ማስገባት ። በዚህ ሁኔታ ለሚቀርብ ክስ የሚከተሉት እንደመከላከያ ሊወሰዱ ይችላሉ ።

ሀ/ በተባለው ጊዜ ውስጥ እናትዮዋ ግልጽ በሆነ ሁኔታ በሽርሙጥና በመሰማራት የቆየች ከ ሆነ ፤ ወይም

119 ለምሳሌ የፈረንሳይ ፍትሐ ብሔር ሕግን አንቀጽ ፶፮ ይመልከቱ ።

120 በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 118 የተጠቀሰውን ይመልከቱ ። እንዲሁም ጅ.ጋሪሲያ ካንቴሮ ፥ "ስ ሲቲዌሰን ጁሪዲክ ዴዝ ኤንፋንት ኔስ ሆርስ ማሪጅ" በ ራፖርትስ ዲኔሩ አ ኮንግሬስ ኢንተርናሲዮናል ዱ ድርዋት ኮምፓሬ (ብራስልስ ፥ ፲፱፻፸፯) ውስጥ የተጻፈውን ለምሳሌ ገጽ 348 ይመልከቱ ።

ለ/ ተከሳሹ ለመውለድ የማይችል መሆኑ[121] ወይም በደም ምርመራ የልጁ አባት አለመ ሆኑ ከተረጋገጠ ፤
ወይም

ሐ/ በተባለው ጊዜ ውስጥ እናትዮዋ ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመች ከሆነና የዚሁ ሰው አባት መሆን የበለጠ አስተማ ማኝ[123] ከሆነ ። ለዚህ መመዘኛዎች ሰው የው ከሴትዮዋ ጋር ግንኙነት ያደረገበት ጊዜ ብዛት ፣ ወይም/እና ግንኙነቱ የተደረገበት ጊዜ (አማካይ መሆኑ) ፣ ከልጁ ጋር ያለው መመሳሰል ፣ የባለሙያ (ጀይኖኮጅስት) አስተያየት ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ ።

መ/ በመጨረሻ ይርጋ[124] ።

በመጨረሻም ፣ የሕግ አሻሻዩ ኮሚሽን አባሎች በሙሉ ወንዶች ስለሆኑ ፣ ከዚህ በላይ የተጠቆሙትን ነጥቦች በሚመለከት ረገድ የኢትዮጵያን የሴቶች ማህ በር ማማከሩ ጠቃሚ ሊሆን እንደሚቻል መጠቆም እወዳለሁ ።

---

121 ለጽንስ መከላከያ የሆኑ መድኃኒቶች ይወሰዱ የነበረ መሆኑን መጨመሩ በማስረጃ ረገድ ከፍተኛ ችግሮች ያስከትላል ።

122 ኤክሰፕቲቭ ነሎ የም ንኩምቢንቱም ተብሎ የሚታወቀው መከላከያ ነው ።

123 የፖላንድ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ ፹፭(፪) የሚደነግገው (ይህ በ፲፱፻፹፰ ዓ/ም በተደረገው የሕግ መሻሻል አልተለወጠም) ። እንዲሁም ለዞክን ከገጽ 164-165 ይመልከቱ (በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 108 ተጠቅሶአል) ።

124 በአንዳንድ አገሮች ልጁ የሚያቀርበው ክስ (ብዙ ጊዜ በእናትዮዋ የሚቀርብ) ጥብቅ የይርጋ ገደብ አለበት ። በጣም አጭር በሆነበት በአውስትሪያ አንድ ዓመት ነው ። (ሲቪል ጀስትዝቡች ፣ አንቀጽ ፫፻፳) ። ከላይ የተጠቀሰውን ለዞክን የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 108 ገጽ 161 ቁጥር 130 ይመልከቱ ። ዓላማው የማይረቡ ክሶችን በማምጣት የሚፈጸመውን ለመቆጣጠር ይመስላል ። ይህ የይርጋ ገደብ በሕጋዊ ግምት ወይም በማወቅ ወይም በልደት ማረጋገጫ ጽሑፎች ወይም በሁኔታ መኖር የሚመሠረቱ መወለዶችን አይመለከትም ።

ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ሦስተኛ መንግሥታት

ዶክተር ዝጀሰዋብ ባትስዋብ ጋሊትስኪ*

ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መንግሥታትን የሚያስ ገድዱ የሥነ ምግባር ሕግጋት በተስማሚዎቹ መንግ ሥታት ላይ ይመሠርታሉ ። ስምምነቶቹም ዓለም አቀፍ ፣ የተወሰነ ክፍለ ዓለምን የሚመለከቱ ወይም የተወሰኑ መንግሥታትን የሚመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ ። ተስማ ሚዎቹ መንግሥታትም በስምምነቶቹ የገቡባቸውን ግዴታዎች የሚጻረሩ ድርጊቶች መፈጸም የለባቸውም ።

በፍትሐ ብሔር ታዋቂ በሆነው እና ከሮማውያን ፍትሐ ብሔር በተወሰደው "ፓክታ ተርቲስ ነክ ኖሰንት ነክ ፕሮሱንት" (ስምምነቶች ተፈጻሚነት የሚኖራ ቸው በተስማሚዎቹ ወገኖች ብቻ ነው) በሚለው መርህ (ማክሲም) መሠረት ስምምነቶች በሦስተኛ ወገኖች ላይ መብትም ሆነ ግዴታ ሊያስከትሉ አይችሉም ። ይህ መርህ በፍትሐ ብሔር የውል ሕግ ጠቅላላ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ሲሆን[1] በዓለም አቀፍ ሕግ ደግሞ በአገሮች ነፃነት እና የበላይ ገዥነት (ሶቨሪይኒቲ) ሕግ ጋት አንፃር ሲታይ ተጨማሪ ድጋፍ አለው ። ስለሆነም ፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተፈጻሚነት ሊኖራቸው የሚ ገባው በተዋዋይ ወገኖች መካከል ብቻ ስለሆነ ፣ በመ ሠረቱ በስምምነቶቹ ተካፋይ ባልሆኑ ሦስተኛ አገሮች ላይ መብትም ሆነ ግዴታ አይመሠርቱም ።

ይህ መሠረተ ሐሳብ ተቀባይነት አግኝቶ የሚሠራበት ለመሆኑ ከስምምነት ለሚመነጭ ግዴታ መሠረቱ ፈቃድ ነው[2] በሚል መርህ ከተመሠረቱ የመንግሥታት አድራጎ ቶች ፣ የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች እና የሕግ ምሁራን ጽሑፎች በቂ ማስረጃ ይገኛል[3*] ። የዚህንም መ ሠረተ ሐሳብ ተግባራዊ መሆን በሦስተኛ አገሮች ላይ ሊፈ ጸሙ ከሚይችሉ መብቶችና ግዴታዎች ማየት ይቻላል ።

ለምሳሌ ፣ "በፖሊሽ አፐር ሳይለስያ ላይ ጀርመን አለኝ ስላለው መብት" ቋሚው የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ ጦርነቱን ለማቆም የተደረጉትን ልዩ ልዩ ስምምነቶች በማስመ ልከት እንደሚከተለው ወስኖአል ፡-

"ስምምነት ተፈጻሚ የሚሆነው በተስማሚዎቹ አገ ሮች ላይ እንጂ በሦስተኛ አገሮች ላይ በቀጥታ ተፈጻሚ ነው ማለት እንደማይቻል ሁሉ ጦርነትን የማቆም ስም ምነት ጠባይ ያለው ሰነድ ለሦስተኛ አገሮች በማንኛ ውም ሁኔታ ሁሉ መብት ይሰጣል ብሎ መገመት ፈጽሞ አይቻልም ። ስምምነት ሕግ የሚመሠርተው በተስማ ሚዎቹ መካከል ብቻ ነው ።"[4] በዚህ መሠረት ፍርድ ቤቱ ፖላንድ በጦርነቱ ማቆም ስምምነት ተካፋይ ስላ ልነበረች በስምምነቱ መጠቀም አትችልም በማለት ወስኗል ።

እንደዚሁም ፣ "የቾርሎው ፋብሪካ"ን በሚመለከት ጉዳይ ቋሚው ፍርድ ቤት ፖላንድ በጦርነት ማቆም ስምምነቱ ተካፋይ ስላልነበረች በስምምነቱ መጠቀም አትችልም በማለት ወስኗል ።[5]

በሦስተኛ አገሮች ላይ ወደፊት ግዴታን ይመሠር ታሉ ተብለው የሚገመቱትን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሚመለከት አንፃር "የአደር ወንዝ ዓለም አቀፍ ኮሚ ሽን የወሰን ክልል" በሚመለከት ጉዳይ ቋሚው ፍርድ ቤት በብዙ አገሮች መካከል ተደርጎ የነበረው የባርሰሎና ስምምነት በስምምነቱ ተካፋይ ባልነበረችው በፖላንድ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ብሎ ለመወሰን አልፈለገም ። ፍርድ ቤቱ ፣ "የቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት[6] አን

---

*ረዳት ፕሮፌሰር ሕግ ፋኩልቲ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፣ በዓለም አቀፍ ሕግ ሌክቸረር ፣ ዎርሶው ዩኒቨርስቲ ።

1 በሮም የውል ሕግ የታወቁትን "ግዴታ ሦስተኛ ወገንን አይመለከትም (አብሊጋስዮ ተርትዮ ኖን ኮንትራሂቱር) ፣ ስምምነቶች ከተስማሚዎቹ ውጭ በሌሎች ሰዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም (ፓክታ ኖን አብሊጋንት ኒሰጀንቱስ ኢንተር ኳስ.ኢኒሸያ) የሚሉትን መርሆዎች (ማክሲም፡ስ) ይመለከቷል ።

2 "በዓለም አቀፍ ስምምነቱ ያልተካፈሉትን ብሔሮች (ሦስተኛ ብሔሮች ተብለው የሚጠሩ) በምንነቱ ሊመለከታቸው የማይችል (ረብ ኢንተር አልየስ አክታ) በመሆኑ ስምምነቶች ከተስማሚዎች ውጭ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ጥቅም ሆነ ግዴታ አያስከትሉም (ፓክታ ተርቲስ ነክ ኖስንት ነክ ፕሮሱንት) የሚለው መሠረተ ሐሳብ በሕጋዊ አስተሳሰብ ሆነ በተክክለኛ አስተሳሰብ (ከሞን ሰንስ) የተደገፈ ነው ።" ሎርድ ማክነይር ፣ ዘሎው ኦፍ ትሪቲስ ፣ (ሎንደን ፣ እ ኤ አ ፲፱፻፴፩) ገጽ 309 ።

3 ቾ.ኤ.ሩስ ፣ ፕሪንሲፕ ጀንሮ ዱ ድርዋ ኢንተርናስዮናል ፕብሊክ ፣ (ፓሪስ እ ኤ አ ፲፱፻፵፱) ቦልዩም 1 ፣ ገጽ 453 ። በተጨማሪ የሚከተሉትን ይመለ ከቷል አር.ኤፍ.ሮክሰቡር ፣ ኢንተርናሽናል ኮንቨንሽንስ ኤንድ ተርድ ስቴትስ ፣ (በስቶን እ ኤ አ ፲፱፻፲፯) ገጽ 19 ፤ ኤ.ካቫል የሪ ፣ "ረገል ጀነራል ዱ ድርዋ ደ ላፕይ ፣ ረስወይ ደ ኩር ፣ አካዳሚክ ደ ድርዋ ኢንተርናስዮናል (ዘ ሕግ ፣ እ ኤ አ ፲፱፻፴፱) ቦልዩም 26 ፣ ገጽ 257 ፣ ዲ አምዚሎቲ ፣ ኩር ደ ድርዋ ኢንተርናስዮናል ፣ (ጂ ጊደል ትርጉም ፣ ፓሪስ እ ኤ አ ፲፱፻፴፱) ፣ ገጽ 414 ፣ እና ኤል.ኤፍ.ኤል. ኦፐንሽይም ፣ ኢንተርናሽናል ሎው ኤ ትሪቲስ ፣ (፰ኛ እትም በኤች ላውተርፓሽት ፣ ሎንዶን ኒውዮርክ እ ኤ አ ፲፱፻፶፭) ፣ ቦልዩም ፩ ገጽ 995

* ለአተረጓጐሙ ሲባል የጸሐፊው የግርጌ ማስታወሻ የትርጉሙ የግርጌ ማስታወሻ ፤ የጸሐፊው የግርጌ ማስታወሻ ፤ የትርጉሙ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር ሆኖዋል ።

4 ፓብሊኬሽንስ ኦፍ ዘ ፕሮማነንት ኮርት ኦፍ ኢንተርናሽናል ጀስቲስ ፡ ጀጅመንትስ ፡ ኦርደርስ ኤንድ አድባይዘሪ ኦፒንየንስ ፡ (እ ኤ አ ፲፱፻፳፯) ሲርይስ ኤ ቁ 7 ገጽ 24-29

5 ፒ.ሲ.አይ.ጀ. ፐርማነንት ኮርት ኦፍ ኢንተርናሽናል ጀስቲስ ማለትም ቋሚው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት) ፓብሊኬሽንስ (እ ኤ አ ፲፱፻፳፰) ሲርይስ ኤ ቁ 17 ገጽ 43-46 ፤ አንዋል ዳይጀስት 1927-28 ጉዳይ ቁ. 286 ገጽ 416-17 ትንም ይመለከቷል ።

6 ይህ አንቀጽ ዓለም አቀፍ ይዘት አላቸው ተብለው የሚገመቱትን ባሕረ ሰላጤዎችና ወንዞችን በሚመለከት ረገድ በዓለም አቀፍ ስምምነቱ ከአንቀጽ ፫፻፴፪-፫፻፴፯ የተደነገጉት ሕጎች "በተባበሩት ኃያላን መንግሥታት (አላይድ ኤንድ አሶስየትድ ፓወርስ) በሚደረገው እና በመንግሥታት ሕብረት (ሊግ ኦፍ ነሽንስ) በሚጸድቀው ዓለም አቀፍ ስምምነት ሕግ ሊተኩ እንደሚችሉ እና ይህ ዓለም አቀፍ ስምምነት በተለይ በአደር ወንዝና በሌሎችም ተፈጻሚነት እንደሚኖረው ይደነግጋል ።

ቀጽ ፫፻፴፭ትን መሠረት በማድረግ ነገሩን ብናየው እንኳ ፥ የቫርሰሎና አለም አቀፍ ስምምነትን ማጽደቅ አስፈላጊ አይሆንም ለማለት ስለማይቻል የቫርሰሎና ዓለም አቀፍ ስምምነት ሳይጸድቅ በቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ ፫፻፴፭ የተደነገጉትን ውጤቶች ያስከትል ማለት አይቻልም”[7] ሲል ወስኗል ።

በተመሳሳይ “በአፐር ሳቮይ ፍሪ ዞንስ እና በጀኽስ ወረዳ ጉዳይ” ቋሚው ፍርድ ቤት ፍሬ ዞንስን ለማስ ቀረት የተደረገው የቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት ክፍል ፪ ፥ አንቀጽ ፭፻፴፭ ፤

“ስዊትዘርላንድ በስምምነቱ ስላልተካፈለች ከስም ምነቱ በኋላ የፈቀደችውን ግዴታ በሚመለከት አንፃር ካልሆነ በስተቀር ስምምነቱ ሊፈጸምባት አይችልም”[8] በማለት ወስኗል ።

ማክስ ሁበር የተባሉት ዳኛ ፖልማስ ደሴት በተ ባለው ስፓኝ ከሌሎች አገሮች ጋር ባደረገችው ዓለም አቀፍ ስምምነት ስፓኝ በፖልማስ ደሴት ያላትን መብት ሌሎች አገሮች አውቀውላታል በማለት የቀረበላቸውን ክርክር መርምረው በሰጡት ውሳኔ ፤

“የስምምነቱ ትክክለኛ አተረጓጐም ምንም ቢሆ ንም ፥ የሦስተኛ ነፃ አገሮችን መብቶች ያስቀራል ብሎ መተርጎም እንደማይቻል ግልጽ ነው ። ‘ፊሊፒንስ’ የስፓኝ ግዛት መሆኗን በማረጋገጥ ስፓኝ ከሦስተኛ አገሮች ጋር የፈጸመቻቸው ስምምነቶች በኔዘርላንድስ ላይ ተፈጻሚ ሊሆኑ እንደማይችሉም ግልጽ ነው”[9] በማለት ይህን መሠረተ ሐሳብ በመከተል ወስነዋል ።

የሐርባርድ ምርምር (ሪሰርች) ስምምነቶችን በሚመ ለከት ረገድ ይህን ተቀባይነት ያገኘውን የዓለም አቀፍ ሕግ እንደሚከተለው ገልጾታል ፥ “አንድ ስምምነት በስምምነቱ ተካፋይ ባልሆነ አገር ላይ ግዴታን ሊያስ ከትል አይችልም” ።[10]

በአሁኑ ዓለም አቀፍ ሕግ “ፓክታ ተርቲስ ነክ ኖሰ ንት ነክ ፕሮሱንት” በሌሎች አገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት ከሚለው ሐሳብ ጋር በቀጥታ የተ ያያዘ ነው ።[10(ሀ)]

በዓለም አቀፍ ሕግ ኮሚሽን በተዘጋጀው ረቂቅ[11] የተ መሠረተው እ ኤ አ በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም የወጣው ስምምነ ቶችን ስለሚመለከት ሕግ የቨየና ዓለም አቀፍ ስምም ነት (ኮንቨንሽን) አንቀጽ ፴፬ እንደሚከተለው ይደነ ግጋል ፡-

“አንድ ስምምነት በሦስተኛ አገር ፈቃድ ካልሆነ በቀር መብትም ሆነ ግዴታ ሊያስከትል አይችልም ።”

የዓለም አቀፍ ኮሚሽን እ ኤ አ በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ለዚህ አንቀጽ ለጊዜው ሰጥቶት የነበረውን “የስምምነቶች ውጤት በተስማሚ ወገኖች ላይ ብቻ ተፈጻሚነት እን ዲኖራቸው የሚያዝ ጠቅላላ ሕግ” የሚለውን ርዕስ በመጨረሻ “ሦስተኛ ብሔሮችን የሚመለከት ጠቅላላ ሕግ” በሚል ርዕስ ተክቶታል ። እንደዚሁም ይህ “አንድ ስምምነት ተፈጻሚነት የሚኖረው በተስማሚዎቹ ወገ ኖች መካከል ብቻ ነው ” ተብሎ ተደንግጎ የነበረ ውን አንቀጽ ለግለሰቦች ተፈጻሚነት አይኖረውም ወደ ሚል ያልሆነ ግምት እንዳያመራ በማሰብ ከላይ በተጠ ቀሰው አንቀጽ ተተክቷል ።

“ፓክታ ተርቲስ ነክ ኖሰንት ነክ ፕሮሱንት” የሚ ለው መርህ በዓለም አቀፍ ሕግ የተለየ ሁኔታን በሚመ ለከት ረገድ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ወይስ አይኖረ ውም ? የሚለው ጥያቄ ሁልጊዜ አከራካሪ ነበር ። ኮሚ ሽኑንም በሐሳብ የከፋፈለው ይኸው ነጥብ ነበር ። ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተካፋይ ባልሆኑ ወገኖች ላይ ግዴ ታን የማያስከትሉ በመሆናቸው ፥ ግዴታን በሚመለከት ረገድ መርሁ ምን ጊዜም ቢሆን ተፈጻሚ ነው በሚለው ሐሳብ ላይ የኮሚስዮኑ አባላት ሙሉ በሙሉ የተስማሙ ሲሆን በሐሳብ የተለያዩት ዓለም አቀፍ ስምምነቶቹ ተካፋይ ላልሆኑ ወገኖች መብት ያስገኛሉ ወይስ አያስ ገኙም በሚለው ጥያቄ ላይ ነበር ።

በዚህ መሠረተ ሐሳብ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን አን ዳንድ ጊዜ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ባልተካፋሉባቸው

---

7 ፒ ሲ አይ ጀ ፓብሊክሽንስ (እ ኤ አ ፲፱፻፳፱) ሲሪይስ ኤ ፥ ቁ 23 ፥ ገጽ 21 ።

8 ከላይ የተጠቀሰው (እ ኤ አ ፲፱፻፴፪) ሲሪይስ ኤ/ቢ ፥ ቁ 46 ፥ ገጽ 141 ።

9 ሪፖርትስ አፍ ኢንተርናሽናል አርቢትራል አዋርድስ ፥ (የተባበሩት መንግሥታት እትም) ቦልዩም 2 ፥ ገጽ 31 ።

10 “ሪሰርች ኢን ኢንተርናሽናል ሎው አፍ ትራቲስ” አሜሪካን ጀርናል አፍ ኢንተርናሽናል ሎው ፤ (እ ኤ አ ፲፱፻፴፭) 29 ቮልዩም ማሚያ (ሳፕሊመንት) ።

10(ሀ) ኢንሳይክሎፒድያ ጥራዋም የድዝይና ሮዶወጎ ኤ ስቶሉንኮው ም ድዝይናሮድ ውይች (የዓለም አቀፍ ሕግና ግንኙነት ኢንሰይክሎፒድያ) ፥ (ዋርሶው እ ኤ አ ፲፱፻፷፮) ፥ ገጽ 253 ።

11 ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ሦስተኛ ብሔሮችን በሚመለከት ረገድ በተባበሩት መንግሥታት የዓለም አቀፍ ሕግ ኮሚሽን የቨየናው ዓለም ዓቀፍ ስምምነትን ባዘጋጀበት ጊዜ የተደረገውን ከፍተኛ ዋናት መጥቀሱ አስፈላጊ ነው ። ኮሚሽኑ እ ኤ አ በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ባደረገው የመጀመሪያ ስብሰባው የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሕግጋት በሕግ ለመቀረጽ (ከዲፊከሽን) አመቺ ናቸው በማለት ከገለጻቸው ሕግጋት አንዱ ነበር ። ነገር ግን ፥ ኮሚሽኑ በሥራ ብዛት ምክንያት እስከ እ ኤ አ ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ድረስ ምንም ለማድረግ አልቻለም ነበር ። እ ኤ አ በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ባደረገው አሥራ ሦስተኛ ስብሰ ባው ፥ ኮሚሽኑ በፊት መርጧቸው በነበሩው አዘጋጆች በተጠቆመው መሠረት የተቀረጸ ሕግ (ኮድ) ከማዘጋጀት ይልቅ ተስማሚ ለሆነ ኮንቨንሽን (ስም ምነት) መሠረት የሚሆን የዓለም አቀፍ ስምምነት ሕግ በሰር ሐምፈሪ ዋልዶክ ኃላፊነት እንዲዘጋጅ ወሰነ ። በአሥራ አራተኛው (እ ኤ አ በ፲፱፻፷፪ ዓ/ም) ፥ በአሥራ አምስተኛው (እ ኤ አ በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም) እና በአሥራ ስድስተኛው (እ ኤ አ በ፲፱፻፷፬ ዓ/ም) ስብሰባው ኮሚሽኑ በአዘጋጁ. በቀረበለት ሪፖርት መሠረት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ከሚመለከተው ሕግ የመጀመሪያዎቹን ሦስት ክፍሎች አጸደቀ ። መንግሥታት ያቀረቡለትን አስተያ የቶች መሠረት በማድረግ ፥ ኮሚሽኑ ክፍሎቹን ጎአስ ከፍሎቹንና የአንቀጾቹን ትዶም ተከተል በማሻሻል የመጨረሻውን የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሕግ እ ኤ አ በ፲፱፻፷፮ ዓ/ም አጸደቀ ። በዚህ ጉዳይ ፥ ሪፖርት ዘ ኢንተርናሽናል ሎው ኮሚሽን አን ዘ ወርክአፍ ኢትስ ኤይቲንዝ ሰሽን (የዓለም አቀፍ ረቂቅሕግ ኮሚሽን አሥራ ስምነተኛ ስብሰባ ዘገባ)— ጀኔቭ—ሚይ4—ጁላይ29፤ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ድራፍት አርቲክል አን ዘ ሎው አፍ ትሪቲስ—ጀኔቭ ኤኤስ አፍ ሬክ 21 ፥ ሳፕሊ (ማሚያ) ቁ 9 በኤ/6309 /ሪቭ 1/ ይመለከቷል ። እነዚህ ረቂቅ አንቀጾች እ ኤ አ በ፲፱፻፷፰-፲፱፻፷፱ በቨየና ለተደረገው ዲፕሎማቲክ ስብሰባ መሠረት ሆነው የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሕግ ስምምነት አዘል በሆነ መልክ ተረቀቀ ።

ሦስተኛ አገሮች ላይም በአንዳንድ ሁኔታዎች ተፈጻሚ ነት እንዳላቸው አያከራክርም ። አከራካሪ የሚሆነው እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ተቀባይነትና ሕጋዊነት የሚ ኖራቸው በምን ዓይነት ጉዳዮችና እስከምንስ ድረስ ነው የሚለው ነጥብ ነው ። በመሠረቱ እነዚህ የተለዩ ሁኔታዎች በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ ። እነዚህም ፡ ፩/በሦስተኛ አገሮች ላይ ግዴታዎችን የሚያስከትሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች (ፓክታ ኢን ደትሪመንቱም ተርቲ) ፡ እና ፪/ ለሦስተኛ አገሮች መብቶችን የሚያስ ገኙ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች (ፓክታ ኢን ፋቮሬም ተርቲ) ናቸው ።

እነዚህን ሁለት ሁኔታዎች ከማየታቸን በፊት ፡ ከነ ዚህ ሁለት ሁኔታዎች ውጭ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሦስተኛ አገሮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑባቸውን ሁኔ ታዎች መመርመር አስፈላጊ ይሆናል ።

ለምሳሌ ተስማሚዎቹ አገሮች በፊት ሰጥተውት ከነ በረ ይበልጥ ጥቅም የሚሰጡ አንቀጾች የያዘ የንግድ ዓለም አቀፍ ስምምነት ከተስማሚዎቹ አገሮች ጋር በሌላ ስምምነት ከሁሉም በበለጠ የመታየት መብት (ሞስት ፌቨርድ ኔሽን ክሎዝ) ባገኙ ሦስተኛ አገሮችም ተፈጻሚ ይሆናል ። ነገር ግን እነዚህን አገሮች በሙሉ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያያይዝ ተቀባይነት ያገኘ ሁኔታ አለ ። በመሆኑም ‘‘ሦስተኛ አገር ማለት በዓለም አቀፍ ስምምነት ያልተካፈለ አገር ማለት ነው’’12 የሚለ ውን በቬየና ስምምነት የሚገኘውን ጠቅላላ ሕግ አይ ከተልም ።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አንድ አገር ምንም እንኳን በአ ንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት ተካፋይ ባይሆንም በሌላ ዓለም አቀፍ ስምምነት ግዴታውን ከተቀበለ ያልተካፈ ለበትን ስምምነት ማክበር ይኖርበታል ። ለምሳሌ ‘‘የፖ ላንድ ዜጎችን አያያዝ በዳንዚግ’’ በሚለው ጉዳይ ቋሚው ፍርድ ቤት በቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት ክፍል ፪ አንቀጽ ፭፻፬ አንፃር የዳንዚግ ነፃ ከተማን አቋም መርምሯል ። ምንም እንኳን የዳንዚግ ነፃ ከተማ በስምምነቱ ባትካፈልም በሌሎች ነፃ ከተማዋን እና በሷ እና በፖላንድ የሚኖረውን ሕጋዊ ግንኙነት ባቋ ቋሙት ሰነዶች ስምምነቱን እንደተቀበለችው ተቆጥ ራለች ። ፍርድ ቤቱ በሐሳቡ ማጠቃለያ ‘‘ነፃዋ ከተማ ፡ ዋናዎቹ ቃል ኪዳን የገቡ ኃያላን አገሮች በቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ ፭፻፬ መሠረት በመ ደራደር የደረሱበትን ስምምነት መቀበሏ እርግጠኛ በመሆኑ አንቀጹን መቀበሏ አያጠራጥርም’’13 በማለት ወስኗል ።

በሦስተኛ አገሮች ላይ ግዴታዎችን የሚያስከትሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች (ፓክታኢን ደትሪመንቱም ተርቲ)

በአጠቃላይ አነጋገር ያለ አንድ ሦስተኛ አገር ፈቃድ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መብትም ሆነ ግዴታ ሊያስ ከትሉ አይችሉም የሚለውን ሕግ በማስፋፋት፡ የቨየና ዓለም አቀፍ ስምምነት (ኮንቨንሽን) በሦስተኛ አገሮች ላይ ግዴታን ስለሚያስከትሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሚከተለውን መሠረተ ሐሳብ አስፍሯል ፡- ‘‘አንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት በሦስተኛ አገር ላይ ግዴታን የሚያስከትለው ስምምነቱን የመሠረቱት አገሮች ስም ምነቱ በሦስተኛ አገር ግዴታን እንዲያስከትል ሐሳብ ሲኖራቸው እና ሦስተኛው አገርም ግዴታውን በማያ ሻማ ሁኔታ በጽሑፍ ሲቀበለው ነው ።’’14

ይህ ሕግ በስምምነቱ ተካፋይ ያልሆነ ሦስተኛ አገር በስምምነቱ ተገዳጅ ከመሆኑ በፊት መሟላት ያለባ ቸውን የሚከተሉትን ሁለት ሁኔታዎች ይደነግጋል ፡-

፩/ ተስማሚዎቹ አገሮች አግባብ ባለው የስምምነቱ ክፍል በስምምነቱ ተካፋይ ባልሆነው አገር ግዴታ እንዲ መሠረት ማድረግ ፡ እና

፪/ በስምምነቱ ተካፋይ ያልሆነው ሦስተኛው አገር ግዴታውን ለማክበር በማያሻማ ሁኔታ መስማማት ።

ይህም ዓለም አቀፍ ስምምነቱን በመጀመሪያ በተፈ ራረሙት አገሮች እና በሦስተኛው አገር ተጨማሪ ስም ምነት መኖር እንዳለበት ያሳያል ። በዚህ አንፃር ሲታይ የሦስተኛው አገር ግዴታ ሕጋዊ መሠረቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቱ ሳይሆን ተጨማሪው ስምምነት ይመስላል ። የሆነ ሆኖ ሁኔታው የሚያሳየው ዓለም አቀፍ ስምምነቱ ተካፋይ ባልሆነበት አገር መፈጸሙን ነው ።

የሕጉን አሠራር በይበልጥ ለመረዳት ቋሚው ፍርድ ቤት በፍሪዞንስ ጉዳይ የቨርሳይ ስምምነት አንቀጽ ፭፻፸፭ትን በማስመልከት የወሰደውን አቋም መመርመር ይጠቅማል ። ስዊትዘርላንድ በቨርሳይ ስምምነት አል ተካፈለችም ። ነገር ግን ስምምነቱ ከመፈረሙ በፊት በስምምነቱ አንቀጽ ፭፻፸፭ ትስማማ እንደሆነ በፈረ ንሳይ መንግሥት ተጠይቃ ነበር ። የስዊትዘርላንድ ፌዴራል ምክር ቤትም አንዳንድ ሁኔታዎች ከተሟሉ አንቀጽ ፭፻፸፭ትን ስዊትዘርላንድ እንደምትስማማበት ገልጾ ነበር ። ስዊትዘርላንድ በአንቀጹ ይዘት ካልተስማ ማችባቸው ምክንያቶች አንዱ የድሮዎቹ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በጊዜው ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ አብ ረው አይሄዱም15 የሚል ይገኝበታል ። ፈረንሳይ የዱ ሮዎቹ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በአንቀጽ ፭፻፸፭ ተሸ ረዋል በማለት ያቀረበችውን ክርክር ፍርድ ቤቱ አል

12 የቨየና ዓለም አቀፍ ስምምነት (ኮንቨንሽን) አንቀጽ ፪ እና ፭ (ኤች) ።

13 ‘‘ፒ ሲ አይ ጄ ፓብሊክሽንስ (ኤ ኤ አ ፲፱፻፳፫) ፡ ሲ.ፒ.ይ.አ ቢ ፡ ቁ 44 ገጽ 30 ።

14 አንቀጽ ፴፭ ።

15 ማለትም የፍሪ ዞንስ ከጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አብሮ ያለመሄድና መሻርን በማረጋገጥ ።

ተቀበለውም ። ያልተቀበለበትም ምክንያት ስዊትዘር ላንድ አንቀጽ ፱፻፴፭ትን ሙሉ በሙሉ አልተቀበለች ውም በማለት ነበር ። ፍርድ ቤቱ "ስዊትዘርላንድ በቨ ርሳይ ስምምነት ያልተካፈለች ስለሆነ በተቀበለችው መጠን ካልሆነ በቀር አንቀጽ ፱፻፴፭ በስዊትዘርላንድ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም ፤ ስዊትዘርላንድ አንቀጽ ፱፻፴፭ትን እስከ ምን ያህል እንደተስማማችበት የሚ ወስነው በሜይ ፭ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ/ም ለፈረንሳይ የላ ከችው ማስታወሻ ነው ። ምክንያቱም የስዊስ መንግ ሥት አንቀጽ ፱፻፴፭ትን "ተቀብሎታል" ማለት የሚ ቻለው በዚህ ማስታወሻ በተገለጹት ገደቦች መሠረት ነው"[16] በማለት በፍርድ ሐተታው ገልጾታል ።

አንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት በሦስተኛ አገር ላይ ኃላፊነትን ወይም ተስማሚ ያልሆኑ ግዴታዎችን መመሥረት ይችላል ። ለምሳሌ ተስማሚዎቹ አገሮች በራሳቸው ላይ እንደዚህ ዓይነቶቹን ግዴታዎች ከመ ሠረቱ በኋላ ሦስተኛ ብሔሮች በተመሳሳይ ሁኔታ በግ ዴታዎቹ እንዲስማሙባቸው እንደሚጥሩ ቃል የሚ ገቡበት ጊዜ ሊኖር ይችላል ። የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር አንቀጽ ፪ የሚደነግገውም እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ ነው ። የአንቀጹ ይዘት የሚከተለው ነው ፦-"ዓለም አቀፍ ሰላምንና ፀጥታን ለመጠበቅ አስፈላጊ በሆነው መጠን የተባበሩት መንግሥታት አባል ያልሆኑ አገሮች እነዚህን መሠረታዊ ዓላማዎች[17] በመከተል እንደሚ ተባበሩ ጽሕፈት ቤቱ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት ።"

የአንታርክቲክ ዓለም አቀፍ ስምምነትም (በዲሰ ምበር ፩ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ/ም በዋሺንግቶን ከተማ የተፈረመ) ተመሳሳይ ድንጋጌ ያለው አንቀጽ ይገኝ በታል ። በዚህ ስምምነት መሠረት ተዋዋዮቹ ወገኖች "በስምምነቱ የተገለጹትን መሠረታዊ ዓላማዎች የሚ ፃረሩ ድርጊት ማንም ሰው እንዳይፈጽም አስፈላጊውን ጥረት ለማድረግ" ተስማምተዋል ። ይህ አንቀጽ በተ ጨማሪ ተስማሚዎቹ ወገኖች የሚያደርጉት "ተገቢው ጥረት" "ከተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ጋር" የማ ይቃረን መሆን እንዳለበት መደንገጉ ሳይገለጽ መታለፍ የለበትም ። ይህን ገደብ የአንታርክቲክ ዓለም አቀፍ ስምምነትና የተባበሩት መንግሥታት አባል ያልሆነ አገር እንዴት ይመለከተው ይሆን ? የሚል ጥያቄ ያስ ነሳል ።

ሦስተኛ አገር በቀጥታ የግባበት ግዴታ ባይኖርም ተስ ማሚዎቹ አገሮች የሚፈጽሙት ድርጊት ሕገ ወጥ እስካ ልሆነ ድረስ ፣ ሦስተኛው አገር የሚፈጽማቸው ድርጊ ቶች የስምምነቶቹ ተፃራሪ አለመሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታቸውን ለመወጣት የሚከለክላቸው ነገር አይ ኖርም ። ሆኖም እንደዚህ ዓይነቱ ዓለም አቀፍ ስም ምነት በሦስተኛው አገር ላይ ግዴታ እንደማይመሰ ርት መታወቅ አለበት ።

ሌላው መታየት ያለበት ሁኔታ በፀብ አጫሪ አገር ላይ ግዴታን የሚመሠርት ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው ። ለዚህ ሁኔታ ጀርመንን በሚመለከት አንፃር የፓትስዳም ዓለም አቀፍ ስምምነት መጥቀሱ ጠቃሚ ይሆናል ። በኮሚሽኑ ውይይት ስምምነቱ በፀብ አጫሪ አገር ላይ ተፈጻሚ የመሆኑ ጉዳይ አጠያያቂ ሆኖ ነበር ። ኮሚሽኑ የፀብ አጫሪ አገር ጉዳይ የስምምነቱን መሠረተ ሐሳብ አይመለከተውም የሚል አቋም ወስዷል ። በዚህ ጊዜ ኮሚሽኑ በዓለም አቀፍ ስምምነቱ ረቂቅ አንቀጽ ፶፱ መሠረት የአንድ አገር ፈቃደኛነት በኃይል ወይም በማስፈራራት ሲገኝ ውጤት የማይኖረው በማስገደድ የተገኘው ፈቃድ "የተባበሩት መንግሥታት ቻርተ ርን መሠረተ ሐሳብ የሚፃረር ድርጊት ለማስፈጸም ሲሆን ብቻ ነው"[18] በሚል ሐሳብ ተስማምቷል ። ስለዚህ በፀብ አጫሪ አገር ላይ በግድ ተፈጻሚ የሚሆን የዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ ከተባ በሩት መንግሥታት ቻርተር መሠረተ ሐሳቦች ጋር የማይፃረር ከሆነ ሕጋዊ ስለሚሆን የኮሚ ሽኑን ዓለም አቀፍ ስምምነት ረቂቅ አንቀጽ ፶፱ኘን አይፃረርም ። ኮሚሽኑ የአንዳንድ መንግሥታትን ማሳ ሰቢያ በመከተል ፀብ አጫሪ አገርን በሚመለከት ረገድ በቻርተሩ መሠረት በሚወሰዱት እርምጃዎች አንዳንድ ግዴታዎች በፀብ አጫሪ አገር ላይ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ቻርተሩ ስለሚደነግግ እነዚህን ግዴታዎች በሚመለ ከት አንፃር የሦስተኛው አገር ፈቃድ እንደማያስፈልግ የሚደነግግ አጠቃላይ በሆነ ይዘት የተዘጋጀ ንድፈ ሐሳብ በረቂቁ አንቀጽ ፷ ሆኖ እንዲጨመር ወሰነ ።[19]

ሦስተኛ አገርን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ግዴታዎች የመሰረዝን ወይም የማሻሻልን ሁኔታ በቭየና ስምምነት (ኮንቨንሽን) እንደሚከተለው ተደንግጓል ፦-

"የተስማሙት በሌላ አኳኋን መሆኑ ካልተረጋ ገጠ በቀር ፣ ግዴታው ሊሰረዝ ወይም ሊሻሻል የሚ ችለው በተስማሚዎቹ አገሮችና በሦስተኛው አገር ፈቃድ ብቻ ነው ።"[20]

ግዴታውን ለመሰረዝ የፈለገው ሦስተኛው አገር እስከ ሆነ ድረስ ይህ ሕግ በትክክለኛ አቋም የተመሠ ረተ ይመስላል ። ነገር ግን ግዴታውን ለመሠረዝ የፈ ለጉት ተስማሚዎቹ ወገኖች ከሆኑ የሦስተኛውን አገር ፈቃድ የማግኘቱ ጉዳይ ቀላል አይሆንም ። ተዋዋዮቹ ወገኖች ግዴታውን የማስፈጸም መብታቸውን ለመ ተው በሚወስኑበት ጊዜ የሦስተኛው አገር ፈቃድ መጠ የቅ አለበት ማለቱ ትክክለኛ ላይሆን ይችላል ። ሆኖም እንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ችግር የመኖሩ ዕድል በጣም የመነመነ ነው ። የዓለም አቀፍ ሕግ ኮሚሽን ይህን አቋም የወሰደው በዓለም አቀፍ ግንኙነት እንደዚህ ዓይነቶቹ ቀላል ሁኔታዎች በጣም

---

16 ፒ ሲ አይ ጄ ፓብሊኪሽንስ (አ ኤ አ ፲፱፻፳፭) ፣ ሲርይስ ኤ ፣ ቁ22 ገጽ 17-18 እና (አ ኤ አ ፲፱፻፴፪ ዓ/ም) ፣ ሲርይስ ኤ/ቢ ፣ ቁ46 ፣ ገጽ 141 ።

17 በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር በአንቀጽ ፪ እንደተደነገገው ።

18 የቭየና ዓለም አቀፍ ስምምነት (ኮንቨንሽን) አንቀጽ ፶፱ " - - በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር የተደነገጉትን የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረተ ሐሳቦች መጣስ")

19 የቭየና ዓለም አቀፍ ስምምነት (ኮንቨንሽን) አንቀጽ ፷፭ ፣ "ፀብ አጫሪ አገር በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር መሠረት ስለ ፀብ አጫሪነቷ በዓለም አቀፍ ስምምነት የሚወሰኑባት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ይሆናሉ ።"

20 አንቀጽ ፶፮(፩) ።

ጥቂቶች ናቸው ፤ አብዛኛውን ጊዜ የሦስተኛ አገር ግዴታ የበለጠ ጥልቀትና ክብደት ያዘለ ግንኙነትን የሚመለከት ስለሚሆን ማንኛውም የግዴታ ለውጥ በጋራ ስምምነት መደረግ አለበት ከሚል እምነት የተ ነሳ መሆን አለበት ።

ለሦስተኛ አገሮች መብቶችን የሚያስከትሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች (ፓክታ ኢን ፋቦረም ተርቲ) ።

ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ ግዴታዎችን በሚመለከት ረገድ የሦስተኛ አገር ስምምነት ምንጊዜም ቢሆን አስ ፈላጊ ለመሆኑ በኮሚሽኑ ሙሉ በሙሉ ስምምነት ቢደ ረስበትም ፣ አንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት በስምምነቱ ተካፋይ ላልሆነ ሦስተኛ አገር መብት ያስገኛል ወይስ አያስገኝም ? በሚለው ጥያቄ ላይ የሐሳብ ልዩነት ተፈ ጥሮ ነበር ። ከኮሚሽኑ አባሎች ከፊሎቹ መብትን በሚ መለከት ረገድ ተስማሚዎቹ አገሮች እስከፈቀዱ ድረስ ዓለም አቀፍ ስምምነቱ ተስማሚ ባልሆነው ሦስተኛ አገር ላይ መብት ለመፍጠር ይችላል ፤ ነገር ግን ተስማሚ ያልሆነው ሦስተኛው አገር መብቱን የመቀበል ወይም በመብቱ የመጠቀም ግዴታ አይኖርበትም የሚል አቋም ነበራቸው ።

ይህ የሐሳብ ልዩነት የመነጨው ለሦስተኛ አገሮች ጥቅም ስለሚደረጉ ውለታዎች በዓለም አቀፍ ሕግ ምሁ ራን መካከል በነበረው የሐሳብ ልዩነት ነው ። ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ለሦስተኛ አገሮች ጥቅም የሚሰጡ ገደቦች ሊይዙ እንደሚችሉ በምሁራኑ መካከል ስም ምነት ቢኖርም ፣ ሦስተኛው አገር የመብቱ ባለቤት ለመሆን ስምምነቱን ማጽደቅ አለበት ወይስ የለበትም ? በሚለው ጥያቄ የአቋሙ ልዩነት እስከ አሁን ድረስም አለ ።

ለምሳሌ ያህል ለሦስተኛ አገር ጥቅም የሚደረግ ገደብ ሦስተኛው አገር እንዲቀበል ከሚቀርብ ውል ያል ተለየ ፣ ተፈጻሚ እንዲሆንም የሦስተኛውን አገር መቀ በል የሚጠብቅ ድርድር ነው ፤ ሦስተኛው አገር ሲቀበ ለውም ሁለተኛ ስምምነት ተደርጓል ማለት ነው ። ከዚህ ስምምነት በኋላም ሦስተኛው አገር ተዋዋይ ወገን እንጂ ሦስተኛ አገር ነው ለማለት አይቻልም የሚል አቋም ነበር ። ይህም አቋም ነጉለስኮ በሚባሉ ዳኛ በፍ ሬዞንስ ጉዳይ እንደሚከተለው ተገልጾአል ፡-

“የዓለም አቀፍ ስምምነት (ኮንቨንሽን) ለሦስተኛ አገር መብት የያዘ ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን በአንድ አገር ሕግ የአንድ ሦስተኛ ወገን መብት የሚመነጨው ከስምምነቱ አንቀጾች ሲሆን ፣ በዓለም አቀፍ ሕግ መሠ ረት ግን ተዋዋዮቹ አገሮች መብት ከተሰጠው ሦስተኛ አገር ጋር የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ስምምነት ክፍል አካል የሚሆን ተጨማሪ ስምምነት ለማድረግ በጋራ ግዴታ ይገባሉ ።”[21]

ነገር ግን ዶ አረካርጋ እንዳሉት ፤

“ይህ የውል ማቅረብ ጽንሰ ሐሳብ ከሃምሳ ዓመት በፊት የፍትሐ ብሔር ምሁራን ስቲፑላስዮን ኢን ፋቮረም ተርቲ የሚባለውን ፅንሰ ሐሳብ ባሁለት ተከታታይ ውሎች ለመግለጽ የሰነዘሩት ሐሳብ ነው ። ይህ ጽንሰ ሐሳብ በዓለም አቀፍ ሕግ ተቀባይ ነት ሊኖረው አይገባም ፤ ምክንያቱም ጥቅምን መቀ በል ሁለተኛ ውል መዋዋል ነው ማለት አይቻ ልም ።”[22]

ይህ ውልን መቀበል ሊባል አይቻልም ። ሦስተኛው አገር መፈጸም ያለበት ድርጊት ለሁለተኛ ስምምነት የሚያስፈልግ ፈቃድ መስጠት ሳይሆን በዓለም አቀፍ ስምምነት ያለውን መብት መቀበል ብቻ ነው ። ሦስተኛው አገር በመብቱ የመጠቀም ወይም መብቱን ላለመቀበል ያለው መብት የተጠበቀ ነው ። ስለዚህ ስምምነቱን መቀበል በዚህ አንጻር ሲታይ ፣ ተጠ ቃሚው መብቱን እንዳልናቀው የሚያስቆጥር ድር ጊት ብቻ ይሆናል ።[23]

የቭየና ስምምነት (ኮንቨንሽን) “አንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት ሦስተኛው አገር ካልፈቀደ በስተቀር መብት አያስገኝለትም” የሚለውን አንቀጽ ፴፬ትን በማስፋፋት ግዴታዎችን በሚመለከት ረገድ ካለው አቋም ለየት ያለ አቋም ይዞአል ። በዚህም መሠረት የስምምነቱ አንቀጽ ፴፮ የመጀመሪያው አዲስ መስ መር ተቃራኒ ሐሳብ ካልተገለጸ በስተቀር የሦስተ ኛው አገር ፈቃድ እንደተሰጠ ይቆጠራል በማለት ይደ ነግጋል ። ኮሚሽኑ የአንቀጹ ይዘት ይህ እንዲሆን የመረጠበት ምክንያት መብቱ የተሰጠው በአጠቃ ላይ አገሮችን ለመጥቀም ወይም የተወሰኑ አገሮችን ለመጥቀም በሚሆንበት ጊዜ ሕጉን በቀላሉ ሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል በማሰብ ነው ።

ኮሚሽኑ እንደተገነዘበው ሁሉ ተጠቃሚዎቹ አገ ሮች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ ። በቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት ስዊትዘርላንድን[24] እና ዴንማርክን[25] ለመ ጥቀም እንደተደረገው ሁሉ አንዳንድ ጊዜም በገደብ መጠቀም የሚችሉ አገሮች የተወሰኑ ሊሆኑ ይችላሉ ። ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት[26] በኋላ በተደረጉት የሰላም ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደሚታየው ደግሞ አንዳ ንድ ጊዜ የገደቡ ተጠቃሚዎች የተወሰኑ አገሮች ሊሆኑ

---

21 ፒ. ሲ. አይ. ጄ. ፓብሊከሽንስ (እ ኤ አ ፲፱፻፴፱) ፣ ሲሪይስ ኤ ቁ 22 ፣ ገጽ 36-37

22 ኢ. ጀ. ዶ. አሬካጋ ፣ “ትርቲ ስቲፑሌሽንስ ኢን ፊቨር አፍ ተርድ ስቴትስ” ፣ አሜሪካን ጆርናል አፍ ኢንተርናሽናል ሎው ፣ (እ ኤ አ ፲፱፻፶፮) ፣ ቦል ዩም 50 ፣ ገጽ 352 ።

23 “በዓለም አቀፍ ስምምነት የሚገኙ በስምምነቱ ላልተካፈለ ሦስተኛ አገር ጥቅም የሚሰጡ አንቀጾች በሦስተኛው አገር ተቀባይነት ማግኘት አለ ማግኘታቸው የሚወሰነው በሦስተኛው አገር ነው” ከሚለው እ ኤ አ በፌብርዋሪ ፳ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ከተደረገው የሐሳናው ስለ ዓለም አቀፍ ስም ምነቶች ሕግ ስምምነት (ኮንቨንሽን) ከአንቀጽ ፴ ጋር ማነጻጸር ጠቃሚ ይሆናል ።

24 የቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ ፫፻፶፭ እና ፴፮ ።

25 የቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ ፭፻፶ ።

26 ከፊንላንድ (አንቀጽ ፴፱) ኢታሊ (አንቀጽ ፵፮) ፣ ቡልጋሪያ (አንቀጽ ፴፰) ፣ ሐንጋሪ (አንቀጽ ፴፪) እና ሩማንያ (አንቀጽ ፴) የተደረገትን የሰላም ስምምነቶች በአሜሪካን ጆርናል አፍ ኢንተርናሽናል ሎው ፤ (እ ኤ አ ፲፱፻፵፰) ቦልዩም 24 ፣ ሳፕሊመንት (ማሟያ) ይመለከቷል ።

ይችላሉ ። እነዚህ የሰላም ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በጦርነቱ የተሸነፉ አገሮች በጦርነቱ ያገኙት ጥቅም በስምምነቶቹ ላልነበሩትና ጥቅሙ ለሚገባቸው አገሮች መልቀቅ እንደነበረባቸው ደንግገዋል ። የተባበሩት መንግሥታት ቻርተርም ፣ ለምሳሌ ያህል ፣ አባል ያልሆኑ አገሮች የሚመለከታቸው እስከሆነ ድረስ በሴኩሪቲ ካውንሲል በሚደረገው በማንኛውም ያለመግባባት ውይይት እንዲካፈሉ (አንቀጽ ፴፪) ወይም አለመግባባቱን ያስከተሉት ነገሮች ለሴኩሪቲ ካውንሲል ወይም ለጠቅላላው ስብሰባ እንዲያቀርቡ (አንቀጽ ፴፭) መብት ይሰጣቸዋል ። በመጨረሻም ይህ ሦስተኛ አገሮችን ለመጥቀም የሚደረገው ገደብ ፣ በዓለም አቀፍ ወንዞች ባሕረ ሰላጤዎችና ክልሎች ትራንስፖርትን ስለማካሄድ ነፃነት[27] እንደተደነገገው ሁሉ መብቱን በአጠቃላይ ለብሔሮች መስጠትን ይመለከታል ።

እነዚህን ፍሬ ነገሮች በሚመለከት ረገድ የቭየና ስምምነት (ኮንቬንሽን) ለሦስተኛ አገሮች የሚሰጥ መብት "ለሦስተኛው አገር ለተወሰኑ ሦስተኛ አገሮች ወይም ለአገሮች በሙሉ"[28] እንዴት ሊመነጭ እንደሚችል ይደነግጋል ።

መብቱ የሚሰጣቸው አገሮች እንደሚፈቅዱ በመገመት ስምምነቱ ወሳኝ አድርጎ የሚቆጥረው የተስማሚዎቹ አገሮች የስምምነቱ አንቀጽ መብቱን እንዲያስገኝ በማቀድ መስማማት ነው ። "ከአንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት ለሦስተኛ አገር መብት የሚመነጨው ተስማሚዎቹ አገሮች ሦስተኛው አገር መብት እንዲኖረው በማቀድ የተስማሙበት አንቀጽ ሲኖር ነው።"[29]

እንግዲህ ከስምምነቱ የሚመነጭ ከጥቅም ብቻ የተለየ ሕጋዊ መብት ለአንድ ሦስተኛ አገር ሊኖር የሚችለው ተስማሚዎቹ አገሮች ከላይ የተገለጸው ሐሳብ ሲኖራቸው ብቻ ነው ።

ሐሳቡን በሚመለከት ረገድ መደበኛው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እ ኤ አ በ፲፱፻፴፱ ዓ/ም በፍሪ ዞንስ ጉዳይ በሰጠው ፍርድም እንደሚከተለው ወስኗል ፦

"ሌሎች አገሮች በፈጸሙት ስምምነት የተገኘ መብት አለ ወይስ የለም ? የሚለው ጥያቄ መታየትና መወሰን ያለበት በያንዳንዱ ጉዳይ ነው ፤ ለሦስተኛ አገር ጥቅም ያዘለ ስምምነት የተስማሙት አገሮች መብቱ ተሰጥቶኛል ለሚለው አገር መብቱ እንዲያገለግል ያቀዱ ለመሆናቸውና አገሩም ይህን መብት ለመቀበሉ መረጋገጥ አለበት ።"[30]

የሐርባርድ ሪሰርች (ምርምር) አንቀጽ ፲፮ (ለ) ሦስተኛ አገር ጥቅም አለኝ ለማለት የሚችለው ጥቅሙ ይሰጠኛል የሚለው አንቀጽ የተደረገው "በግልጽ በስምምነቱ ላልተካፈለ ወይም ስምምነቱን ላላጸደቀ ሦስተኛ አገር ጥቅም እንዲሰጥ ታቅዶ ሲሆን ነው"[31] በማለት ይደነግጋል ።

በቭየና ስምምነት (ኮንቬንሽን) በአንቀጽ ፶፮፮ በዓለም አቀፍ ወንዝ ወይም ለመርከብ አገልግሎት በሚያገለግል ባሕረ ሰላጤ በምን ሁኔታ መጠቀም እንደሚቻል እንደተደነገገው ሁሉ ተጠቃሚው አገር በመብቱ መጠቀም የሚችለው በስምምነቱ ስለመብቱ አጠቃቀም የተደነገጉትን ገደቦች በመከተል መሆን አለበት ።[32]

እንደዚህ ዓይነት ገደቦች በስምምነቱ መኖር አለባቸው ወይም በስምምነቱ መሠረት መነደፍ አለባቸው ማለት ግን የተስማሚዎቹ አገሮች ለሦስተኛ አገሮች የሰጡት መብት የማሻሻል ሥልጣናቸውን ይወስንባቸዋል ማለት ሊሆን አይችልም ።

የቭየናው ስምምነት (ኮንቬንሽን) እንደዚህ ዓይነቱ የማሻሻል ሥልጣን የተሰጡት መብቶችን እስከመሰረዝ ሊደርስ እንደሚችል ይደነግጋል ።

ተጠቃሚው አገር ሳይስማማበት ተስማሚዎቹ አገሮች በተከታይ ስምምነት መብት የሚሰጠውን የስምምነቱን አንቀጽ ለማሻሻል ወይም ለመሠረዝ ይችላሉ ወይስ አይችሉም ? ለሚለው ጥያቄ በዓለም አቀፍ ሕግ ምሁራን ሦስት የተለያዩ አቋሞች ነበሩ ።

አንደኛው ጠበብ ያለው አቋም ፣ ሦስተኛው አገር በስምምነቱ መጠቀም የሚችለው መብት የሚሰጠው የስምምነቱ አንቀጽ በሥራ ላይ እስካለ ድረስ ብቻ ሆኖ ፣ ሦስተኛው አገር አንቀጹ ተፈጻሚ እንዲሆን የመጠየቅ ሕጋዊ መብት ስለሌለው ተስማሚዎቹ አገሮች በማንኛውም ጊዜ ለሦስተኛው አገር መብት የሚሰጠውን አንቀጽ የማሻሻል ወይም የመሠረዝ መብት አላቸው የሚል ነው ።[33]

ሁለተኛው አቋም ዓለም አቀፍ ስምምነቱ በተስማሚዎቹ አገሮች መካከል ተፈጻሚነቱ እስካልተቋረጠ ድረስ የሦስተኛው አገር የተጠቃሚነት መብት እንደ ተጠበቀ ይቆያል የሚል ነው ። በዚህ አቋም ፣ ሦስተኛው አገር ሳይስማማበት ተስማሚዎቹ አገሮች ለሦስተኛው አገር ስጥተውት የነበረውን መብት በሌላ ስምምነት ማስቀረት እንደሚችሉ ግልጽ ነው ።[34]

---

27 ለምሳሌ ፣ ምንም እንኳን ተስማሚዎቹ ብሔሮች ትልቋ ብሪታንያ ፣ የተባበሩት የአሜሪካ መንግሥታት እና ፓናማ ብቻ የነበሩ ቢሆንም ፣ እ ኤ አ በ፲፱፻፳፩ ዓ/ም በታላቋ ብሪታንያ እና በተባበሩት የአሜሪካ መንግሥታት የተደረገው የቭይ ፓውንስፎተ ዓለም አቀፍ ስምምነት እና እ ኤ አ በ፲፱፻፲፫ ዓ/ም በተባበሩት የአሜሪካ መንግሥታት እና በፓናማ መካከል የተደረገው የቭይ ቭሪላ ዓለም አቀፍ ስምምነት የፓናማ ካናል ለማንኛውም አገር የንግድ መርከብና የጦርነት መርከብ ክፍት እንደሚሆን ይደነግጋሉ ።

28 አንቀጽ ፴፮ ፤ ፓራግራፍ ፩ ።

29 ከላይ የተጠቀሰው

30 ፒ. ሲ. አይ. ጀ. ፓብሊከሽንስ (እ ኤ አ ፲፱፻፴፪ ፣ ሲርይስ ኤ/ቢ ፣ ቁ 46 ፣ ገጽ 147-8

31 ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 10 የተጠቀሰውን ይመለከቷል ።

32 "የተባበሩት መንግሥታት አባል ያልሆነ አገር" አለመግባባቱን በሚመለከት ረገድ "በቻርተሩ እንደተደነገገው አለመግባባትን በሰላማዊ መንገድ የማስወገድ ግዴታ አስቀድሞ ከተቀበለ'፤ "የሚመለከተውን ማንኛውንም አለመግባባት ለሴኩሪቲ ካውንሲል ወይም ለጠቅላላው ስብሰባ ማቅረብ ይችላል" በማለት የሚደነግገውን የተባበሩት መንግሥታት አንቀጽ ፴፩(፪) ትን በተጨማሪ ይመለከቷል ።

33 ኤሌ ኤ ፓዶስታ ኮስታ ፣ ማንዋል ዶ ዶረክ ኢንተርናስዮናል ፑብሊክ ፣ (ሁለተኛ እትም ፣ ቦናስ አይረስ እ ኤ አ ፲፱፻፵፯) ፣ ፓራግራፍ 137 ፣ ኤል ኤም ሞሬኖ ኩታና ፣ ዶረክ ኢንተርናስዮናል ፑብሊክ ፣ (ቦናስ አይረስ እ ኤ አ ፲፱፻፶) ፣ ጂ ሳልቨዩን ፣ "ለ ረግል ዝነራል ደላ ፕይ ፣" ረስወይ ደ ኩር (እ ኤ አ ፲፱፻፴፫) ቦልዩም 46 ፣ ገጽ 29-30

34 ለምሳሌ የሐርባርድ ሪሰርች (ምርምር) አንቀጽ ፲፮(ለ) እንደሚከተለው ይደነግጋል ፤ "አንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት በስምምነቱ ተካፋይ ላልሆነ አገር ጥቅም የሚሰጥ ከሆነ ፤ አገሩ ስምምነቱ ፀንቶ በሚቆይበት በማንኛውም ጊዜ ጥቅሙን የመጠየቅና የማስፈጸም መብት አለው ።

ሦስተኛው አቋም ፥ ተስማሚዎች አገሮች ከፈቀዱ በሚያደርጉት ስምምነት ለሦስተኛ አገር መብት ለመ ስጠት ይችላሉ ፤ መብቱ ከተሰጠ በኋላ ማስቀረት የሚ ቻለው ግን ባለመብቱ ሦስተኛው አገር ሲስማማበት ብቻ ነው[35] የሚል ነው ።

በዚህ ከላይ በተገለጸው ሕግ መሠረት በሌሎች ተስ ማሚ አገሮች በተደረገ ስምምነት የተገኘ መብት አለ ወይስ የለም የሚለው ጥያቄ እያንዳንዱን ስምምነት በመመርመር የሚመለስ ጥያቄ ሆኖ ፥ ሦስተኛው አገር መብት አለኝ ማለት የሚችለው ተስማሚዎቹ አገሮች በስምምነቱ ግዴታ ለመቀበል ሲፈቅዱ ብቻ ነው ። ቋሚው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤትም በፍሬ ዘንስ ጉዳይ በ፲፱፻፴፪ ዓ/ም በሰጠው ፍርድ[36] የወሰደው አቋም ይኸው ነበር ።

አንዳንድ ጊዜ ይህን ጥያቄ ዓለም አቀፍ ስምምነቱ ራሱም ይወስነዋል ። ለምሳሌ በቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት በአንቀጽ ፫፻፹፮ እንደተደነገገው ፥ በዚህ ስም ምነት በአንቀጽ ፫፻፹[37] የተሰጠው መብት ተፈጻሚ ይሁንልኝ በማለት የፍርድ መፍትሔ መጠየቅ በስም ምነቱ ተካፋይ ባይሆንም የማንኛውም አገር መብት ነው ።

እርግጠኛ የሆነ የማይሻር መብት የመስጠት ፈቃድ በግልጽ የሚታይ ወይም ከነገሩ አካባቢ ሁኔታ የሚወ ሰን ሊሆን ይችላል ። ለምሳሌ ያህል ፥ በአንድ የሰላም ዓለም አቀፍ ስምምነት አንድ መንግሥት ከግዛቱ ውስጥ በከፊል ለሌላ መንግሥት አሳልፎ ለመስጠት ግዴታ ቢገባም ፥ የሦስተኛው አገር መብት ግልጽ የሆነና የማ ይሻር መብት ካልሆነ ይህ ስምምነት ግቡን ሊመታ አይችልም ።[38]

በሌላ በኩል የማይሻር መብት የመስጠት ፈቃድ ያል ነበረ ለመሆኑ ከዓለም አቀፍ ስምምነት ታሪክ እና ከነገሩ ሁኔታ ማየት ይቻላል ። ለምሳሌ ፥ የአሜሪካ ሰኔት በሔይፓውንሰፎቱ ዓለም አቀፍ ስምምነት የመ ጀመሪያ ረቂቅ ውስጥ በፓናማ ካናል በመርከብ መጠ ቀምን በሚመለከት ረገድ ሦስተኛ አገሮች ስምምነቱን ለማጽደቅና ለመቀበል ስለሚችሉበት ሁኔታ ተደንግ ገው የነበሩትን አንቀጾች አስቀርቷል ። እነዚህ የስም ምነቱ አንቀጾች የተሰረዙት ለሦስተኛ አገሮች መብት የሚሰጡ ግዴታዎችን ለማስቀረት ታቅዶ ስለሆነ ፥ ይህ ሁኔታ ሊሻሻል የሚችለው ተስማሚዎቹ አገሮች በሚያደርጉት ተከታታይ ስምምነት ይመስላል ።

በ፲፱፻፷፬ ረቂቅ ኮሚሽኑ ከአንድ ዓለም አቀፍ ስም ምነት ለሦስተኛ አገሮች ስለሚመነጭ መብት ሆነ ግዴታ የወሰደው አቋም መብቱን ሆነ ግዴታውን የሚ ሰጠው አንቀጽ "የሚሰረዝ መሆኑ ከስምምነቱ ካልተ ረጋገጠ በቀር ፥ ሊሰረዝ ወይም ሊሻሻል የሚችለው በሦስተኛው አገር ስምምነት ብቻ ነው"[39] የሚል ነው ።

ነገር ግን ስለዚህ ጉዳይ በኋላ በተደረገው ውይይት ከላይ የተጠቀሰው የ፲፱፻፷፬ ረቂቅ ተስማሚዎቹ አገ ሮች ለሦስተኛ አገር ጥቅም ያደረጉትን ስምምነት የመ ሰረዝ ወይም የማሻሻል መብታቸውን አለአግባብ ያጠ ብባቸዋል ፤ ለሦስተኛው አገር የተሰጠው መብትም አላግባብ ነው[40] የሚል አቋም በአንዳንድ መንግሥታት ለኮሚሽኑ ተገለጸ ። ከዚህም ሌላ ተስማሚ አገሮች ለሦ ስተኛ አገሮች መብት ከመስጠት እንዲቆጠቡ በመገ ፋፋት የአገሮችን የአሠራር ነፃነት ያደናቅፋል ። እነ ዚህን ሁኔታዎች በመገንዘብ ኮሚሽኑ በ፲፱፻፷፮ ረቂቁ የሦስተኛ አገር መብት ሊሰረዝ የማይቻለው መብቱ የማይሻር መብት መሆኑ ወይም ያለ ሦስተኛው አገር ፈቃድ የማይሻሻል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው[41] በሚል ሕግ የ፲፱፻፷፮ ረቂቁን አሻሽሎታል ።

ስለዚህ ለሦስተኛ አገር የተሰጠው መብት የማይሻር መሆን አለመሆኑ መወሰን ያለበት የዓለም አቀፍ ስም ምነቱን ይዘት ወይም ተስማሚዎቹ አገሮችና ሦስተ ኛው አገር ያደረጉትን ስምምነት ወይም መግባባት መሠ ረት በማድረግ እያንዳንዱን ጉዳይ በመመርመር ነው ።

ነገር ግን ፥ የሦስተኛ አገር መብት ሊሰረዝ ወይም ሊሻሻል የሚችለው መብቱ በተስማሚዎቹ አገሮች ሊሠረዝ ወይም ሊሻሻል እንደሚቻል ታቅዶ የተሰጠ መብት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው የሚለው ሕግ ግዴታ ለማስቀረት የሦስተኛው አገር ስምምነት አስፈላጊ ነው ከሚለው ጋር ሲነፃፀር ግራ የሚያጋባ ሕግ ነው ።

---

35 ጀ. ኤል. ባየርሊ ፥ "ረግል ጀነራል ዱ ድርዋ ደ ላ ፕይ" ረስወይ ደ ኩር (አ ኤ አ ፲፱፻፴፯) ኤፍ ኤል ፥ አፐንሐይም ፥ ከላይ የተጠቀሰው፣ገጽ 927 ፥ ኤ. ጀ. አረካ ፥ ከላይ የተጠቀሰው ፥ ገጽ 344-45

36 ፒ ሲ አይ ጀ ፓብሊከሽንስ (አ ኤ አ ፲፱፻፴፪) ፥ ሲርይስ ኤ/ቢ ፥ ቁጥር 46፣ ገጽ 147-8

37 "የክየል ካናል እና አካባቢዎቹ ለማንኛውም ከጀርመን ጋር በሰላም ለሚገኝ አገር የንግድ ወይም የጦር መርከቦች ፍጹም በሆነ እኩልነት ክፍትና ነፃ ይሆናል ።"

38 ለምሳሌ ኡራጉዋይ ነፃ ሆና የወጣችበት በአርጀንቲናና በብራዚል መካከል እ ኤ አ በአክቶበር ፴ ቀን ፲፰፻፸፭ ዓ/ም የተደረገ የሰላም ስምምነት ።

39 የአ ኤ አ ፲፱፻፴፪ ዓ/ም ረቂቅ ፥ አንቀጽ ፴፭ ።

40 ሪፖርት . . . ሳፕሊመንት (ማሚያ) ቁ ፱/ኤ6309/ረብ 1 / ቦልዩም 2 ፣ ገጽ 60

41 እንደዚሁም የቨየናው ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ ፴፮ ።

መደምደሚያ ።

የቨየናው ስምምነት (ኮንቨንሽን) በዓለም አቀፍ ወንዞች ወይም ባሕረ ሰላጤዎች የመጠቀም መብትን ፣ ወይም አንዳንድ አካባቢዎችን ወይም ግዛቶችን ገለል ተኛ ወይም ከጦር ትጥቅ ነፃ ስለማድረግ እንደተደረጉት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተጨባጭ የዓለም አቀፍ ሕግን ለመደንገግ[42] የታቀደ ስምምነት አለመሆኑ መገንዘብ ይገባል ። ልማድ (ካስተም) አንዳንድ ጊዜ በአንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት የተደነገጉትን ሕግጋት ከተስማሚዎቹ አገሮች ውጭ ተፈጻሚ ዓለም አቀፍ ሕግ እንዲሆኑ የሚያደርገውን አስተዋጽኦ በመገንዘብ ስምምነቱ ያቀፋቸው አንቀጾች "በዓለም አቀፍ ሕግ ተቀባይነት ባገኘው የዓለም አቀፍ ልማድ መሠረት በሦስተኛ ብሔሮች ተፈጻሚ መሆን የሚገባቸውን ሕጎች ተፈጻሚ ከመሆን አያግዱም"[43] በማለት ይደነግጋል ። ምንም እንኳን ይህ አንቀጽ የሚገኘው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ሦስተኛ አገሮች በሚለው በስምምነቱ ክፍል ከሚገኙት አንቀጾች ውስጥ በመጨረሻ ቢሆንም ለጉዳዩ መሠረታዊ የሆነውን ጥያቄ ይነካል ።

ዓለም አቀፍ ግንኙነትና በአገሮች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች እየተስፋፉ በመሄድ ላይ መሆናቸውን ስንመለከት ፣ "ፓክታ ኢንፍቮረም ተርቲ" ወይም "ፓክታ ኢን ደትሪመንቱም ተርቲ" የሚባሉት የቆዩ አስተሳሰቦች አግባብ እንደሌላቸው እንገነዘባለን ። የአሁኑ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሕጋዊ ይዘት እንደ ዚህ በቀላሉ ሊታይ አይቻልም ። በአሁኑ ዘመን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አብዛኛውን ጊዜ በስምምነቶቹ ባል ተሳተፉ አገሮች ላይ መብቶችና ግዴታዎች ይመሠርታሉ ።[44] በሌላ በኩል ሲታይ ሦስተኛዎቹ አገሮች የትኛቹ ናቸው ብሎ ለመወሰን ያስቸግራል ። አንዳንድ ጊዜ በስምምነቱ አባላት ያልሆኑ አገሮች ስምምነቱን ለማዘጋጀት በሚደረገው ስብሰባ ተመልካቾች በመላክ ወይም ተስማሚ አገሮችን በማማከር[45] በስምምነቱ ድርድር ይካፈላሉ ። ምንም እንኳን በቨየናው ዓለም አቀፍ ስምምነት የተቀነባበሩት ሕጎች ጥቅማቸው በቀላሉ የማይገመት ቢሆንም ፣ በአሁኑ ጊዜ እና ለወደፊቱም በጣም አስፈላጊ የሆነውና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው በዘልማድ የሚመሠረቱት ሥነ ምግባሮች በልማዳዊ ዓለም አቀፍ ሕግ ተቀባይነት አግኝተው "ኢዩስ ኮግንስ" ማለትም የዓለም አቀፍ ጠቅላላ ሕግ አካል ስለሚሆኑበት ሁኔታ ነው ።

---

42 ለምሳሌ የኑረምበርጉ ዓለም አቀፍ ጦር ፍርድ ቤት በመሬት ስለሚደረገው ወጊያ በሔግ ዓለም አቀፍ ስምምነት (ኮንቨንሽን) የተደረጉት ስምምነቶች ተፈጻሚነት ያላቸው ከልማድ የመነጩ የዓለም አቀፍ ሕግ መሆናቸውን ገልጾአል ።

43 አንቀጽ ፬፮ ።

44 ለምሳሌ የፓትስዳሙ ዓለም አቀፍ ስምምነት ተሸናፊዋ ጀርመኒ ግዛት እንድትለቅ ግዴታ ሲጥልባት ፣ በዚሁ አኳያ ፖላንድ ግዛት እንድታገኝ መብት ሰጥቷታል ። ጀርመኒ እና ፖላንድ በስምምነቱ አልተካፈሉም ።

45 ለምሳሌ የፓትስዳም ዓለም አቀፍ ስምምነትን በሚመለከት ረገድ ፣ ፖላንድ በዚህ ሁኔታ ትገኝ ነበር ።

ቀደም ሲል በተሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት ስለሚከብዱ ወንጀሎች ክስ አቀራረብ የተለየ ሥነ ሥርዓትና ዓላማው ፤ በማናቸውም ሁኔታ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ወይ ?

በዮሴፍ ገብረ እግዚአብሔር*

የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፭፻፲፬ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት ከባድ ቅጣት ስለሚያስቀጡ ወንጀሎች የተለየ የክስ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት ይደነግጋል ። በዚህ አንቀጽ መሠረት አንድ ተከሳሽ ፈጸመ የተባለው ወንጀል ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት ከባድ ቅጣት ያስቀጣዋል ከተባለ ቅጣትን በሚያከብደው ወንጀል አይከሰስም ። መከሰስ ያለበት ቅጣቱን በማያከብድበት ወንጀል ነው ። አቃቤ ሕጉ ተከሳሹ ቀደም ሲል የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶበት የነበረ መሆኑን ማስረዳት ያለበት ተከሳሹ በተከሰሰበት ቅጣትን በማያከብደው ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ብቻ ነው ።

በዚህ አንቀጽ ላይ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ተከሳሹን ቅጣቱን በሚያከብደው ወንጀል መከሰስ ሲቻል ለምን የተለየ ሥነ ሥርዓት አስፈለገ ? የሚለው ነው ። ለዚህ ጥያቄ ግልጽ ሆኖ የሚታየው መልስ ፥ ክስ በፍርድ ቤት እንዲሰማ የሚደረግበት ምክንያት ወንጀል ተፈጽሞ እንደሆነ ለማስረዳት ነው ። ይሽውም ፥ አንድ ተከሳሽ ቀደም ሲል በፈጸመው ወንጀል ጥፋተኝነቱ በፊት የተወሰነ ስለሆነ እንደገና ማስረዳት አስፈላጊ አይሆንም ። በክስ ማመልከቻ መገለጽና በማስረጃ መረጋገጥ ያለበት አዲሱ የወንጀል ክስ ብቻ ነው ። ቀደም ሲል የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ነገር በአዲሱ የክስ ማመልከቻ ላይ መገለጽ የለበትም የተባለው ስለዚህ ነው የሚል ሊሆን ይችላል ።

ሆኖም ይህን የተለየ ሥነ ሥርዓት መቀየስ ያስፈለገው ከላይ በተገለጸው ምክንያት ብቻ ነው ለማለት አስቸጋሪ ይሆናል ። ዓቃቤ ሕጉ ተከሳሹ "... ከዚህ ቀደም በወንጀል የተቀጣበትን ለፍርድ ቤት ማስረዳት ..."[1] እንዳለበት ተደንግጓል ። ይህ ሲታይ ልዩ ሥነ ሥርዓት ያስፈለገበት ምክንያት ከላይ የተገለጸው ብቻ ቢሆን ኖሮ ቀደም ሲል የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበትን ወንጀል ዓቃቤ ሕጉ ክሱ በፍርድ ቤት በሚሰማበት ጊዜ ከጥፋተኝነት ውሳኔ በኋላ ብቻ ማስረዳት እንዳለበት መደንገጉ ባላስፈለገም ነበር ። ስለዚህ ዓቃቤ ሕጉ ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎችን ማስረዳት ያለበት ተከሳሹ በተከሰሰበት ቅጣትን በማያከብደው ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በኋላ ነው ተብሎ የተደነገገበት ሌላ ምክንያት መኖር አለበት ።

የተለየ ሥነ ሥርዓት ያስፈለገበት ምክንያት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ. ፭፻፴፭ የተደነገገውን መሠረተ ሐሳብ ተግባራዊ ለማድረግ መስሎ ይታያል ። በዚህ አንቀጽ መሠረት ፥ በሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር[2] ተከሳሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑ ካልተረጋገጠ ፥ ቀደም ሲል ውሳኔ የተሰጠባቸው ጥፋቶች ለፍርድ ቤቱ መገለጽ የለባቸውም ፤ በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት መዝገብ ውስጥም መገለጽ የለባቸውም ።

የቁ. ፭፻፴፭ ዓላማ ክሱን የሚሰማው ፍርድ ቤት በተከሳሹ ላይ አስቀድሞ የጥፋተኝነት ግምት እንዳያሳድር ለመከላከል ሆኖ ይታያል ። ፍርድ ቤቱ ክሱን ከመስማቱ በፊት ተከሳሹ ከክሱ በፊት የፈጸማቸው ወንጀሎች መኖራቸውን ካወቀ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ፈጽሟል ወይስ አልፈጸመም?[3] የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በንጹሕ ሕሊና ማስረጃውን መመርመር ሲገባው ተከሳሹ ይህንንም ወንጀል ሳይፈጽም አይቀርም

---

* ሌክቸረር ፥ ሕግ ፋኩልቲ ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

1 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ 114(2)

2 "ሕጉ በተለይ በግልጽ ካልፈቀደ በቀር" የሚለው ሐረግ የማስረጃ ሕግን ለማስመልከት የታቀደ ይመስላል ። በዚህ ቁጥር የተደነገገው ሕግ "ኮመን ሎውን" በሚከተሉ ሐገሮች የማስረጃ ሕግ ነው ። ይህን ለመገንዘብ ፒ ኤን ራማስዋሚ እና ኤስ ራጀግፓላን ፥ ውድሮፍ ኤንድ አሚር አሲስ ሎው ኦፍ ኤቪደንስ ኢን ኢንድያ (ሎው ቡክ ካምፓኒ አላሃባድ ፥ ፲፭ኛ እትም እ ኤ አ ፲፱፻፷፫) ቮልዩም 2ሣጽ 11597 እና ጂ.ዲ.ኖክስ ፥ አን ኢንትሮዳክሽን ቱ ኤቪደንስ (ሱንዶን ስዊት ኤንድ ማክስዌል ፱ኛ እትም እ ኤ አ ፲፱፻፷፯) ገጽ 136-41 ይመለከቷል ። የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓታችን የውጭ ሀገር ሕግ ምንጮች ከሞን ሎው እና ሲቪል ሎው ለመሆናቸው ፥ ስታሊን ዜድ ፊሸር ፥ ኢትዮፒያን ክሪሚናል ፕሮሲጀር ኤ ሶርስ ቡክ (ሕግ ፋኩልቲ አዲስ አበባ ዩኒአርስቲ ከአክስፎርድ ዩኒአርስቲ ጋር በመተባበር ያሳተመው ፥ እ ኤ አ ፲፱፻፷ ዓ/ም) ገጽ 4-12 (ታሪካዊ መግቢያ) ይመለከቷል ። ስለሆነም የሲቪል ሎውን ይዘት በመከተል በሥነ ሥርዓት ሕግ የማስረጃ ሕግ ተደንግጎ እናያለን ። ይህ የሲቪል ሎው አሠራር ስለመሆኑ ስለ ማስረጃ የሚደነግጉት ነገር ግን በፍትሐ ብሔር ሕግ የሚገኙት የፍትሐ ብሔር ሕጋችን ቁ 2001-2021 ይመለከቷል ።

3 የበፊት ጥፋቶች ከጥፋተኝነት ውሳኔ በፊት የማይገለጹበት ምክንያት ይህ ለመሆኑ ጆን ኤች.ዊግመር ፥ ኤ ትሪቲስ አን ዘ አንግሎ አሜሪካን ሲስተም ኦፍ ኤቪደንስ ኢን ትራያልስ አት ኮሞን ሎው (ቦስቶን ፥ ሊትል ፥ ብራውን ኤንድ ኮምፓኒ ፥ ፫ኛ እትም ፥ እ ኤ አ ፲፱፻፵፯) ቮልዩም ፯ ገጽ 412-415 እና 454-456 ይመለከቷል ።

ወደሚል ግምት እንዳያመራ ለመከላከል የታቀደ ሆኖ ይታያል ። የፖሊስ ምርመራ መዝገብ በቁ ፭፻፴፰ አለመጠቀሱም ሲታይ ይህ አንቀጽ እንዲከላከል የታቀደው ይህን ክሱን የሚሰማ ፍርድ ቤት ሊያድርበት የሚችለውን ከላይ የተገለጸውን ግምት መሆኑን ያመለክታል ። የቀዳሚ ምርመራ መዝገብ ክሱን ለመስማት ብቸኛ ሥልጣን ላለው ለከፍተኛው ፍርድ ቤት[4] በፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር በኩል መቅረብ አለበት ። የወንጀል ክሶችን በሚመለከት አንፃር ፥ የሬጅስተሩ ሥልጣን ለችሎቶች ማከፋፈል እንደመሆኑ ፥ የቀዳሚ ምርመራ መዝገብ ክሱን ለመስማት ሥልጣን ወዳለው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ችሎት[5] በሬጅስትራሩ አማካይነት መተላለፍ እንዳለበት የታወቀ ነው ። የፖሊስ ምርመራ ራፖር ግን መላክ ያለበት ለዐቃቤ ሕጉ[6] ነው ። በመሠረቱ ፥[7] የፖሊስ ምርመራ ራፖርን በሚመለከት ረገድ ክሱ በሚሰማበት ጊዜ በነገሩ አግባብ ካላቸው መካከል ዐቃቤ ሕጉ ብቸኛ ሥልጣን አለው ። ከተጠቀሰው አንቀጽ በግልጽ እንደሚታየውም ፥ ዐቃቤ ሕጉ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለማስገኘት መተማመን ያለበት ቀደም ሲል በተከሳሹ በተሰጡ የጥፋተኛ ውሳኔዎች ሳይሆን ተከሳሹ ፈጽሟል ተብሎ በተከሰሰበት ወንጀል ተመርምሮ በተገኘው ማስረጃ ብቻ ነው ። ስለዚህ ፥ ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች መኖራቸው በቀዳሚ ምርመራ መዝገብ ከተገለጸ ክሱን የሚሰማው ፍርድ ቤት ክሱን መስማት ከመጀመሩ በፊት ተከሳሹ ቀደም ሲል ወንጀል መፈጸሙን ያውቃል ፤ ካወቀም ይህንንም ወንጀል ሳይፈጽመው አልቀረም የሚል ግምት ሊያሳድርበት ይችላል ። ከሆነም የቁ. ፭፻፴፰ ዓላማን የሚቃረን ይሆናል ።

የፖሊስ ምርመራ ራፖርን በሚመለከት ረገድ ግን በራፖሩ ሥልጣን ያለው ዐቃቤ ሕግ በመሆኑ ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኛ ውሳኔዎች በፖሊስ ምርመራ ራፖር ቢገለጹ ክሱ በትክክለኛ መንገድ እንዳይታይ ሊያደርገው አይችልም የሚል እምነት ያለ ይመስላል ።[8] ቅጣትን ለማክበድ ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ካሉ መጠቀስ ያለባቸው ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ነው ። ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት ስለሚከብዱ ወንጀሎች ክስ አቀራረብ የተለየ ሥነ ሥርዓት መደንገግ ያስፈለገበት ምክንያት በቁ. ፭፻፴፰ የተደነገገው ዓላማ ተግባራዊ ሆኖ ክሱ በገለልተኛነት እንዲሰማ ለማድረግ ባይሆን ኖሮ የተለየ ሥነ ሥርዓት ባለስፈለገም ነበር ።

አንድ ተከሳሽ ልማደኛ ወንጀለኛ መሆን አለመሆኑን ማስረዳት የሚቻለው ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎችን በማስረዳት መሆኑ ግልጽ ነው ። በአንድ በንብረት ላይ በሚፈጸም ወንጀል የተጠረጠረ ግለሰብ ሲያዝና ምርመራ ሲደረግ ድርጊቶቹ የተለያዩ ወንጀሎች ናቸው ሊያሰኝ በሚያስችል "አዲስ ጥፋት"[9] ተደጋጋሚ የስርቆት ወንጀሎች ፈጽሞ ሊገኝ ይችላል ። እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ ቅጣት የሚወሰነው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥሮች ፷፭ እና ፭፻፹፱ በመሆኑ ምንም እንኳን ውጤቱ ቅጣትን ማክበድ ቢሆንም ቅጣቱ የሚከብደው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ. ፭፻፹፱ እንጂ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት አይደለም ። ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች አንድ ወንጀለኛ የወንጀሉን ድርጊት እንደሞያ ሥራው አድርጎ የሚጠቀምበት መሆን አለመሆኑን ለመወሰንም ይረዳሉ ። ለምሳሌ ያህል አንድ በማስወረድ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ወንጀለኛ በዚህ ወንጀል የበፊት ጥፋቶች ያሉት መሆኑን ዐቃቤ ሕጉ ለማስረዳት ከቻለ ክሱን የሚመረምረው ፍርድ ቤት ወንጀለኛው የማስወረድ ወንጀልን እንደሞያው አድርጎ የሚጠቀምበት መሆኑን ለመወሰን ይችላል ።

ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ ዐቃቤ ሕጉ አንድ ተከሳሽ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት በከባድ ወንጀል የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል የሚል እምነት ካደረበት ፥ ተከሳሹ መከሰስ ያለበት ቅጣት በማያከብደው ወንጀል ሆኖ ክሱ መቅረብ ያለበት ቅጣቱን የሚያከብደውን ወንጀል ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ነው ። ስለዚህ በቁ. ፭፻፹፰ የተገለጸው ዓላማ ግቡን እንዲመታ ለማድረግ የታቀደው ልዩ ሥነ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችለው ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት የሚከብዱ ወንጀሎችን ክስ የሚያየው ፍርድ ቤት እና ቅጣትን የማያከብዱት ወንጀሎችን ክስ የሚያየው ፍርድ ቤት አንድ ሲሆን ነው ።

የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት የሚከብዱ ወንጀሎችን በሁለተኛው ታላቅ ክፍል በሚገኙት በተለያዩ ቁጥሮች ይደነግጋል ።

በዚህ በሁለተኛው ታላቅ ክፍል የሚገኙት ቁጥሮች ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት የሚከብዱ ወንጀሎችን የሚገልጹ ሐረጎች "የዘ

---

4 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ 80(2)

5 ዐቃቤ ሕጉ ጥፋተኛ ስማድረግ በቂ ማስረጃ የሌለ መሆኑን የተገነዘበ እንደሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ 42(1) (ሀ) መሠረት ክሱ አላቀርብም የማለት ግዴታ አለበት ። ምንም እንኳን ይህ ቁጥር የቀዳሚ ምርመራ መዝገብን ባይጠቅስም ፥ የሥነ ሥርዓቱ ሕግ ቁ ፹/፪ እና ፭፻፱(፩) ብንመረምር ቁ ፵፪(፩) (ሀ) በቂ ማስረጃ በማያመለክት ቀዳሚ ምርመራ መዝገብም ተፈጻሚ መሆን ይኖርበታል ። በዚህ ነጥብ ፥ ፒ ግራሽን "ላ ኖቬል ፕሮሲጀር ፔናል ኢትዮጵያን ፥" ረብ ፔናል ስዊስ ፫፱አኔ እ ኤ አ ፲፱፻፷፫ የግርጌ ማስታወሻ ቁ ፭፱ በስታንሌ ዜድ ፊሸር ፥ ኢትዮጵያን ክሪሚናል ፕሮሲጀር ኤ ሶርስ በክ (ሕግ ፋኩልቲ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከእክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር ያሳተመው እ ኤ አ ፲፱፻፷፱ ዓ/ም) ፥ ገጽ 200 ይመለከቷል ።

6 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፭፻፯(፪)

7 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፭፻፵፭ትን ይመለከቷል ።

8 ትክክለኛ የሆነ ምርመራን በሚመለከት አንፃር የበፊት ጥፋቶች አጉል ግምት ሊያሳድሩ አይችሉም ወይ ? የሚል ጥያቄ ለመጠየቅ ይቻላል ። ሆኖም ሕጉ በዚህ ነጥብ የደነገገው የለም ።

9 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ 60-63 ይመለከቷል

ወትር የሞያ ሥራው ያደረገ" (በመንግሥቱ የቀረጥና የግብር ገቢዎችና በጠቅላላ የገንዘብ ጥቅሞቹ ላይ ስለ ሚሠሩ ወንጀሎች ቁ. ፻፻፷፭) ፡ "ልማዳዊ ወይም የሞያ ሥራ ሆኖ የተያዘ ጉዳይ" (ግልጽ በሆኑ ገንዘቦች ፡ ማሕ ተሞች ቴምብሮችና መሣሪያዎች ላይ ስለሚሠሩ ወን ጀሎች ቁ. ፻፻፹፭ (፩)) ፡ "ሞያው አድርጎ ይዞት እንደ ሆነ" (በሕዝብ ጥቅሞችና በማሕበራዊ ኑሮ ላይ ስለሚ ሠሩ ወንጀሎች ፡ የንግድ ዕቃዎችን ወደ ሐሰተኝነት ስለ መለወጥ ፡ ቁ. ፻፻፻ (፩)) ፡ "እንደ ሞያ ሥራው አድርጎ የያዘ እንደሆነ" (በቁ. ፩፻፲፩ እና ፩፻፲፯ ስተገለጹት ወን ጀሎች ማክበጃ)) ፡ "የማስወረድን ተግባር ሥራው አድርጎት እንደሆነ" (የማስወረድ ወንጀል ማክበጃ) ፡ "ሞያ አድርጎ የያዘ" (በመልካም ጠባይና በቤተ ዘመድ ላይ ስለሚደረጉ ወንጀሎች ፡ ቁ. ፭፻፭ (፩) (ለ)) ፡ "ሞያ ተብሎ በተያዘው አቃጣሪነት" (በመልካም ጠባይና በቤተ ዘመድ ላይ ስለሚደረጉ ወንጀሎች ፡ በሌላ ሰው አመንዝራነት ስለ መጠቀም ቁ. ፭፻፭) ፡ "ስርቆት ፡ ወይም ሌሎች ወንጀሎችን ሥራው አድርጎ የያዘ እንደሆነ" (በሀብት ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች ፡ ቁ. ፭፻፴፭ (፫)) (ሀ)) " የጦር መሣሪያ ይዞ የወንበዴነት ወንጀል መሥራትና ወንበዴዎችም ባንድ ክፍል የተቋቋሙ የውንብድና ማህበረተኞች የሆኑ እንደሆነ" (በሀብት ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች ፡ ቁ. ፭፻፴፯ (፪) ሁለተኛው አዲስ መስመር) ፡ "ያታላይነት ሥራ ሞያው አድርጎት እንደሆነ" (በንብ ረት መብቶች ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች ፡ ቁ. ፭፻፵፰ (ሁ)) ፡ እና "እንደ ሞያ ሥራው አድርጎ ይዞአል በሚያሰኝ ሁኔታ" (በንብረት መብቶች ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች ቁ ፭፻፸፪ (ሀ)) ናቸው ።

እነዚህን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሁለተኛውን ታላቅ ክፍል ቁጥሮችን ስንመረምር ፡ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥ ፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት ወንጀል ለማከበድ ሁለት መንገዶች መቀየሳቸውን እንገነዘባለን ። እነዚህም ፡-

ሀ/ ወንጀል የማክበድ ሁኔታን የሚያስከትሉ ድርጊ ቶች በአንድ የልዩ ክፍል ቁጥር ዘርዝሮ በመግለጽ እነዚህ ድርጊቶች ሲሟሉ ከአንድ ፍርድ ቤት ሥልጣን ውጭ ሊሆን በማይችለው ቅጣቱን በማያከብደው ወን ጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው ወንጀለኛ ቅጣቱ እንዲከብድበት በመደንገግ ፤[10]

ለ/ ወንጀል የማክበድ ሁኔታን የሚያስከትሉ ድርጊ ቶች በአንድ የልዩ ክፍል ቁጥር ዘርዝሮ ይህን የልዩ ክፍል ቁጥር ራሱን የቻለ ከባድ ወንጀል በማድረግ ቅጣ ቱን ከማያከብደው ወንጀል በመለየት ። በዚህ መንገድ የተለዩት ቅጣትን የማያከብዱ ወንጀሎች ክስ እና ቅጣ ትን የሚያከብዱ ወንጀሎች ክስ የማየቱ ሥልጣን በአ ንድ ፍርድ ቤት ወይም በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ሊሆን ይችላል ።[11]

ቅጣቱን የሚያከብዱ ሁኔታዎች የተደነገጉት ከላይ በፊደል (ሀ) በተገለጸው መንገድ ሲሆን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፭፻፴፭ ዓላማ ምንጊዜም ቢሆን ተግባራዊ ይሆናል ። ይህ የሚሆንበት ምክንያ ትም የልዩ ክፍሉ ቁጥር የተደነገገው የተለየ ወንጀልን ለመወሰን ሳይሆን በክፍሉ የተመለከቱት ወንጀሎች ቅጣትን በሚያከብድ ሁኔታ ሲፈጸሙ ቅጣቱ እንዴት መክበድ እንዳለበት በአጠቃላይ ክፍሉን የሚመለከቱ የማክበጃ ሁኔታዎች የሚደነገግ ስለሆነ እንደዚህ ዓይ ነቱ አንቀጽ የፍርድ ቤቶችን ሥልጣን በሚመለከት ረገድ የተወሰነ አንድ ፍርድ ቤት ብቻ እንዲያየው ሊደ ረግ የማይቻል በመሆኑ ነው ። ስለዚህ ቀደም ሲል በተ ሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት ቅጣት የሚያ ከብድ ክስ ወይም ቅጣት የማያከብድ ክስ ያው ሥልጣኑ የተወሰነው በአንድ ፍርድ ቤት ብቻ ስለሆነ ፡ አንድ ተከሳሽ ቅጣትን በማያከብድ ወንጀል ተከሶ በመቅረቡ ብቻ ፍርድ ቤቱ ይህ የሆነው ቀደም ሲል በተሰጡ የጥ ፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት መሆን አለበት የሚል ግምት ለመውሰድ አይችልም ።

ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታዎች የተደነገጉት ከላይ በፊደል (ለ) በተገለጸው መንገድ ሲሆን ግን ቅጣት የማ ያከብደውን ወንጀል እና ከባዱን ወንጀል ለማየት ሥል ጣን ያለው ፍርድ ቤት አንድ ፍርድ ቤት ካልሆነ የወ ንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. ፭፻፴፭ ዓላማ በተለየው ሥነ ሥርዓት ምክንያት ተግባራዊ ሊሆን አይ ችልም ። ይህንንም የተለየው ሥነ ሥርዓት ከሚደነግ ገው ከቁ ፭፻፲፬ ራሱ ለመገንዘብ ይቻላል ። ቅጣት የማያ ከብደውን ወንጀል እና ከባዱን ወንጀል ለማየት ሥል ጣን ሊኖራቸው የሚችል ፍርድ ቤቶች በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይኸው አን ቀጽ ጠቁሞ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ቀደም ሲል በተሰ ጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት ቅጣትን በሚ ያከብድ ወንጀል መቀጣት ያለበት ተከሳሽ መከሰስ ያለ በት ቅጣትን በማያከብደው አንቀጽ ሆኖ ክሱ ግን መቅ ረብ ያለበት ቅጣትን የሚያከብደውን ወንጀል ለማየት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት መሆን እንዳለበት ይደነ ግጋል ።

ይህንንም ሁኔታ በይበልጥ ለማብራራት ፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ. ፭፻፴፯ (፩) የተደነገገውን እንመልከት ። ለጊዜው የዚህን ቁጥር ንኡስ ቁጥር ፩ (ለ)ን ወደ ጎን በመተው ሌሎቹን የቅጣት ማክበጃ ሁኔታዎች ብንመ ረምር ፡ በክስ ማመልከቻው መዘርዘር ያለባቸውና ክሱ በሚሰማበት ጊዜም በማስረጃ መረጋገጥ ያለባቸው ሆነው እናገኛቸዋለን ። ይህም የሚሆንበት ምክንያት የወንጀሉ መክበድ የተመሠረተው ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተ ኛነት ውሳኔዎች ባለመሆኑ ነው ። በዚሁ ቁጥር ንኡስ ቁጥር ፩ (ለ) የተደነገገውን ስንመለከተው ግን የቅጣቱ ማክበጃ ምክንያት ቀደም ሲል የተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች መሆናቸው በግልጽ ይታያል ። የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ. ፭፻፴፭ ሥልጣን የአውራጃ ፍርድ ቤት የቁ. ፭፻፴፭ ደግሞ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢሆን ኖሮ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ምክንያት በቁ. ፭፻፴፭ መቀጣት የሚገባው ተከሳሽ መከሰስ ያለበት

10 ለምሳሌ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፻፻፷፭ እና ፻፻፹፭ን ይመለከቷል ።

11 ለምሳሌ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ ፭፻፴ እና ፭፻፴፭ እና ፭፻፴፯ እና ፭፻፴፯ን ይመለከቷል ።

በቁ. ፮፻፴፮ ሆኖ ክሱ ግን መቅረብ ይኖርበት የነበረው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆን ነበር ። ነገር ግን ፥ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት በቁ. ፮፻፴፮ ለመቀጣት አንድ ተከሳሽ በቁ. ፮፻፴፮ መከሰስ ይኖርበታል ። በመሆኑም ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሳሹ በቁ. ፮፻፴፮ ተከሶ የቀረበው ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት ብቻ መሆኑን በግልጽ ሊያውቅ ይችላል ማለት ነው ።

ቅጣት የማያከብደውን እና የሚያከብደውን የወንጀል ክስ ለማየት ሥልጣን የተሰጠው አንድ ፍርድ ቤት ብቻ ቢሆን ኖሮ ይህ የቁጥር ፩፻፴፭ ዓላማ ተግባራዊ አለመሆን በቲኦሪ ደረጃ ብቻ የሚያከራክር ሆኖ ይቀር ነበር ። ይህ መሆን አለመሆኑን ለመረዳት እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ወንጀሎች በሚመለከት ረገድ የፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክፍፍል መመርመር አስፈላጊ ነው ።

የተሰረዘው ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አንደኛ ሰንጠረዥን ስንመለከት ከላይ በፊደል (ለ) በተገለጸው መንገድ ከተመደቡት ወንጀሎች ውስጥ ከከባድ ለተፈጥሮ ግብር ተቃራኒ የሆነ የአመንዝራነት ሥራ (ቁ. ፮፻፩ (፩) (ለ)) እና ከከባድ ስርቆት (ቁ. ፮፻፴፭ (፫) (ሀ)) በስተቀር ቅጣትን የማያከብዱትን እና የሚያከብዱትን ወንጀሎች ለማየት ሥልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት አንድ ሆኖ እናገኘዋለን ። ስለዚህ እነዚህን ወንጀሎች በሚመለከት ረገድ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. ፩፻፴፭ ዓላማ ምንጊዜም ቢሆን ተግባራዊ ይሆናል ።

ከዚህ ከተሰረዘው አንደኛ ሰንጠረዥ እንደሚታየው ፥ ከባድ ለተፈጥሮ ግብር ተቃራኒ የሆነ አመንዝራነትን እና ከባድ ስርቆትን በሚመለከት ረገድ የቀድሞ የፍርድ ቤቶች ክስን የማየት ሥልጣን ክፍፍል የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. ፩፻፴፭ን ዓላማ ያፈርሰዋል ።

የተሻሻለው የፍርድ ቤቶች ሥልጣን ክፍፍል ግን[12] የተፈጥሮ ግብር ተቃራኒ የሆነ አመንዝራነትንና ማክበጃውን ወንጀል የማየት ሥልጣን የአውራጃ ፍርድ ቤት ብቻ እንዲሆን በመወሰን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፩፻፴፭ ዓላማ ተግባራዊ እንዲሆን አድርጎታል ። ይሁን እንጂ ሥርቆትን እና ከባድ ስርቆትን በሚመለከት ረገድ ማሻሻያው ሕግ ስርቆት የወረዳ ፍርድ ቤት ሥልጣን ፥ ከባድ ስርቆት ደግሞ የአውራጃ ፍርድ ቤት ሥልጣን እንዲሆን በመወሰኑ ፥ አውራጃው ፍርድ ቤትም ፥ ምንም እንኳን ክሱን መስማት ከመጀመሩ በፊት ተከሳሹ አሁንም እንደአመሉ የተከሰሰበትን ድርጊት ሳይፈጽም አይቀርም የሚል ግምት ሊያድርበት የሚችል ቢሆንም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ ፩፻፲ መሠረት የስርቆትን ክስ የመቀበል ግዴታ ስላለበት የስርቆት ወንጀልን በሚመለከት ረገድ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፩፻፴፭ ዓላማ ሙን ጊዜም ተግባራዊ ሊሆን አይችልም ። ታዲያ ይህ ግምት በተከሳሹ ላይ ለሚሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ ምክንያት ሊሆን አይችልም ማለት ይቻላል ወይ ?

መደምደሚያ

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ ፩፻፴፭ ዓላማ ሁል ጊዜ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም የሚል ግምት ያለ ለመሆኑ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ በቁ. ፩፻፲፬ በተደነገገው ልዩ ሥነ ሥርዓት ተጠቁሟል ። ዓላማው የስርቆትንና የከባድ ስርቆትን ወንጀሎች በሚመለከት ረገድ ምን ጊዜም ተግባራዊ እንደማይሆን በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት በቁ ፩፻፲ አስቀድሞ ታይ ቷል ።

ነገር ግን ከላይ እንዳየነው ሁሉ ፥ የተለየ ሥነ ሥርዓቱ ዓላማ ቁ. ፩፻፴፭ትን በተግባር በመተርጎም የአንድ ተከሳሽ የበፊት ጥፋቶች በተከሰሰበት ክስ በማስረጃ ጥፋተኛ ሆኖ ከመገኘቱ በፊት ፍርድ ቤቱን ጥፋት ፈጽሟል ወደሚል አጉል ግምት እንዳያመሩት ለማድረግ ነው ። ዳኛ ሰው ነውና የዚህ ዓይነቱ ግምት በጥፋተኛነት ውሳኔ አሰጣጡ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድርበት እንደሚችል አያጠራጥርም ። ስለዚህ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. ፩፻፴፭ ዓላማ ቀደም ሲል በተሰጡ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ምክንያት በሚከብድ በማንኛውም ወንጀል ሁሉ ተፈጻሚነት ቢኖረው ትክክለኛ ፍትሕን ለማስገኘት የሚያስችል መሣሪያ ስለሆነ የሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ፥ የሕግ ማሻሻያ ኮሚቴ በጉዳዩ ቢያስብበት ጠቃሚ እንደሚሆን ጸሐፊው ያምናል ።

---

12 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አንደኛ ሠንጠረዥ ማሻሻያ ደንብ ፥ ፲፱፻፭፰ ዓ/ም ቁ ፫ ፥ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ ፲፯ ነጋሪት ጋዜጣ ፥ ፴፬ኛ ዓመት ፥ ቁ ፴፰ ።

በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፩ሺ፯፻፷፯ ላይ

የተሰጠ አስተያየት ።

በጆ. ክሽችኖቢች*

አንቀጽ ፩ሺ፯፻፷፯ ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር ስለሚደረግ ውል

፩/ ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር የተደረጉ ውሎች ሊሻሻሉ የሚችሉት ፥ የውሉ ስምምነቶች የተፈጸሙበት የዋነኛው ስምምነት ሁኔታ በሕዝባዊ ባለ ሥልጣን የተለወጠ ሲሆንና ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋራ የተዋዋለው ሰው የውሉን ግዴታ ለመፈጸም የከበደ የገንዘብ ጉዳት የሚያመጣበት ወይም ለመፈጸም የማይቻል ሲሆን ነው ።

፪/ ስለእንደዚህ ያለው ጉዳይ በአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ስለ ተፈጸሙ ውሎች ሁሉ በዚህ ሕግ ስለ አስተዳደር ክፍል መሥሪያ ቤት ውሎች የተነገሩት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ ። (ከቁ ፫ሺ ፭፻፯—፫ሺ፭፻፺፫)

ከዚህ አንቀጽ የሚከተሉትን መገንዘብ ይቻላል ፡-

፩/ እኔ እንደማስታውሰው የአሁኑ ንኡስ አንቀጽ (፩) ይዘት ፥ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ውስጥ ከመንግሥት ጋር የሚደረጉ ውሎችን የሚመለከት ሰፊ አንቀጽ (ታይትል 19) እንዲጨመር ከመወሰኑ በፊት ገና እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፺፬ ዓ/ም ራሱን በቻለ አንቀጽነት የተዘጋጀ ነበር ። በኋላ ግን በዚህ ሁኔታ ተዘጋጅቶ የነበረው አንቀጽ የአንቀጽ ፩ሺ፯፻፷፯ ንኡስ አንቀጽ ፩ ሆኖ ንኡስ አንቀጽ ፪ እንዲጨመርበት ተደረገ ። በንኡስ አንቀጽ ፪ የአንግሊዝኛው ቅጂ አንቀጽ ፫ሺ፭፻፺፯ መሆኑ ቀርቶ ፫ሺ፭፻፺፯፩ መባሉ ግልጽ የሆነ የጽሑፍ ስህተት ስለሆነ መታረም ይገባዋል ።

፪/ በዚሁ በኋላ በተጨመረው ንኡስ አንቀጽ ፪ መሠረት ከመንግሥት የአስተዳደር ክፍል መሥሪያ ቤቶች ጋር የሚደረጉ ውሎችን በሚመለከት አግባብ አላቸው ተብለው የተጠቀሱት አንቀጾች ፥ በግልጽ እንደሚታየው ከንኡስ አንቀጽ ፩ ጋር የሚቃረኑት የመንግሥት ሥርዓት ንኡስ ክፍል አንቀጾች (ከአንቀጽ ፫ሺ፭፻፺፯-፫ሺ፭፻፺፺) ናቸው ። ስለሆነም የአንቀጽ ፩ሺ፯፻፷፯ ንኡስ አንቀጽ ፩ ተሽሮ ንኡስ አንቀጽ ፪ በሚከተለው ሁኔታ በመሻሻል ራሱን የቻለ አንድ አንቀጽ መሆን ይገባዋል ፥

አንቀጽ ፩ሺ፯፻፷፯ ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር ስለሚደርግ ውል

የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች የሚያደርጓቸውን ውሎች ከሚደነግገው አንቀጽ (ታይትል) ውስጥ የመንግሥትን ሥርዓት የሚመለከተው ንኡስ ክፍል አንቀጾች (ከአንቀጽ ፫ሺ፭፻፺፯-፫ሺ፭፻፺፫) ከአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ጋር በሚደረጉ በማናቸውም ውሎች ተፈጻሚዎች ይሆናሉ ።

ይህ አንቀጽ የቃላትን መደጋገም በማስወገድ ፥ የአስተዳደር ክፍል መሥሪያ ቤቶች የሚያደርጓቸውን ውሎች ከሚደነግገው አንቀጽ (ታይትል) ውስጥ "የመንግሥት ሥርዓት" የሚመለከተው ክፍል ብቻ የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ውል ተብለው የሚታወቁትን (በአንቀጽ ፫ሺ፭፻፸፪ እንደተተረጐመው) እና የአስተዳደር ክፍሎች የሚያደርጓቸውን የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ውል ያልሆኑትን ማናቸውንም ውሎች በሚመለከት ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን በግልጽ ያሳያል ።

የዚህ አንቀጽ በዚህ ሁኔታ መስተካከል አሁን ያለው የአንቀጽ ፩ሺ፯፻፷፯ አጻጻፍ ከፈጠረው አስፈላጊ ያልሆነ ጭንቀት ፍርድ ቤቶችን ይገላግላቸዋል ።

---

* የሕግ ፕሮፌሰር ፥ ሕግ ፋኩልቲ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

በከፍተኛው ፍርድ ቤት

የተሰጠ ፍርድ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት

የከፍተኛው ፍርድ ቤት

የፍ ብ መ/ ቁ ፫፱፪/፷፪

የካቲት ፷፪ ቀን ፲፱፻፷፷፪ ዓ/ም

ዳኞች ፤ ፩

፪

፫

አመልካች የይ.ኃ. ሞግዚት አቶ ዘ. ዓ.

ተቃዋሚዎች ፩ ወ/ሮ የ. ኪ. ማ.

፪ ” የ. አ. ኪ. ማ.

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል ።

ውሳኔ

አመልካች መስከረም ፷፱ ቀን ፲፱፻፷፰፪ ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታና መጋቢት ፷፩ ቀን ፲፱፻፷፰፪ ዓ/ም አሻሽለው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ላይ ይ.ኃ. ማ. የተባለው ሞግዚት የሆኑለት ልጅ ወ/ሮ ማ.እ. እና አቶ ኃ. ማ. ል. በ፲፱፻፶፭ ዓ/ም ተጋብተው ከላይ ስሙ የተጠቀሰው ልጅ በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም ከሁለቱ ሰዎች በጋብቻ ውስጥ ሲወለድ አቶ ኃ. ማ. ሰኔ ፲፮ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ስለሆነ ይ.ኃ. ማ. የአቶ ኃ. ማ. ልጅ መሆኑ ይታወቅልን በማለት ነው ። ከአቤቱታቸውም ጋር ፭/ መስከረም ፷፱ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ/ም አቶ ኃ.ማ.ለይ. ኃ.ማ. ማሳደጊያ የሚሆን በየወሩ ፶ ብር (ሃያ ብር) ለመክፈል የተስማሙበት አንድ ገጽ ሰነድ ፪/ መስከረም ፷፯ ቀን ፲፱፻፷ ዓ/ም አቶ ኃ.ማ.እና ወ/ሮ ማ. ተጋብተው ሲኖሩ ለመፋታት ስለፈለጉ የፍቺው ውሳኔ እስከ ተሰጠበት ጊዜ ድረስ ተለያይተው ለመኖር የተስማሙበትና እስከፍቺው ውሳኔ ድረስ አቶ ኃ. ማ. ለወ/ሮ ማ. በወር ፴ ብር (ሠላሳ ብር) ቀለብ ለመክፈል የተስማሙበት አንድ ገጽ ሰነድ ፫/ በጎዳር ፴ ቀን ፲፱፻፷ ዓ/ም አቶ ኃ. ማ. እና ወ/ሮ ማ. ባልና ሚስት ሆነው መኖራቸውን በመግለጽ ከዚህ ቀን ጀምሮ ግን መፋታቻቸውን የሚያመለክት አንድ ገጽ ሰነድ በማስረጃነት አያይዘው አቅርበዋል ።

ተቃዋሚዎቹም ለክስ ማመልከቻው በግንቦት ፲፮ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ/ም በተጻፈ መልሳቸው ላይ አቶ ኃ. ማ. ል. የወንድማቸው ልጅ መሆኑን በመግለጽ በጠላት ወረራ ዘመን አቶ ኃ. ማ. የስድስት ዓመት ልጅ ሆኖ ጣሊያንን ተከትሎ የመጣ ራያ አባለዘሩን ሙልጭ አድርጎ የሰለበው በመሆኑ ከሴት ጋር ለመገናኘት ፥ ሚስት ለማግባትም ሆነ ልጅ ለመውለድ የማይችል ስለሆነ ከወ/ሮ ማ. ጋር የቀጣሪና የግርድና እንጂ የባልና ሚስት ግንኙነት የላቸውም ፤ ይ. የተባለውም ልጅ የአቶ ኃ. ማ. ልጅ አይደለም በማለት መልስ ከሰጡ በኋላ ፭ኛ/ በሰኔ ፲፮ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ/ም አቶ ኃ.ማ.በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ተመርምሮ ስልብ እንደሆነ የተረጋገጠበት በሰኔ ፷፮ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ከሆስፒታሉ የተሰጠ የምስክር ወረቀት ፪ኛ/ አቶ ኃ. ማ. እካሉ የጎደለ መሆኑን በመግለጽ ንጉሡ እንዲረዱት በጎዳር ፷፮ ቀን ፲፱፻፸፮ ዓ/ም ማመልከቻ ያስገባበት ፫ኛ/ በዚሁ ማመልከቻ መሠረት የተጠቀሰው ጉዳት ደርሶበት እንደሆነ እንዲያስመስክር በታዘዘው መሠረት በጥር ፲፫ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ሦስት ምስክሮች ቀርበው አቶ ኃ. ማ. የተሰለበ መሆኑን የመሠከሩበት ጎዳር ፲፮ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም በቁ ፬፻፹፮/፷፰ በተጻፈ ደብዳቤ አማካይነት ከሊጋባው ጽ/ቤት የተላኩ ሁለት ገጽ ሰነዶችን አቅርበዋል ።

አመልካችም በበኩላቸው አቶ ኃ. ማ. እና ወ/ሮ ማ. ባልና ሚስት ሆነው በሚኖሩበት በጋብቻቸው ጊዜ ውስጥ ይ.ኃ.ማ. የተወለደ ለመሆኑ ያስረዳን በመሆናችን ልጅነቱ እንዳይታወቅ የሚያደርግ ምንም ዓይነት ማስተባበያ ተቃዋሚዎች ሊያቀርቡ አይችሉም ። በሕጉ መሠረት ይ. ልጅ ስለሆነ ተቃዋሚዎች ይህንን የመሰለ እንደመካድ ዓይነት መቃወሚያ በልጅነት ማሳወቂያ መዝገብ ውስጥ በመከላከያነት ሊያቀርቡ አይገባም ። የመካድን መብት የሚጠቀመበትም በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፶፻፶፫ ውስጥ የተዘረዘሩት ሰዎች እንጂ የወንድም ልጆች ሊጠቀሙበት አይችሉም ፤ አቶ ኃ. ማ. ራሱም ቢሆን ልጅ ለመሆኑ አምኖ ያቀፈውና ቀለብ የቆረጠለት ከመሆኑም በላይ ልጅ እንደተወለደለት በኢትዮጵያ ድምጽ ጋዜጣ ያወጣ ስለሆነ ተቃዋሚዎች ይህንን ለመካድ አይችሉም ሲሉ ተከራክረዋል ።

ይህም ፍርድ ቤት የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኋላ ጥቅምት ፷፩ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ/ም በዋለው ችሎት አመልካች ስለአቶ ኃ. ማ. እና ስለወ/ሮ ማ. ጋብቻ ካቀረቧቸው ሰነዶች ሌላ ሁለቱ በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም ተጋብተው ይ. የተባለውም ልጅ በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም በጋብቻ ውስጥ ለመወለዱ አራት ምስክሮች እንዲያስመስክሩ ተቃዋሚዎችም አራት የመከላከያ ምስክሮች እንዲያሰሙ አዘዘ ። በአመልካች በኩል የቀረቡት ምስክሮች አራቱም አቶ ኃ. ማ. እና ወ/ሮ ማ. በባልና ሚስትነት አብረው መኖራቸውንና በጋብቻቸውም ጊዜ ይ. ኃ. ማ. የተወለደ ለመሆኑ በአንድ ቃል መስክረዋል ። በመከላከያነት ከቀረቡት አራት ምስክሮች ውስጥ ሦስቱ ስልብ ነው በማለት ሲመሰክሩ ከነዚሁ መካከል ሁለቱ ወ/ሮ ማ. ገረድ እንደሆነች አቶ ኃ.ማ. ነግሮናል ፤ ልጅ የተወለደው ግን ወ/ሮ ማ. ከአቶ ኃ. ማ. ቤት እያለች ነው ሲሉ አንደኛው ምስክር ግን ወ/ሮ ማ. እና አቶ ኃ. ማ. በአንድ ክፍል ውስጥ ይተኙ ነበር በማለት መስክረዋል ።

በአመልካችና በተቃዋሚዎች በኩል የቀረበው ክርክርና ፍሬ ነገር ከዚህ በላይ እንደተዘረዘረው ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ መወሰን የሚገባው ጭብጥ በአቶ ኃ. ማ.

እና በወ/ሮ ማ. መካከል ሕጋዊ ጋብቻ አለ ወይስ የለም ? የሚለው ነው ።

በአቶ ኃ. ማ. እና በወ/ሮ ማ. መካከል የጋብቻ ውል እንደተፈጸመ በጽሑፍና በሰው ምስክር መረጋገጡ ታውቋል ። ይሁን እንጂ ፍትወተ ሥጋ ለመፈጸም ካል ተቻለ ጋብቻው ሊፈርስ የሚችል ለመሆኑ የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፭፻፻፯ ፣ ፭፻፻፭ (ሐ) ይገልጽልናል ። ፈቃድ በስህተት የተሰጠ ነው በማለት ለጋብቻው መፍረስ ጥያቄ ሊያቀርብ የሚችለውም ፣ ፈቃዱን በስህተት የሰጠው ተጋቢ (አንቀጽ ፭፻፻፭) ፣ ፈቃዱን በስህተት የሰጠው ተጋቢ ቤተ ዘመድ (አንቀጽ ፭፻፻፮ (፭) ፣ ፭፻፭፬) ዐቃቤ ሕግ (አንቀጽ ፭፻፻፮(፪) ብቻ ሊሆኑ ፣ ሌላ ማንም ሰው ቢሆን ይህንን ጥያቄ ሊያቀርብ እንደማይችል የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፭፻፻፮(፫) ይገልጽልናል ። ዐቃቤ ሕግም ቢሆን ይህን ዓይነት መቃወሚያ ሊያቀርብ የሚችለው ጋብቻው በተከበረበት ጊዜ ብቻ መሆን እንዳለበት የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፭፻፻፫ (፭) ያስረዳል ። ፈቃዱን በስህተት የሰጠው ተጋቢም ቢሆን የጋብቻን ማፍረስ ጥያቄ ለማቅረብ የሚችለው ስለሌላው ወገን ፍትወተ ሥጋን ለመፈጸም አለመቻሉን በተረዳው በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ (አንቀጽ ፭፻፻፭ (፭)) ፣ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ጋብቻው ከተፈጸመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ እንደማይችል አንቀጽ ፭፻፻፭ (፪) ያስረዳል ።

አቶ ኃ. ማ. ከሴት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ሊያደርግ የማይችል ሙልጭ ያለ ስልብ ለመሆኑ በተቃዋሚዎች በኩል የቀረበው የጽሑፍና የሰው ማስረጃ በበቂ ሁኔታ ያስረዳል ። ይሁን እንጂ አቶ ኃ.ማ. እና ወ/ሮ ማ. ጋብቻቸውን የፈጸሙት በ፲፱፻፻፭ ዓ/ም መሆኑ ሲረ ጋገጥ ወ/ሮ ማ. ሆኑ ወላጆቻቸው ወይም ዐቃቤ ሕጉ የመጨረሻ የፍቺ ውሳኔ (ስምምነት) እስከተደረገበት ጊዜ ማለትም እስከ ፲፱፻፻፮ ዓ/ም ድረስ አቶ ኃ. ማ. ፍትወተ ሥጋን ለመፈጸም የማይችሉ ናቸው በማለት ጋብቻው እንዲፈርስ በጊዜው ያልተጠየቀ በመሆኑ ፣ የአሁኑ ተቃዋሚዎችም ይህንን ዓይነት ክርክር ለማቅረብ መብት ስለሌላቸው ፣ ጋብቻ ስለመኖሩም በአመልካች በኩል በበቂ ሁኔታ የተመሰከረ ሲሆን በተቃዋሚዎች በኩል የመከላከያ ምስክሮች በበቂ ሁኔታ የጋብቻውን መኖር ያላስተባበሉ በመሆናቸው በአቶ ኃ.ማ.እና በወ/ሮ ማ. መካከል ከ፲፱፻፻፭ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፻፮ ዓ/ም ድረስ ሕጋዊ ጋብቻ አለ ብለን ወስነናል ።

ስለጋብቻው ውሳኔ ከተሰጠ ስለ ውጤቱ መመርመር ሁለተኛው መወሰን የሚገባው ጭብጥ ነው ። ሁለት ሰዎች ተጋብተው ሲኖሩ በጋብቻው ውስጥ የሚወለደው ልጅ ባል የተባለው ለተወለደው ልጅ ሕጋዊ አባቱ እንደ ሆነ የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፭፻፸ (፭) ፣ ፭፻፸፭ ፣ ፭፻፸፫ (፭) ፣ በግልጽ ያስረዳሉ።አቶ ኃ.ማ. እና ወ/ሮ ማ. ከ፲፱፻፻፭ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፻፮ ዓ/ም ድረስ በባልና ሚስትነት አብረው ሲኖሩ በ፲፱፻፻፱ ዓ/ም ይ. ኃ. ማ. ከወ/ሮ ማ. የተወለደ በመሆኑ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጾች መሠረት አቶ ኃ.ማ.የይ ኃ.ማ. ሕጊዊ አባት ናቸው ብለን ወስነናል ።

በሕጉ መሠረት ልጅነቱ የተወሰነበት ወገን የተጠቀሰውን ልጅ አባትነቱ ከተወሰነበት ሰው ሊወለድ አይችልም የማለት ክርክር ሊያቀርብ የሚችለው የመካድን ክስ በማቅረብ ስለሆነ ይህ የመካድ ክስ በልጅነት ማሳወቂያ መዝገብ ውስጥ በመከላከያነት ሊቀርብ ይችላል ወይስ አይችልም ? የሚለው ሌላው ጭብጥ ነው ። የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፭፻፸፰፪ እና እንዲሁም ተከታታዮቹ ቁጥሮች አተኩረን ብንመለከት የመካድ ክስ በመሠረቱ ሊቀርብ የሚችለው በመጀመሪያ ልጅነቱ በሕግ የተወሰነ ሲሆን ብቻ ነው ። አመልካች ይ.ኃ.ማ. የኃ. ማ. ልጅ ለመሆኑ ይታወቅልን በማለት ክስ የመሠረቱ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ልጅ ነው የሚለውን ውሳኔ ሳይሰጥ ወይም በሕጋዊ ግምት ልጅነቱ ሳይረጋገጥ የመካድን ክስ ለማቅረብ አይችልም ።

የመካድ ክስ በመከላከያነት ሊቀርብ ይችላል ቢባልም እንኳን የአሁን ተቃዋሚዎች እንደሚሉት ይ.ኃ.ማ. ልጅ አይደለም በማለት የመካድ ክስ ሊያቀርቡ ይችላሉ ወይስ አይችሉም ? የሚለው በመጨረሻ መወሰን የሚገባው ጭብጥ ነው ።

በሕጉ መሠረት አባትነቱ የተወሰነበት ወገን ሊወለድ አይችልም የሚለውን የመካድ ክስ ሊያቀርብ የሚችለው አባት ነው የተባለው ሰው ብቻ እንደሆነ የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፭፻፸፭ (፭) ይገልጽልናል ። ሆኖም ይህ አጠቃላይ ድንጋጌ በአንቀጽ ፭፻፻፫ ሥር ለሚመጡት ሁኔታዎች ልጅነት በመፍጠር ሌሎችም ሰዎች የመካድን ክስ ለማቅረብ እንዲችሉ አድርጓል ። እነዚህም ሰዎች አባት ነው የተባለው ሰው ወዳታች የሚቆጠሩ ተወላጆች (አንቀጽ ፭፻፻፫ (፫)) ናቸው ። ሌላ ሰው ግን ይህንን ጥያቄ ለማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ የፍትሐ ብሔር ሕግ ፭፻፻፫ (፫) ያስረዳል ። የአሁን ተቃዋሚዎች የአቶ ኃ. ማ. አክስቶች በመሆናቸው በአንቀጽ ፭፻፻፫ ሥር ከተዘረዘሩት ሰዎች ውጭ ስለሆኑ የመካድን ጥያቄ ለማቅረብ መብት የላቸውም ብለን ወስነናል ።

በአንቀጽ ፭፻፻፫ ሥር የተዘረዘሩት ሰዎች ቢሆንም እንኳን በዚህ መብት ለመጠቀም የሚችሉት አባት ነው የተባለው ሰው ችሎታ እያለው የመካድን ክስ ለማቅረብ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ሳያቀርብ የሞተ እንደሆነ ወይም ችሎታ ያጣ እንደሆነ ብቻ ለመሆኑ አንቀጽ ፭፻፻፫ (፭) ይገልጽልናል ። ይህም ጊዜ ልጁ በተወለደ በአንድ መቶ ሰማንያ ቀን ውስጥ ብቻ ለመሆኑ የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፭፻፻፮ (፭) ያስረዳል ። ይ. ኃ. ማ. የተወለደው በ፲፱፻፻፯ ዓ/ም ሲሆን ይህ የመካድ ክስ በመቶ ሰማንያ ቀን ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ ተቃዋሚዎች ይህንን የመካድ ክርክር አሁን ሊያቀርቡ አይችሉም ብለን ወስነናል ።

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ይ.ኃ.ማ. ሕጋዊ ልጅ ነው ብለን ልጅነቱን አውቀንለታል ። ተቃዋሚዎችም ለአመልካች ኪሣራ እንዲከፍሉ አዘናል ። የኪሣራው መጠን ዝርዝር በፍ/ ሥ/ ሥ/ ቁ ፬፻፸፫ - ፭፬ መሠረት ተዘጋጅቶ ሲቀርብ ይወሰናል ። የውሳኔው ግልባጭ ለሚፈልገው ወገን ለሚፈልገው መሥሪያ ቤት ይላክ ። ይህ ፍርድ ዛሬ የካቲት ፭፪ ቀን ፲፱፻፭፬ ዓ/ም አዲስ አበባ ባስቻለው የከፍተኛው ፍ/ቤት ሦስተኛ ፍትሐ ብሔር ችሎት ተሰጠ ።

በፍርዱ ላይ የቀረበ ትችት ።

በጆርጅ ክሽችኖቪች*

የቤተ ዘመድ ሕግ ፣ ስለ መወለድ ፣ አባት ነው ስለ ሚያሰኝ ግምትና በዚሁ ላይ ስለሚነሳ ክርክር አመልካች ይ. ኃ. ማ.

ተቃዋሚዎች ወ/ሮ የ. ኪ. ማ. እና ወ/ሮ የ. አ. ኪ. ማ.

የአዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐ ብሔር መዝገብ ቁጥር ፫፪፪/፷፪፪ ዓ/ም

በዚህ ትችት ውስጥ እላይ የተመለከተውን የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ እንመረምራለን ።

በአንድ ቀደም ሲል በቀረበ የመወለድ ጉዳይ ላይ ፣[1] የጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሰጥቷል ። በሰጠውም ውሳኔ ፤

"በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፯፻፵፭ እንደተጻፈው በጋብቻው ጊዜ የተፀነሰው (ወይም የተወለደው) ልጅ አባቱ ያው የናቱ ባል ነው" ፤ እና

"ልጁ አይደለም ብሎ ከሶ ከልጅነቱ ቢያስወግ ደው ራሱ አመዛዝኖ የሚያደርገው እንጂ ሌላ ማናቸ ውም ሰው የሱ ልጅ አይደለም ብሎ ለመክሰስ አይ ችልም" (የፍ. ብ. ሔ. ቁ. ፯፻፺) ብሏል ።

ይህ ፍርድ ቤቱ ለሕጉ የሰጠው ትርጉም በመሠረቱ ትክክልና[2] አሁን ትችት ከሚቀርብበት ከፍ. ፍ. ቤት ከሰጠው ውሳኔ ጋር ተስማሚ ነው ። ይሁን እንጂ አሁን ትችት የሚቀርብበት ጉዳይ ከቀድሞው ለየት ያለ በመሆኑ አስተያየት የሚሰጥበት ሆኖ ተገኝቷል ።

በጠቅላይ ፍ. ቤቱ ውሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ ልጁ ሕጋዊ አባቱን በመካድ ያቀረበው ክርክር ከሌላው አባቴ ነው ከሚለው ሰው መወለዱ እንዲረጋገጥና እን ዲወርሰው ካቀረበው ጥያቄ ጋር ተጣምሮ የቀረበ ክስ ነው ።

በሌላ በኩል ግን ፣ በዚህ አብዛኛውን ጊዜ በማያ ጋጥመው ጉዳይ ሕጋዊ አባት የሆነው የሟቹ አክስቶች ሟቹን ለመውረስ ጥያቄ ከማቅረባቸው በፊት ልጁ ከሟቹ መወለዱ እንዲታወቅለት የቀረበውን ጥያቄ በመቃወም ተከራክረዋል ። ሕጋዊ አባት የሆነው ሰው በአካል ስልብ መሆኑም ጉዳዩን የተለየ አድርጎታል ።

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ልል አስተያየት አትኩሮ ሲመለከቱት ፍርድ ቤቱ ሦስት ዋና ዋና ጭብጦችን የመዘነ መሆኑን ያሳያል ። እነዚህም ጭብጦች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ፡-

፩/ ልጁ በተወለደበት ጊዜ ፣ ሟቹን የልጁ ሕጋዊ አባት የሚያደርገው የጋብቻ ግንኙነት በእርሱና በልጁ እናት መሐከል ነበርን ?[3]

፪/ ልጁን "ለመካድ" የሚቀርብ ክስ ከላይ በቁጥር (፩) በተመለከተው ሁኔታ ሕጋዊ ልጅነቱ ከመ ረጋገጡ በፊት ሊቀርብ ይችላልን ?

፫/ ልጁን "ለመካድ" የሚቀርብ ክስ በሟቹ አክስ ስቶች ሊመሠረት ይችላልን ? ምንም እንኳን በከ ፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ውጤት ከሕጉ ጋር ተስማሚ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ከዚህ በላይ በተመለከቱት ጭብጦች ላይ የሰጠው ሐተታ ጉዳ ዩን ለመወሰን ከሚያስፈልገው በላይ ሆኖ ይታ ያል ።[4]

ይህም ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ስህተቶች ሊያስ ከትል ችሏል ። እነዚህን የተጠቀሱትን ሦስት ጭብጦች በቅደም ተከተል እንመለከታቸዋለን ።

፩ኛ/ ጭብጥ

ሀ/ ምንም የጋብቻ ውል ወይም ጽሑፍ አልቀረበም ። ፍርድ ቤቱ የጋብቻውን መፈጸም ያረጋገጠው በሌላ ማስረጃ ነው ። ይኸውም በተባሉት ባልና ሚስት መካከል (በሕሊና ግምት)[5] የባልና ሚስትነት

---

* የሕግ ፕሮፌሰር ፣ ሕግ ፋኩልቲ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

1 ይግባኝ ባዮች ፣ ገ. ጀ. እና ጀ. በ. ፣ መልስ ሰጭ ታ. የጠቅላይ ፍ/ቤት ፣ የፍትሐ ብሔር ይግባኝ ቁጥር ፭፻፴፭/፶፭ ዓ/ም የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት (እ ኤ አ ፲፱፻፷፭) ፣ ቅጽ 5 ፣ ገጽ 53 ።

2 በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፯፻፶፫ የተጠቀሱት ሰዎች "በርሱ ምትክ" የመካድን ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉት በአንቀጽ ፯፻፶፫(፩) የተመለከቱት የተ ለዩ ሁኔታዎች ሲኖሩ ብቻ ነው ። የዚህ አንቀጽ ርዕስ የእንግሊዝኛው ትርጉም ትክክል ስላልሆነ አሳሳች ነው ። ርዕሱ "የተለየ ሁኔታ" ተብሎ መነበብ ይኖርበታል (ትኩረት የተጨመረ) ።

3 በነገራችን ላይ ፣ የእንቀጽ ፯፻፶፭ ሕግ ግምት ቢነሳ ኖሮ ፣ ይህን "የጋብቻ ግንኙነት" ጭብጥ አስፈላጊ አይደለም ሊያሰኘው አይችልም ነበርን ?

4 የፈረንሳይ/እና የሌሎችም የአብዛኞዎቹ "የተጻፈ ሕግ" ያላቸው አገሮች ፍርድ ቤቶች የሚከተሉትን ዘዴ በሚቃረንሁኔታ ፣ ስታይልስ እፍ አፔሌት ጆዲሻል ዲሲሽንስ (ኡፐሳላ እ ኤ አ ፲፱፻፷፭) እና ፍክ ሽሚት ፣ ዘ ራሲዮ ዴሲዴንዲ (ኡፐሳላ እ ኤ አ ፲፱፻፷፭)ን ያስተያዩአል ።

5 የተሰጠው ፍርድ በዚህ ነጥብ ላይ ግልጽ አይደለም ።

ሁኔታ መኖሩን በአንቀጽ ፮፻፶፱-፮፻[6] በታዘዘው መሠረት (በፍርዱ ውስጥ አንቀጽ በግልጽ አልተ ጠቀሰም) የአራት ምስክሮችን ቃል አስረጅነት በቂ አድርጎ በመውሰድ ነው ።[7]

ለ/ ፍርድ ቤቱ እዚህ ላይ ማቆም ሲገባው ፣ ከዚህ አልፎ ጋብቻው የፀና መሆን አለበት በማለት በአ ንቀጽ ፮፻፶፭ ያልተመለከተ ሁኔታ ጨምሯል ። የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ በሕጉ ውስጥ የለም ። የጋብቻን ሁኔታ አለመጠበቅ በሚያስከትለው ቅጣት (አንቀጽ ፮፻፵ ፣ ፮፻፶ ፣ ፮፻፲፪ ፣ ፮፻፲፭ ፣ ፮፻፲፯ ፣ ፮፻፲፰) ምክንያት የተደረገ የጋብቻ መፍ ረስ እንደ ውል[8] ሕግ (አንቀጽ ፭ሺ፰፻፲፭) ወደ ኋላ ተመልሶ የሚሠራ ውጤት የለውም ። ቁጥር ፮፻፶፯ ፣ ንኡስ ቁጥር (፪ትን[9] እና በንኡስ ቁጥር (ሮ) ውስጥ ፣ "ያሉ ከሆነ ፣ ከፈረሰው ጋብቻ የተወለ ዱትን ልጆች ጥቅም" የሚሉትን ቃላት ይመለ ከቷል (ትኩረት የተጨመረ) ።[10]

ሐ/ ለአንቀጽ ፮፻፶፭ አሠራር ጋብቻው የፀና መሆን ይገባዋል ("በጋብቻ አብሮ መኖር") የሚባል ቢሆን ኖሮ እንኳን ፣ የሚች አክስቶች ጋብቻው "የፀና" አይደለም በማለት ያቀረቡትን ተቃውሞ አንቀጽ ፮፻፲፭ (፭)ድን[11] ብቻ በመጥቀስ ውድቅ ለማድረግ ይችል ነበር ። በዚህ ዓይነት ባይታገድም እንኳን ፣ የጋብቻውን መፍረስ ሊጠይቅ የሚች ለው ያገባው ሰው የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን መፈ ጸም የማይችል[12] መሆኑን ሳያውቅ የቆየው ሌላው ተጋቢ ወገን ብቻ መሆኑን በሚጠቁሙት በአ ንቀጽ ፭፻፶፮ እና ፭፻፶፭ (ሐ) መሠረት ውድቅ ማድ ረግ ይቻል ነበር ። ፍርድ ቤቱ እነዚህን አንቀጾች ጠቅሶ ነበር ፣ ነገር ግን በዚሁ በማቆም ፈንታ ለዚህ ጉዳይ አግባብ ከሌላቸው ስለ ጋብቻ "መቃወ ሚያ" ከሚያወሱት አንቀጾች (ቁጥር ፭፻፶፮ ንኡስ ቁጥር (፭) እና (ሮ) ጋር) በአንድነት አትቶባቸዋል።[13] በተጨማሪም ፣ ጋብቻው ከተፈጸመ በኋላ "መቃወ ሚያም" ሊቀርብ አይችልም (አንቀጽ ፭፻፶፫) ። በጊዜው ቢቀርብም ኖሮ እንኳን ለጋብቻው መፍ ረስ ምክንያት አይሆንም (አንቀጽ ፮፻፲፱ (ሮ))።

፪ኛ/ ጭብጥ

ይህም ፍርድ ቤቱ ግልጽ ባልሆነ መንገድ የተነሳው "ሌላ ጭብጥ" ከሦስተኛው ጭብጥ ውጤት አንጻር ሲታይ (እታች ይመለከቷል) አስፈላጊነት የሌለው ይመ ስላል ። ከዚህም በላይ ፣ በዚህ ላይ የሚደረግ ሐተታ መደጋገምን ወይም እርስ በርስ መቃረንን ያስከ ትላል ። ፍርድ ቤቱ አንቀጽ ፮፻፫፪ እና የሚከተሉ ትን አንቀጾች[14] መሠረት በማድረግ እንደገለጸው ሁሉ "በሕጋዊ ግምት ኃ. ማ. የይ. አባት መሆኑ የተረጋገጠ ለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ከመወሰኑ በፊት የመካድን ክስ ማቅረብ አይቻልም" ከተባለ ጭብጡ አስቀድሞ እንደተወሰነ ስለሚቆጠር ፣ (ሀ) ይህ ውሳኔ ቀደም ሲል እንደተወሰደ ከተቆጠረ ይህንኑ እንደጭብጥ መያዝ ለምን አስፈለገ ? ወይም (ለ) ገና በጭብጡ ላይ ውሳኔ ያልተደረሰበት ከሆነ ስለ "መካድ" መተቸት እንዴት ተቻለ ?[15]

፫ኛ/ ጭብጥ

የመጨረሻው ጭብጥ ጥያቄዎችን የያዘ ነው ። እነ ዚህም ፣ ፭ኛ/ የሚች አክስቶች ሚቹ ልጁን ለመካድ ያለውን መብት ሊጠቀሙበት ይችላሉን[16] ?
፮ኛ/ ይችላሉ ቢባልስ በጊዜው አንስተውታልን ?

ለመጀመሪያው ጥያቄ "አይችሉም" በማለት ፍ. ቤቱ ተገቢ መልስ ሰጥቷል ። ለመጀመሪያው ጭብጥ "አይችሉም" የሚል መልስ ከተሰጠ ክሳቸውን በጊዜ አቅርበዋል ወይስ አላቀረቡም ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠቱ የሚቹን አክስቶች ሕጋዊ አቋም ስለማይለ ውጠው ፍርድ ቤቱ በዚህ ላይ ሐተታ መስጠቱ አስፈ ላጊ አልነበረም ።

ፖሊሲ

"የፍትሐ ብሔሩ የመወለድ ሕግ"[18] አንዱ ዓላማ የውርስ ክርክሮችን መቀነስና እንዲሁም መሠረተ ቢስ በሆኑ የአባትነት ክሶች ወይም ክርክሮች የተነሳ የቤተ ሰቦች ሰላምና ደህንነት እንዳይናጋ ለመከላከል ቤተ ሰቦችን በጣም ደካማ ከሆኑ የአባትነት ጥያቄዎች ወይም

---

6 አንቀጽ የሚለው የምን እንደሆነ ባልተገለጸበት ቦታ የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽን ያመለክታል ።

7 በሶስት ምስክሮች ብቻ በቀረበ የማፍረሻ ማስረጃ ፊት (አንቀጽ ፮፻፶፱/፪) እንደተተረጎመው "የባልና ሚስትነት ሁኔታ ለመኖሩ" ጥቆማ ለማያደር ግው ።

8 "ውል" በአንቀጽ ፭ሺ፮፻፵፭ እንደተተረጎመው ።

9 "መፋታት" ውጤቱ ወደኋላ ተመልሶ የሚሠራ አይደለም ፣ ስለ መወለድ ዮተይነገገውንም አይነካም ።

10 የሕግ መሻሻል አጥኚ ኮሚቴ ፭ ፣ እ ኤ አ የ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ረቂቅ ፣ አንቀጽ ፻፻፭፮(፪) በዚህ ነጥብ ላይ እንዲያውም የበለጠ ግልጽ ነው ። ሬኔ ዳቪድ (የኛ የፍትሐ ብሔር ሕግ አርቃቂ) ፣ ለ ድርዋ ደ ላ ሩሚይለ ዴ ኮድ ሲቪል ኢትዮጵየ (ሚሊኖ ፣ ጎር ዮፍሬ ፣ እ ኤ አ ፲፱፻፷፮) ገጽ 57 ፣ ካቴሪን አ ዶኖቫን ፣ "ቮይድ ኤንድ ቮይደብል ማሮ የጅስ ኤን ኢትዮጵየን ሎዞየኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት (እ ኤ አ ፲፱፻፷፪) ፣ 8ኛ ቮልዩም ቁ. 2 ገጽ 446 እና 454 ያስተያዩአል ።

11 በእንግሊዝኛው ትርጉም ውስጥ "ሁሉኤቨር" የሚለውን (ከፈረንሳይኛው ዋና ጽሑፍ በተሳሳተ መንገድ የተተረጎመ) ዘ ፕርሰን ሁ) ("ሰልዊ ኪ") ተብሎ እንዲነበብ በማድረግ ያስተካክሏል ። የአማርኛውን ትርጉም ያስተያዩአል ።

12 ይህ ከአማርኛው የተወሰደ ነው ። የእንግሊዝኛውም የፈረንሳይኛው ቅጅዎች አንቀጽ ፭፻፶፭(ሐ) የበለጠ ጠንከር በማለት የብልትን አለመኖር ይጠ ይቃሉ ።

13 የጋብቻን መፈጸም ለማስቀረት ያለ የመቃወም መብት "ምክንያቶች" በማሳየት ላይ የተወሰነ አይደለም ።

14 በተለይም አንቀጽ ፮፻፶፫ እና ፮፻፶፭ ይመልከቷል ።

15 ፍ.ቤቱ "የመካድ ክስ በመከላከያ ማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል መሆኑን" ያለምክንያት ይጠቁማል ። ይህ አባት ለተባለው ሰው ብቻ የሚቻለው ሁኔታ ሊነሳ የሚቻለው እናትነትን ለመመሥረት ከሚነሳ ክስ ጋር በመያያዝ ነው (አንቀጽ ፮፻፵፱) ።

16 በዚህ ጉዳይ ውስጥ ስልብ ለሆነው ለወንድማቸው ልጅ ፣ ልጅ መውለድ "ፍጹም አለመቻሉን" (አንቀጽ ፮፻፶፭) በማንሳት ።

17 ፍርድ ቤቱ አንቀጽ ፮፻፲፫ አጣሞ ያነበበ መሆኑ በግልጽ ቢታይም ይህ የሰጠው የአሰታ መልስ ትክክል ነው ።

18 የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት (እ ኤ አ ፲፱፻፷፯) ፫ኛ ቮልዩም ። በተለይ ፣ ገጽ ፭፻፲፭ድን እና ፭፻፷፫ትን በአጭሩ ይመለከቷል ።

ክርክሮች ለመጠበቅ እንደሆነ መሆኑን ተመልክተናል ።[19]

ይህ ፖሊሲ መወለድን በተፈጥሮ ሕቅ ከማረጋገጥ ዓላማ ቅድሚያ ተሰጥቶታል ። ይህንንም ፣ በጋብቻና ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት በመኖር የሚመሠረት አባትነት ማፍረሻ የማይቀርብበት ሕጋዊ ግምት ለመ ሆኑ ፣ መረዳት ይቻላል ።[20] ይህ በከፍተኛ ፍርድ ቤት በትክክል የተወሰነው ጉዳይ ሕጉን ለመከተል ሲባል ምን ያህል ግልጽ የሆነ የተፈጥሮ ሐቅን (መሰለብ) ጉልህ በሆነ መንገድ ማለፍ እንደሚቻል በጥሩ ሁኔታ ያመለክታል ። ለመሆኑ በዚህ ለየት ያለ ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ ለሕጉ መሠረት የሆነውን ፖሊሲ አሟል ቷል ወይ ? ስልቡ ከመሞቱ በፊት ከሚስቱ ጋር ተፋ ትተው የነበረ መሆኑ ሲታይ ጥበቃ ይደረግለት የነበረው የሰላማዊ ቤተሰብ ደህንነት ነበር ማለት ይቻላል ወይ ? ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ የትኛውም ቢሆን ግልጽ ሕግ ከሐቅም ሆነ ከፖሊሲ በላይ ይሆናል ።[21] የሆነው ሆኖ የዚህ ጉዳይ ውጤት ትክክለኛ ነው ፣ ምክንያቱም ሟቹ የተቀበለውንና እንደራሱ ልጅ አድርጎ ይመለከ ተው የነበረውን ልጅ ጥቅም ጠብቋልና ነው ።

ሥነ ሥርዓት

ሳይናዘዝ የሞተ ሰው ውርስ "ሲከፈት" (አንቀጽ ፷፱፭) ፣ አብዛኛውን ጊዜ የአባትነት ጥያቄዎች የሚ ነሱት ለውርስ (ወይም በውርሱ ለመሳተፍ) ሲባል ነው ።[22] የልጅነት ሁኔታ (አንቀጽ ፯፱፫) የሌላቸው ልጆች በቁጥር ፯፱፫፱ና በሚከተሉት አንቀጾች መሠ ረት ፣[23] የአባትነት ሕጋዊ ግምትን ወይም አባትነትን ማወቅን ድጋፍ በማድረግ ለመውረስ ይጠይቃሉ ። በውርስ ሕግ የተደነገጉት ሥርዓቶች አብዛኛውን ጊዜ ይታለፋሉ ። በመሠረቱ በአንቀጽ ፯፱፬፩ ፣ ፯፱፬፩ ወይም ፯፱፬፯ መሠረት የሟቹ ሕጋዊ ልጅ የሆነ የውርስ ጠያቂ ሟቹ አባቱ ስለመሆኑ የፍርድ ማረጋገጫ እንዲሰጠው መጠየቅ ሳይኖርበት (ሯ፫ኛውን የግርጌ ማስታወሻ ይመ ለከቷል) ፣ የተጠቀሱትን የሕግ አንቀጾች ተፈጻሚነት በማስረዳት በአንቀጽ ፱፱፯፯ መሠረት የወራሽነት የም ስክር ወረቀት እንዲሰጠው በቀጥታ ማመልከት ይገ ባዋል ። ፍርድ ቤቱ ብዙ ልጆች ሲኖሩ እያንዳንዱ ልጅ ማመልከቻ ከማቅረቡ አስቀድሞ ስለውርስ ማጣራት የተደነገጉትን ሕጎች እንዲከተል ማድረግ ይኖርበታል ። ኑዛዜ የሌለ ሲሆን በአንቀጽ ፮፱፬፱ እና በሚከተሉት አንቀጾች መሠረት ልጅ ወደታች ተወላጅ ያልሆኑ ዘመ ዶችን በማገልገል ሕጋዊ ወራሽ ይሆናል ። ልጁ በቀ ጥታ የውርሱ አጣሪ ስለሆነ (አንቀጽ ፱፯፬፯) ፣ ኑዛዜ እንዳለ መፈለግ (አንቀጽ ፱፱፮፱) ፣ ኑዛዜ ከሌለ በእርሱ አስተያየት ውርሱ እንዴት እንደሚከፋፈል ለባለጉዳ ዮች ማስታወቅ አለበት (አንቀጽ ፱፱፱፱) ።[24] "ባለ ጉዳዮች" የሚባሉት የሟቹ ሌሎች ልጆች ብቻ ናቸው (አንቀጽ ፱፱፱፭ (፫)ትን ያስተያዩአል) ። እንደነዚህ ያሉት ልጆች ሁሉ ፣ በሕይወት ያሉም ሆኑ "በምትክ ነት የቀረቡ" (አንቀጽ ፮፱፬፱(፫)) ፣ "የሚካፈሉ" (አን ቀጽ ፮፱፬፱(፱) እና አብረው የሚያጣሩ[24] (አንቀጽ ፱፱ ፬፯) በመሆናቸው ፣ ከመካከላቸው ባንዱ ላይ ተቃውሞ አቅርበውበት ፍርድ ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ከሚያደርገው በስተቀር (አን ቀጽ ፱፱፯፭(፱)) ፣ ልጆች በአንድነት በአንቀጽ ፱፱፯፭ መሠረት ስለወራሽነታቸውና እኩል የሚካፈሉ ስለ መሆናቸው የሚያስረዳ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በአንድነት ጥያቄ ቢያቀርቡ ምንም ችግር አይፈጥ ርም ።

ትችት በተሰጠበት ጉዳይ ውስጥ የልጁ ሁኔታ ከዚህ የበለጠ ቀላል ነበር ። ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሚታየው የሟቹ ብቸኛ ልጅ ነበር ። ስለዚህ ወራ ሽና አጣሪ እርሱ ብቻ እንደመሆኑ ብቸኛ ወራሽነቱን የሚገልጽ የምስክር ወረቀት ከማግኘቱ በፊት ሊያስታ ውቃቸው የሚገባ "ባለጉዳዮች" አልነበሩም ። የልጁ ዓላማ ለመውረስ ነበር ከተባለ (በሞግዚቱ አማካይ ነት) ፤ በአንቀጽ ፱፱፯፭ የተመለከተውን ግልጽ ሥርዓት መከተል ነበረበት ።

---

19 እላይ በተጠቀሰው መጽሔት ውስጥ ፣ ፲፱ኛ የግርጌ ማስታወሻ ።

20 በዚያው መጽሔት ውስጥ ገጽ 513-514

21 ይበልጡን በአጠቃላይ ለሕጎች አተረጓጎም ከሚሠራው ከአንቀጽ ፭ሺ፭፻፴፫ ዓላማ የተወሰደ ። ይህ ዓላማ የሕዝቡን በሕግ ላይ የመተማመን ችሎታ ያጠናክራል ። አለዚያ ሕግ ማውጣት ራሱ ዋጋ የሌለው ይሆናል ።

22 በተተቸው ጉዳይ ውስጥ የይ. ማመልከቻ ዓላማ ይኸው የነበረ መሆኑን ያለጥርጥር መረዳት ይቻላል ።

23 እነዚህን ጥያቄዎች ሲመለከቱ ፍ/ቤቶች ብዙውን ጊዜ በማይሻሻል ሁኔታ ፣ (፮) "በግልጽ የታወቀ ጽሑፍን" አስፈላጊነት (አንቀጽ ፭፻፴፪) ፣ (፱) የልጅነት ሁኔታው አንዲታወቅለት ለማድረግ በእንድ ልጅ የሚቀርብ የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው ፣ የልጁ አባት ነው የሚባለው ሰው በክሱ ውስጥ እንዲገባ ተደርጎ ፣ በእናትዮዋ ወይም በወራሾችዋ ላይ ብቻ ነው የሚለውን ሕግ (አንቀጽ ፭፻፴፯ (፱-፫) ለመለጠፍ ሁኔታዎች ብቻ የተወሰነ ነው የሚለውን ሕግ (አንቀጽ ፭፻፴፭) ያልፋሉ ። ለእነዚህ ተስማሚ ያልሆኑ አንቀጾች የሕግ አውጭው ማብራሪያ አስፈላጊ ነው ። "ኒው ኩዊዝስ ኢን ፋሚሊ ሎው ፡" የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት (እ ኤ አ ፲፱፻፸፫) ፲ልዩም 9 ፣ ገጽ 204 ተመልከት ።

24 እርሱ ራሱ ፣ ወይም አካለ መጠን ያላደረሰ ሰው ከሆነ ፣ በሞግዚቱ አማካይነት (አንቀጽ ፱፱፶፩) (፩) ከ፱፱፻፱ ጋር ባንድነት ።

25 በትርጓሜው መሠረት "ባለጉዳዮች" ባልሆኑ ራቅ ባሉ ዘመዶች አይደለም ።

፩/ ከላይ የተመለከቱት አስተያየቶች የቀረቡት በታላቅ ትህትና ነው ። ከላይ ትችት የተሰጠበት የመወለድ ጉዳይ ውጤት ሙሉ በሙሉ ትክክል ቢሆንም ፣ የፍርዱ አጻጻፍ ይህ ያህል አይደለም ። የሌሎች እንዳንድ ፍርዶች አጻጻፍም ቢሆን እንደዚሁ ነው ። ይህ የፍርድ ቤቶች የአጻጻፍ ችግር አብዛኛውን ጊዜ የሚመነጨው ከፍርድ ቤቶች ሳይሆን በፈረንሳይኛው ዋና ጽሑፍ የተተረጎሙት የአማርኛና የእንግሊዝኛ ቅጅዎች (እና አንንዳንድ ጊዜ የፈረንሳይኛው ጽሑፍ ራሱ) ትርጉማቸው አሻሚ ከመሆኑና ሕጉን የሚያብራሩ ጽሑፎችም ካለመኖራቸው ነው ።

፪/ እኔ እስከማውቀው ድረስ ፣ የሕጋዊ ልጁን አባትነት ሕጋዊው አባት ራሱ ካልሆነ በስተቀር ሌሎች ሰዎች ለመካድ እንደማይችሉ በሚደነግገው ሕግ ላይ (አንቀጽ ፮፻፯)[26] ፍርድ ቤቶች የጸና አቋማቸውን ቀጥለዋል ።

26 በአንቀጽ ፮፻፶፫ በተመለከተው የተለየ ሁኔታ ጊዜ አንጂ ።

PREFACE

The last issue of the *Journal of Ethiopian Law* came out at the eve of the Revolution towards the end of 1973. That was another decade and another era. The Ethiopian nation has since passed through a lot of upheavals and undergone a fundamental reorientation of its values. The struggle is not over for it is a dynamic one that touches every aspect of the life of the nation. And Law and Justice are not areas least affected by the Revolution. This could very well be exemplified by the fact that a major characteristic of the Ethiopian Revolution has been its employment of the machinery of the law in bringing about fundamental social changes. As a matter of fact no basic change has been implemented without corresponding legal prescription.

We dedicate this and ensuing issues of the *Journal of Ethiopian Law* to the heroic Ethiopian people in their continuous struggle for social and individual justice in all sectors of life. At the same time we rededicate the Law and all its institutions to the Revolution and to the building of a Socialist society. We recognize the cardinal fact that the life of the law is a continuous struggle by nations, by classes and by individuals to bring about peace, justice and prosperity.

At this juncture an eminent jurist's teachings come to mind:

> *The law is not mere theory, but living force. And hence it is that Justice which, in one hand, holds the scales, in which she weighs the right, carries in the other the sword with which she executes it. The sword without the scales is brute force, the scales without the sword is the impotence of law. The scales and the sword belong together, and the state of the law is perfect, only where the power with which Justice carries the sword is equalled by the skill with which she hold the scales.*

To concieve of a modern socialist state is to visualise the sword and the scales pro perly balanced. And to effectively balance the sword and the scales a profound instruction- in the law and legal scholarship geared towards providing the best service to the nation is essential and a case in priority. The law, although recognised as one of the components of

social superstructure, it has in the course of time proved itself to be a most powerful component of the superstructure, precisely because of its capacity to affect and influence the social base by serving as a powerful policy instrument of the state.

That the *Journal of Ethiopian Law* reemerges after so many years of hibernation testifies to the heights the popular Revolution has reached. And taking its inspiration from the Revolution itself, the Journal pledges to contribute its share of upholding the revolutionary torch to build the new, strong and prosperous Ethiopia where peace and justice shall be nurtured.

We expect and hereby invite all professionals, be they academicians, court officials or lawyers serving in various capacity in and out of government, to rally round the Journal by contributing publishable materials and the necessary advice and support. We also thank all those whose contribution made possible this first issue of the *Journal of Ethiopian Law* after the Revolution.

Board of Editors

PROGRESS REPORT FROM THE DEAN
1971-72 E.C. (1978-80)

Fasil Nahum, Dean
Faculty of Law
Addis Ababa University

MAJOR DEVELOPMENTS 1971-72 E.C.

The significant task of making the Faculty of Law responsive to national needs at this crucial revolutionary period of intensive socialist change has never been felt more strongly. The challenge has been accepted with the clear conviction that the future holds greater achievements than the past. The establishment of the Faculty of Law in 1963 and subsequent first decade, which immediately followed the codification of Ethiopian Law, laid the foundation for relevant instruction and research in the legal field in Ethiopia. Though the intellectual atmosphere of the time was elitist and apolitical, intended to copy, reflect and not rise beyond the classical academic tradition, the establishment of the Faculty of Law on Ethiopian soil, and the examination of Ethiopian problems, was necessarily a major development. The social upheaval from 1974 onwards saw the temporary disintegration of the Faculty of Law, through dispersion of its academic staff; the majority of its large expatriate staff left Ethiopia, and its small and young Ethiopian staff were involved either in further studies abroad or in helping to fill up vacuums in important government offices.

As a matter of fact, the Faculty of Law has yet to recover from its acute staff shortage. The academic year 1978-79 saw us start with only six full-time instructors and one half-time instructor comprising the whole academic staff of the Faculty of Law. On the other hand, the Faculty has never in its history had more students. Coupled with this, the purposeful curricular experimentations geared towards providing the students with the best possible legal education, has made these years a hectic and difficult period. Yet it is through struggle that one moves forward and the faculty is amply compensated for its struggles in terms of the results it has achieved. Some of the highlights of its achievements are the following:

I. Curricular Development

A. *Curriculum Workshop:* After several years of experimenting with the curriculum of the Faculty in order to produce technically competent and politically attuned graduates to serve as a policy-maker component of government administration, we arranged for a curriculum workshop. The workshop was an intensive 3-day meeting that took place from July 13 to 15, 1979, in which academic staff, graduates and government officials participated. The Ministry of Law and Justice as our primary employer and the institution most concerned was represented by a strong four-man delegation headed by the Permanent Secretary. Chief legal advisers from most government institutions and High Court and mass organization tribunal judges also participated. In addition, a Higher Education Commission representative and the Academic Vice-President of the University participated both as lawyers and in their official capacity. The workshop was a complete success in terms of the far-reaching policy decisions it recommended. The implications of these recommendations and their implementation is of course a longterm project to be carefully worked out by the Faculty.

Further details can be gathered from the minutes of the workshop, which are attached as Appendix I, and its 21-point resolution attached as Appendix II.

